# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን

## የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም የስራ አፈፃፀም በተመለከተ

## የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (Executive Summery) ........ V
ክፍል አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
ተቋማዊ ደሰሳ ........ 1
የኮሚሽኑ አመሰራረት ........ 1
የኮሚሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል ........ 5
ድርጅታዊ መዋቅር ........ 5
የኦዲቱ ዓላማ ........ 6
ክፍል ሁለት ........ 8
ግኝቶች ........ 8
ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂን ስራ ........ 8
ላይ ለማዋል አስፈላጊ ህጎች፣መመሪያዎችና ማዕቀፎችን ........ 8
ሊያዘጋጅ እና የአፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት ........ 8
የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 8
ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ የአደጋ ምላሽ እና ........ 9
የአደጋ ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞችን ........ 9
ያስተባበረ፣ የተከታተለና የገመገመ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 9
ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣ ........ 12
ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ ክምችት የሚይዝ፣ ........ 12
የሚያስተዳድር እና ለምላሽ ስራ የሚያውል መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 12
ኮሚሽኑ የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ምግብ ዕርዳታ ማቅረብ ........ 14
አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ከስትራቴጂክ የመጠባበቂያ ........ 14
ምግብ ክምችት የዕርዳታ እህል በመውሰድ በወቅቱ ........ 14
የሚያሰራጭ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 14
ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በአገር አቀፍ ደረጃ ........ 15
የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ዝግጅትና ክለሳ ስራን የሚመራ እና ........ 15
የሚያስተባብር መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 15
ኮሚሽኑ የአደጋ ጥናት መረጃ ላይ ያተኮረ ምላሽ ........ 17

የሚሰጥ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 17

ኮሚሽኑ በቅድመ-አደጋ፣ በአደጋና በድህረ-አደጋ ወቅት ........ 19

የአደጋ ስጋት ትንበያን ጨምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ ........ 19

የሚካሄዱ ጥናቶችንና ግምገማዎችን የሚመራ እና ........ 19

የሚያስተባብር መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 19

ኮሚሽኑ የፌደራል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ........ 20

የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከልን ስራ ........ 20

በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ የሚያስተዳድርና ........ 20

የሚመራ መሆኑን በተመለከተ፡ ........ 20

ኮሚሽኑ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ........ 22

ማስተባበሪያ ማዕከልን በፌደራል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ መስተዳድሮች ........ 22

በሚገኙ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች እንዲመሰረት ድጋፍ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ ........ 22

ኮሚሽኑ የመረጃና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ........ 24

ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል ........ 24

ሁኔታዎችን ያመቻቸና ድጋፍ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 24

ኮሚሽኑ በየደረጃው የሚቋቋሙ የአደጋ ክስተት ማስተባባሪያ ........ 26

መዋቅሮች በአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል አስተማማኝና ........ 26

የማያቋርጥ የመገናኛ መሳሪያወች እንዲኖራቸው ........ 26

ማድረጉን በተመለከተ፡- ........ 26

ኮሚሽኑ አደጋ በይፋ መገለፁን ተከትሎ ........ 28

የአደጋ ስራ አመራር ምክር ቤት ሲወስን ከአገር ውስጥና ........ 28

ከውጭ ሀገር ሀብት ያሰባሰበ እና ለአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ስራ ........ 28

ጥቅም ላይ እንዲውል ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 28

ኮሚሽኑ ውጤታማ የሆነ የሀብት አሰባሰብ፣ አያያዝና ........ 29

አጠቃቀም ስርዓት የዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 29

ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ሀብት ከውጭ ሀገር የማሰባሰብና ........ 32

የመጠቀም አሰራርን በተመለከተ መመሪያ በማውጣት ........ 32

ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 32

ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር ስርዓትን ለመዘርጋትና ........ 37
ለመተግበር የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በየደረጃው ........ 37
ያከናወነ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 37
ኮሚሽኑ በክልሎች መካከል በአደጋ ጊዜ ተደጋግፎና ........ 40
ተባብሮ የምላሽ ስራን ለመስራት የሚያስችል ........ 40
አሰራር ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 40
ኮሚሽኑ የመረጃ አስተዳደርና ኮሙኒኬሽን ስርዓት ........ 41
በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና በአደጋ ክስተት ስጋት ........ 41
ፕሮፋይል ላይ የተመሰረተ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 41
ኮሚሽኑ ከውጭ በዕርዳታ መልክና በግዥ ወደ ሀገር ውስጥ ........ 42
የሚያስገባቸውን ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውሉ ምግብና ምግብ ነክ ........ 42
ያልሆኑ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች በወቅቱ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ........ 42
እንዲገቡ ያደረገ ስለመሆኑ በተመለከተ፡- ........ 42
ኮሚሽኑ የክምችት መጋዘኖች የሚገቡ/በክምችት ያሉና የሚወጡ ........ 43
ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች የተቀመጠውን የጥራት ደረጃ ........ 43
ያሟሉ ስለመሆናቸው የተከታተለና የተቆጣጠረ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 43
ኮሚሽኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን (ማዕከላዊ መጋዘኖችን) ........ 45
ባግባቡ የመራ፤ያስተባበረና የተቆጣጠር መሆኑን  በተመለከተ፡- ........ 46
ኮሚሽኑ የክምችትና የስርጭት መመሪያ ........ 48
በማውጣት ተግባራዊ ያደረገ እና በየደረጃው ........ 48
ተፈፃሚ ስለመሆኑ የተከታተለና የተቆጣጠር መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 48
ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውል ሀብት ........ 51
ባግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ስለመቆጣጠሩ በተመለከተ፡- ........ 51
ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይልን መነሻ ያደረገ ........ 52
የመጠባበቂያ ዕቅድ በየጊዜው በማዘጋጀት ........ 52
ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 52
ኮሚሽኑ ቅፅበታዊ ለሆኑ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት ........ 53
የሚያስችል ቀልጣፋ የሆነ የአሰራር ስርዓት ........ 53

ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡- 53
ኮሚሽኑ በአደጋ የተጎዱ ወይም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ 58
እንስሳቶችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር 58
የዘረጋና ተግባራዊ ያደርገ መሆኑን በተመለከተ፡- 58
ኮሚሽኑ የክትትልና ግምገማ ስርዓት የዘረጋና 59
ተግባራዊ ያደርገ መሆኑን በተመለከተ፡- 59
ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር በመንግስት 62
የልማት ፖሊሲዎች፣ስትራቴጂዎች፣ የልማት ዕቅድና 62
ፕሮግራሞች እንዲሁም በስርዓተ ትምህርት መካተቱን 62
ያረጋገጠና ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን በተመለከተ፡- 62
ኮሚሽኑ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች ተብሎ የተሰየሙ 63
የፌደራል መንግስት የአስፈፃሚ አካላት በዕቅዳቸው ውስጥ 63
የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ማካተታቸውን የሚያረጋግጥና 63
አፈፃፀሙን የሚከታተል መሆኑን በተመለከተ፡- 63
ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው መሪ ሴክተር መ/ቤቶችና 64
ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር የዘረጋና 64
ተግባራዊ ያደርገ መሆኑን በተመለከተ፡- 64
ኮሚሽኑ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴዎች 65
ከአካባቢ ሁኔታ ጋር የሚስማሙ መሆኑን የገመገምና ለአካባቢ ጥበቃ 65
ትኩረት መስጠታቸውን ያረጋገጠ መሆኑን በተመለከተ፡- 65
ክፍል ሦስት 67
መደምደሚያ 67
ክፍል አራት 71
የማሻሻያ ሃሳቦች 71
አባሪ አንድ 1
አባሪ ሁለት 2
አባሪ ሦስት 6

## የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (Executive Summery)

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት በብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራ አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2008 እስከ 2010 በጀት አመት ድረስ ባለው ጊዜ ሲሆን የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በኮሚሽኑ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም የስራ አፈፃፀም ሥራ ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ያለመ ነው፡፡

ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ሲሆን በኮሚሽኑ ስር ከሚገኙ ከሦስቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ውስጥ በናሙና በተመረጡ (በአዳማ እና በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች) እንዲሁም ክልሎች (በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በጌዲኦ ዞን) በመገኘት የተለያዩ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን በመከለስ፣ በመተንተን እና ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ለባለድርሻ አካላት ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ በተጨማሪም የኦዲት ቡድኑ በአካል ተገኝቶ ስራዎችን ቅኝት በማድረግ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሚከተሉት ዋና ዋና ግኝቶች ተገኝተዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂን ስራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ህጎች፣መመሪያዎችና ማዕቀፎችን አለማዘጋጀቱ እና የአፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ::
2. ኮሚሽኑ በየደረጃው የሚከናወኑ የአደጋ ምላሽ ፕሮግራሞች የተቀናጀ፣ በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተና ያልተማከለ የአሰራር ስርዓትን በመዘርጋት በየደረጃው መወሰድ የሚገባቸውን ተገቢ እርምጃዎች በወቅቱና በየደረጃው በተሟላ ሁኔታ እንዲወሰዱ ያላደረገ መሆኑ::
3. ኮሚሽኑ የአደጋ ጊዜ ፈንድ መመሪያ እና የክምችትና ስርጭት መመሪያ የሌለው መሆኑ፣ በክምችት መጋዘኖቹ ለአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል ቁሳቁስ ክምችት እጥረት መኖሩ በተገለፀበት ሁኔታ ያለምንም መመሪያና የአሰራር ስርዓት ከአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለገቢያ ማረጋጊያ በሚል ስንዴ ወጪ የተደረገ መሆኑ እና ለተጎጂዎች በጥሬ ገንዘብ የሚቀርበው ዕርዳታ በተመለከተ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ በመመሪያ የተደገፈ አሰራር ስለመኖሩ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ::
4. ኮሚሽኑ የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችትን በአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ የሌለው መሆኑና የእርዳታ ዕህል ለሌላ አላማ በመውሰድ ጥቅም ላይ እያዋለ አለመሆኑ::

5. ኮሚሽኑ በአደጋ ጥናት መረጃ ላይ ያተኮረ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ጥናት በተሟላ ሁኔታ አለማከናወኑንና በየጊዜው ክለሳ ያላደረገባቸው በመሆኑ የተነሳ በመረጃ ላይ ያተኮረ ምላሽ እየሰጠ አለመሆኑ::
6. ኮሚሽኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ በቅድመ-አደጋ፣ በአደጋና በድህረ-አደጋ ወቅት እና የአደጋ ስጋት ትንበያን ጨምሮ በማጥናት፣ በማስተባበርና በመገምገም ተግባራዊ ስለማድረጉ የሚያመላክት የሰነድ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ::
7. ኮሚሽኑ የፌደራል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከልን ስራ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያልተደገፈ መሆኑ::
8. ኮሚሽኑ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከልን በፌደራል፣ በየደረጃው ባሉ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች እንዲመሰረት አለማድረጉ::
9. ኮሚሽኑ መረጃዎች በተማከለ ቦታ የማይያዙ መሆኑንና ወቅቱን የጠበቀና የተናበበ የኢንፎርሚሽን ቴክኖሎጂ ሲስተም ተግባራዊ አለመደረጉ::
10. ኮሚሽኑ በየደረጃው የሚቋቋሙ የአደጋ ክስተት ማስተባባሪያ መዋቅሮች በአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉ አስተማማኝና የማያቋርጥ የመገናኛ መሳሪያ አማራጭ አለመኖሩና በአብዛኛው በስልክ አገልግሎት ላይ ብቻ የተንጠለጠለ መሆኑ::
11. ኮሚሽኑ አደጋ በይፋ መገለፁን ተከትሎ የአደጋ ስራ አመራር ም/ቤት ሲወስን ከአገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ሀብት በማሰባሰብ ለአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ስራ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የሃብት ማሰባሰብ፣ አስተዳደር፣ የፕሮጀክት አደረጃጀትና ሂደት፣ የፈንድ ግንባታና ጠቀሜታ፣ የድጋፍ ግንኙነትን በተመለከተ ህጋዊ የሆነና መንግስታዊ እውቅና ያለው የአሰራር መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆን አለማድረጉ::
12. ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ሀብት ከውጭ ሀገር የማሰባሰብና የመጠቀም አሰራርን በተመለከተ መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ::
13. ኮሚሽኑ በመዋቅሩ መሰረት የሰው ሀይል ሊያሟላ እና በአደጋ ክስተት ስራ አመራር የተሰማራ የሰው ኃይል እውቀቱንና ክህሎቱን በስልጠና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማዳበር እንዲያስችል የስልጠና ማዕከል በማቋቋም እየሰራ አለመሆኑ::
14. ኮሚሽኑ በአደጋ ክስተት ስራ ዙሪያ የሚወጡ ህጎች፣ መመሪያዎች፣ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች እንዲሁም የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎች ውስጥ ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ ለአረጋዊያን፣ ለአካል ጉዳተኞችና ኤች.አይቪ. ኤዲስ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ ትኩረት ስለመሰጠታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር ያልዘረጋ መሆኑ::
15. ኮሚሽኑ በክልሎች መካከል በአደጋ ጊዜ ተደጋግፎና ተባብሮ የምላሽ ስራን ለመስራት የሚያስችል አሰራር ተግባራዊ አለመደረጉ::

16.ኮሚሽኑ የመረጃ አስተዳደርና ኮሙኒኬሽን ስርዓት በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና በአደጋ ክስተት ስጋት ፕሮፋይል ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ እና ወቅታዊና ለሁሉም ተደራሽ አለመሆኑ::

17.ቁሳቁሶች የተቀመጠውን የጥራት ደረጃ ያሟሉ ስለመሆናቸው ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል መዋቅር በመዘርጋትና የሰው ኃይል በመመደብ እየሰራ አለመሆኑ::

18.ኮሚሽኑ ለጽ/ቤቶች (ማዕከላዊ መጋዘኖችን) ተግባርና ኃላፊነቶችን ለይቶ በማውረድና የሰው ሀይል ቅጥርና ቁሳቁሶችን በሚሟላት እየመራ አለመሆኑ::

19. ኮሚሽኑ የክምችትና የስርጭት መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ አለማድረጉ እንዲሁም በየደረጃው ተፈፃሚ ስለመሆኑ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር አለማድረጉ::

20. ኮሚሽኑ ለምላሽ ስራ የሚውል መጠባበቂያ በጀት፣ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ እንዲሁም በተጨማሪ በመንግስት የሚመደብና በዕርዳታ የሚሰበሰብ ሀብት በአግባቡ ለምላሽ ስራው ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የሚያስችል ግልፅ የሆነ አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ አለማድረጉ እንዲሁም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ኦዲት ተደርገው የማያውቁ መሆኑ::

21.ኮሚሽኑ ለቅፅበታዊ አደጋ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ቀልጣፋ አሰራር እንዲሁም ፈጣንና ዘመናዊ የሎጂስቲክስ አገልግሎት በመዘርጋት ተግባራዊ እያደረገ አለመሆኑ::

22.ኮሚሽኑ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ግቢ ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ ተሽከርካሪዎችና ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት ተከማችተው የሚገኙ መሆኑና አለመወገዳቸው እንዲሁም ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያስፈልጉ ቋሚ ንብረቶች ያልተሟላ መሆኑ::

23.ኮሚሽኑ በአደጋ የተጎዱ ወይም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ እንስሳቶችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ::

24. ኮሚሽኑ ያከናወናቸውን የአደጋ ምላሽ ስራዎችን እና የመልሶ ማቋቋም ስራዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ አለማድረጉ::

25.ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር በመንግስት የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የልማት ዕቅድና ፕሮግራሞች፣ በግል መ/ቤቶች ዕቅዶች እንዲሁም በስርዓት-ትምህርት እንዲካተት አለማድረጉ::

26. ኮሚሽኑ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴዎች ከአካባቢ ሁኔታ ጋር የሚስማሙ መሆኑን በመገመግም ለአካባቢ ጥበቃ ትኩረት መስጠታቸውን የሚያረጋግጥበት አሰራር ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ:

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ኢትዮጵያ በከፍተኛ ደረጃ በአደጋዎች የምትጠቃ ሀገር ስትሆን ከአደጋዎቹ ውስጥ ድርቅ፣ ጎርፍ፣ የሰውና የእንስሳት በሽታ፣ የሰብል በሽታ እንዲሁም ግጭት ተጠቃሾቹ ናቸው፡፡ከነዚህ ውስጥ ድርቅ ከፍተኛውን ቦታ ሲይዝ ጎርፍ በሁለተኛ ደረጃ ተጠቃሽ በመሆን ጉዳት በማድረስ የሚታወቁ ናቸው፡፡ የቅርብ ጊዜ ክስተቶች በግልጽ እንደሚያመለክቱት በአየር ንብረት ለውጥና ተያያዥ ሁኔታዎች ምክንያት የአደጋዎቹ መጠን፣ የሚያካልሉት ስፋትና ድግግሞሹ እየጨመረ መምጣቱን ነው፡፡
2. በኢትዮጵያ ከደረሱት የርሀብና የበሽታ ሁኔታዎች ለመጀምሪያ ጊዜ የአይን ምስክርነት መረጃ የተገኘው እ.ኤ.አ በ1520 አካባቢ ነው፡፡ ከዚያ ወዲህ መጠኑ እና ዓይነቱ ይለያይ እንጂ ረሀብ በጎንደር እና በሸዋ ነገስታት ጊዜ በ1623 ዓ.ም.፣ በ1650 ዓ.ም.፣ በ1653 ዓ.ም.፣ በ1678 ዓ.ም.፣ በ1700 ዓ.ም.፣ በ1702 ዓ.ም.፣ በ1747 ዓ.ም.፣ በ1748 ዓ.ም. እና በ1752 ዓ.ም. በተደጋጋሚ ተከስቷል፡፡ እንደገና በ1889 ዓ.ም ከሁሉም የበረታና ችግሩ በስፋት የተመዘገበበት ርሃብ የደረሰ ሲሆን፣ ችግሩ በትግራይ፣ በበጌምድር፣ በጎጃም እና በሸዋ ክፍላተ ሀገራት በበርካታ ከብቶች ላይ እልቂት አድርሷል፡፡
3. በ20ኛው ክፍለ-ዘመን ደግሞ በተለይ በአዲስ አበባ አካባቢ ከደረሰው ‹የህዳር በሽታ‹ በስተቀር ጉልህ የርሃብ ታሪክ እስከ 1951 ዓ.ም አልተመዘገበም፡፡ ይሁን እንጂ በ1951 ዓ.ም.፣ በ1957 ዓ.ም. እና በ1963 ዓ.ም በተለያዩ አካባቢዎች ድርቅና ርሃብ ደርሶ ብዙ ሺህ ሰዎች የጉዳቱ ሰለባ ሆነዋል፡፡ እንዲሁም በ1977 ዓ.ም በኢትዮጵያ የታየው ረሀብ እጅግ አስከፊ ረሃብ ነበር፡፡

### ተቋማዊ ደሰሳ

### የኮሚሽኑ አመሰራረት

4. በኢትዮጵያ በተለያየ ጊዜያት በነበሩ ተከታታይ የድርቅ ክስተቶች በሀገሪቱ ላይ ለደረሰው ችግር መፍትሄ ለመፈለግ በየአስተዳደር ስርዓቱ እና ዘመኑ መጠነኛ እንቅስቃሴዎች የነበሩ ቢሆንም፣ ነሀሴ 23 ቀን 1966 ዓ.ም የእርዳታ ማስተባበሪያና መቋቋሚያ ኮሚሽን በአዋጅ ትዕዛዝ ቁጥር 96/66 ዓ.ም ለደረሰው ችግር መፍትሄ ለማፈላለግ እንደገና ለማቋቋምና ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር የሚገኘውን ድጋፍ ለማስተባበር ተቋቋመ፡፡ ትዕዛዙን ተከትሎ የድርቅ ቀበሌዎች እርዳታ ማስተባበሪያ እና ማቋቋሚያ ኮሚሽን የተሰኘውን ተቋም ቢመሰረትም በጊዜው የነበረው መንግስት ለዚህ ተቋም ህጋዊ መብትና የስራ ኃላፊነት ተሰጥቶ በአዋጅ የተቋቋመው ግን በአዋጅ ቁጥር 173/1972 ነበር፡፡
5. የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት የሚባለው መዋቅር ከ1966 ዓ.ም ድርቅ በኋላ የእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን በመባል የተቋቋመ ሲሆን፣ በወቅቱ ኮሚሽኑን ለማቋቋም ምክንያት የሆነው በአገራችን ሰሜናዊ ክፍል የድርቅ አደጋ በመከሰቱ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ መልኩን

እየቀያየረ በመምጣት የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን፣ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ እንዲሁም ከምግብ ዋስትና ቢሮ ጋር በማዋሃድ የአደጋ መከላከል ዝግጁነትና የምግብ ዋስትና ዘርፍ ሆኖ በግብርና ሚኒስቴር ስር ተዋቅሮ በሚኒስቴር ዴኤታ የሚመራ ተቋም ሆኖ ነበር፤ ከዚያ በኋላ ኮሚሽኑን ለማቋቋም በወጣው ደንብ ቁጥር 363/2008 መሰረት ብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን በሚል ተቋቁሟል፡፡

6. ብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ከዚህ በፊት በዋናነት ድርቅ ተኮርና አደጋ ከተከሰተ በኋላ የአስቸኳይ ጊዜ የእለት እርዳታ በማቅረብ ህይወት ማዳን ላይ ያተኩር ከነበረበት የአደጋ ስራ አመራር ወደ ተሟላ የአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር አሰራር ተሸጋግሯል፡፡ ከቀድሞ በተለየ መልኩ የተቀናጀ በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተና ያልተማከለ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በየደረጃው ከአደጋ በፊት፣በአደጋ ጊዜና ከአደጋ በኋላ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎችን በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ እንዲወሰዱ ያደርጋል፡፡ በዚህም በአሁኑ ወቅት የአደጋ ክስተት ስጋትን እና በአደጋ ምክንያት ሊደርስ የሚችል ጉዳትን ለመቀነስ ትኩረት ሰጥቶ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡
7. የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ስርዓት በአደጋ ስራ አመራር ስር ያሉትን ሁሉንም ዘርፎች ማለትም መከላከል፣ ማቅለል፣ ዝግጁነት፣ ምላሽ መስጠት፣ ማገገምና መልሶ ማቋቋም የሚሉትን ስድስት የስራ ክፍሎችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህን የስራ ዘርፎች ይዞ ኮሚሽኑ ቀደም ብሎ ከነበረው አሰራር በተለየ ተግባሩን እንዲወጣ የተቋቋመ ተቋም ነው፡፡
8. ቀደም ሲል የነበረው አሰራር ገጠርና ድርቅ ተኮር ነበር፡፡ በአጠቃላይ ገጠር ላይ ርብርብ የሚያደርግና ብሎም ከአደጋዎቹ መካከል ድርቅን መሰረት ያደረገ ነበር፡፡አሁን ከአገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት እንዲሁም ከአየር ንብረት ለውጥ አንፃር የአደጋዎች በየአይነት መከሰት የነበሩትን ሁኔታዎች ለማጤን አስገድዷል፡፡
9. ከአየር ንብረት ለውጡ ጋር ተያይዞ አደጋው ከጊዜ ወደጊዜ እየጠነከረ በመምጣቱ ምክንያት ኮሚሽኑ በድርቅ ላይ ብቻ ሳይሆን ሌሎች የአደጋ ክስተቶች የሚመለከቱት ሲሆን ለዚህም የሚመለከታቸው አካላትን ሁሉ በማሳተፍና በህግ ማዕቀፍ በመደገፍ በተሟላ መልኩ ስራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ ስርዓት በመዘርጋት በአገራችን ቀደም ብሎ ከነበረው አደጋው ከደረሰ በኋላ ምላሽ ከመስጠት አሰራር ባሻገር አደጋዎቹ ከመድረሳቸው በፊት የመከላከል ስራ ለመስራት ተቋቁሞ እየሰራ ያለ መ/ቤት ነው፡፡

## የኮሚሽኑ ራዕይ

10. "በ2015 ዓ.ም የአደጋ መንስኤዎችና ተያያዥ አደጋዎችን ተፅዕኖ የመቋቋም አቅም በሀገር፣ በአካባቢ፣ በህብረተሰብ፣ በቤተሰብና በግለሰብ ደረጃ ተገንብቶና በአደጋ ምክንያት የሚደርስ ጉዳት ቀንሶ ማየት፡፡

## የኮሚሽኑ ተልዕኮ

11. ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት የሚያጠናክር፣ ህብረተሰቡን ማዕከል ያደረገ፣ የተቀናጀና የተናበበ፣ በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተና ያልተማከለ ዘርፈ-ብዙ የአደጋ መንስኤዎችና ዘርፈ-ብዙ ሴክተሮች አቅጣጫ ላይ የሚያተኩርና በቅድመ-አደጋ፣ በአደጋና በድህረ-አደጋ ጊዜ መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ትኩረት የሚሰጥ ውጤታማ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ስርዓት በመዘርጋት የአደጋ መንስኤዎች ተፅዕኖዎችንና ተያያዥ አደጋዎችን የመቋቋም አቅም ለመገንባትና በአደጋ ምክንያት የሚደርስ ጉዳትን ለመቀነስ የሚያስችል ማዕቀፍ መፍጠር፡፡

## የኮሚሽኑ ዓላማ

12. በብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 363/2008 መሰረት ለኮሚሽኑ የተሰጡ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-
    - ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ በተሟላ መልኩ እንዲተገበርና ዓላማዎቹ እንዲሳኩ ለማስቻል አግባብ ያላቸውን ተግባራት ማከናወን፤ እና
    - በመሪ ሴክተር መ/ቤቶች የሚከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ የማስተባበር፣ ክትትል ማድረግና ተገቢውን ድጋፍ መስጠት የሚሉት ናቸው፡፡

## የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር

13. ኮሚሽኑ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 363/2008 ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መካከል፡-
    - የአደጋ ስጋት ስራ አመራር በመንግስት የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የልማት ዕቅድና ፕሮግራሞች፣ በግል መ/ቤቶች ዕቅዶች እንዲሁም በስርዓተ-ትምህርት መካተቱን ያረጋግጣል፤ ከዚህ ጋር በተያያዘም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ያደርጋል፣
    - በአደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነድ ላይ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች ተብለው የተሰየሙ የፌደራል መንግስት የአስፈፃሚ አካላት በዕቅዳቸው ውስጥ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ማካተታቸውን ያረጋግጣል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤
    - በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ የትግበራ ዕቅዶችን አሰባስቦ ያደራጃል፣ አፈፃፀሙን በየጊዜው ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ለአደጋ ስጋት

ስራ አመራር ምክር ቤት ስለ ስራ አፈፃፀሙ ቢያንስ በበጀት አመቱ ሁለት ጊዜ ሪፖርት ያቀርባል፤

- የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ የአደጋ ምላሽ እና የአደጋ ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይገመግማል፤
- ማንኛውንም መሪ ሴክተር መስሪያ ቤትን የማይመለከት ወይም ከመሪ ሴክተር መ/ቤት አቅም በላይ የሆነ ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥም የምላሽ ስራውን ይሰራል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፤
- ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ ክምችት ይይዛል፣ ያስተዳድራል፤
- አስቸኳይ ጊዜ የዕለት ምግብ ዕርዳታ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ስትራቴጂክ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችትን ከሚያስተዳድር የሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት የዕርዳታ እህል በመውሰድ የዕርዳታ እህል ያሰራጫል፤
- ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በአገር አቀፍ ደረጃ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ዝግጅትና ክለሳ ስራን ይመራል፣ ያስተባብራል፤
- የአደጋ ስጋት ፕሮፋይሉን መሰረት በማድረግ የተሟላ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት በየደረጃው ይዘረጋል፣ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ የተዘረጋው ስርዓት ተደራሽ፣ ለአደጋ ምላሽ ሰጪና ዝግጁ እንዲሁም ለድንገተኛ ደራሽ አደጋዎች የታቀዱ ዕቅዶች ተግባራዊ መሆን መቻላቸውን ለማረጋገጥ በየደረጃው በተከታታይ ወይም በዕቅዱ ላይ ተመስርቶ የናሙና ልምምዶች እንዲከናወኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የማስተካከያ እርምጃዎችንም ይወስዳል፤
- በቅድመ-አደጋ፣ በአደጋና በድህረ-አደጋ ወቅት የአደጋ ስጋት ትንበያን ጨምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ ጥናቶችንና ግምገማዎችን ይመራል፣ ያስተባብራል፤
- የፌደራል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከልን ስራ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ ይመራል፣ ያስተዳድራል፤ እንዳስፈላጊነቱም ተመሳሳይ ማዕከል በፌደራል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ መስተዳድሮች በሚገኙ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች እንዲመሰረት ድጋፍ ያደርጋል፤
- የመረጃና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤ በብሄራዊ ደረጃ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣ እንዳስፈላጊነቱ የክልል መስተዳድሮች ተመሳሳይ የመረጃ ማዕከል እንዲያቋቁሙ ድጋፍ ያደርጋል፤
- አደጋ በይፋ መገለፁን ተከትሎ የአደጋ ስራ አመራር ም/ቤት ሲወስን ከአገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ሀብት ያሰባስባል፤

- የተገኘውን ሀብት በራሱና በሌሎች የሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል መስተዳድሮች በሚገኙ መሪ የሴክተር መ/ቤቶች አማካኝነት ለአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ  ስራ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ስርዓት በፍላጎት በተደራጁና በውጤት ላይ የተመሰረተ የአደጋ ስጋት ስራዎችን በሚሰሩና በበጎ ፈቃደኞች የሚታገዝበትን አሰራር ይዘረጋል፤ በተሟላ መልኩ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
- አግባብነት ባላቸው የአገሪቱ ህጎች መሰረት ለብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ትግበራ አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር አግባብነት ካላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና የመንግስትና የግል መ/ቤቶች ጋር የስራ ግንኙነት ይፈጥራል፤ ይተባበራል፤ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## የኮሚሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

14. የብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሆኖ በአንድ ኮሚሽነር እና በአንድ ምክትል ኮሚሽነር የሚመራ ሲሆን፣ በኮሚሽነሩ ስር አንድ ጽ/ቤትና አምስት/5/ ዳይሬክቶሬቶች ያሉ ሲሆን፣ ከእነዚህ በተጨማሪ በምክትል ኮሚሽነሩ ስር አስር(10) ዳይሬክቶሬቶች እንዲኖሩ ተደርጎ ተዋቅሯል፡፡ የኮሚሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር የሚያሳይ መረጃ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

### የሰው ሀይል

15. ለኮሚሽኑ በጠቅላላው 710 የሰው ሀይል የተፈቀደ ሲሆን፣ ኮሚሽነሩን ጨምሮ በኮሚሽኑ በጠቅላላ በስራ ላይ ያለው የሰው ሀይል እስከ መጋቢት 26/2010 ዓ.ም 405 ቋሚ እና 134 የኮንትራት ሰራተኞች በድምሩ 539 ሰራተኞች ያሉ ሲሆን፣ የቋሚ ሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ በኤም.ኤስ.ሲ/ኤም.ኤ ደረጃ ያሉ 27 (7%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 65 (16.5%)፣ ኮሌጅ ዲፕሎማ 67 (16.5%)፣ ከሌቭል I- IV 23(6%) እንዲሁም የቀለም ትምህርት ያላቸው ሰራተኞች 217 (54%) ይሸፍናሉ፡፡ ከአጠቃላይ በስራ ላይ ካሉት ቋሚ ሰራተኞች ውስጥ 236 (58.2%) ወንዶች ሲሆኑ፣ 169 (41.8%) ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ ከ136 የኮንትራት ሰራተኞች ውስጥ ደግሞ 82 (61.2%) ወንዶች እና 52 (39%) ሴቶች መሆናቸውን ከሰው ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ከተሰበሰበ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የኮሚሽኑ የፋይናንስ ምንጭ

16. የብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ሥራውን የሚያከናውነው በመንግስት በሚመደብለት በጀት ሲሆን፣ በ2008፣ በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመታት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ማስፈጸሚያ ከመንግስት የተመደበ መደበኛ በጀት እና ከለጋሽ ድርጅቶች የተገኘ የገንዘብ መጠን እና አጠቃቀም መግለጫ ከታች በሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

| የበጀት ዓመት | የበጀት ዓይነት | የተመደበ በጀት (በብር) | ጥቅም ላይ የዋለ በጀት (በብር) | የበጀት አጠቃቀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 2008 | መደበኛ | 8,878,965,053.34 | 6,557,248,459.07 | 73.8 |
| | ከለጋሽ ድርጅቶች | - | - | - |
| 2009 | መደበኛ | 8,931,415,064.62 | 8,041,221,174.94 | 90.03 |
| | ከለጋሽ ድርጅቶች | 18,507,403.00 | 13,460,836.20 | 72.7 |
| 2010 | መደበኛ | 6,593,588,946.18 | 7,097,931,726.18 | 107.6 |
| | ከለጋሽ ድርጅቶች | 43,457,725.00 | 24,045,147.00 | 55.3 |
| ድምር | | 24,45,934,192.14 | 21,733,907,343.39 | 88.833 |

## የኦዲቱ ዓላማ

17. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ኮሚሽኑ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎችን ለማቀላጠፍና በአግባቡ ምላሽ ለመስጠት የሚረዳ ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ለመገምገም ሲሆን፣ ውጤቱ የሚጠበቀውን ያህል ሆኖ ካልተገኘም የአሰራር ግድፈቶችን ለይቶ በማውጣት ግድፈቶቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

18. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም የስራ አፈፃፀም ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች

19. ከላይ በተገለፀው የኦዲት አካባቢ ሥር ሁለት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተመርጠዋል፡፡ እነርሱም፡-
    1. የአደጋ ምላሽ ፕሮግራሞችን ለማስተባበር፣ ክትትልና ግምገማ ለማድረግ የሚያስችል ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤

2. የአደጋ ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞችን ለማስተባበር፣ ክትትልና ግምገማ ለማድረግ የሚያስችል ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤የሚሉት ናቸው፡፡

20. እነዚህንም የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 42 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (evaluative critera) የተዘጋጁ ሲሆን፣ በተዘጋጁት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች ላይም የኮሚሽኑ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ቀርቦላቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

21. የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት በብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 363/2008 እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ የአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ናቸው፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

22. ኦዲቱ የተከናወነው ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ነው፡፡

23. ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2008 በጀት ዓመት እስከ 2010 በጀት አመት ድረስ ባለው ጊዜ በብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም የስራ ዙሪያ የተሰራውን ሥራ ነው፡፡

24. ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ሲሆን፤ በኮሚሽኑ ስር ከሚገኙ ከሦስቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ውስጥ በናሙና በተመረጡ በሁለቱ (በአዳማ እና በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች) እንዲሁም በናሙና በተመረጡ ክልሎች (በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአደጋ ስጋትና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት፣ በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምግብ ዋስትናና አደጋ መከላከል ጽ/ቤት እና በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ቢሮ እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ማስተባበሪያ ጽ/ቤትና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በጌዲኦ ዞን የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት፣) በአጠቃላይ በስድስት (6) የክልል ተቋማትና በሁለት(2) ማዕከላዊ መጋዘኖች የተለያዩ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን በመከለስና በመተንተን እና ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ለባለድርሻ አካላት ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ በአካል ተገኝቶ በማየት የተለያዩ የኦዲት ማስረጃዎች ሰብስቧል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ግኝቶች

## ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂን ስራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ህጎች፣መመሪያዎችና ማዕቀፎችን ያዘጋጀ መሆኑን በተመለከተ፡-

25.ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂን ስራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ህጎች፣ መመሪያዎችና ማዕቀፎችን ሊያዘጋጅ እና የአፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት ሊዘረጋና ተግበራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

26.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ መሰረት ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂን ስራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ህጎች፣መመሪያዎችና ማዕቀፎችን እንዳላዘጋጀ እና የአፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት እንዳልዘረጋና ተግበራዊ እንዳላደረገ ለማወቅ ተችሏል፡፡

27.የኦዲት ቡድኑ ጉዳዮን አስመልክቶ ለኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራርን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ፖሊሲውን ማስፈጸሚያ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ስትራቴጂክ ፕሮግራምና ኢንቨስትመንት ፍሬም ወርክ ተግባራት ተለይተው፣ የሃብት ፍላጎት ተዘጋጅቶ፣ በሃገሪቱ ያሉ አሰራሮችንና የልማት ፕሮግራሞችን የዳሰሳ-strategic map ተዘጋጅቶ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በውይይት ዳብሮ ወደ ተግባር ለመግባት በእንቅስቃሴ ላይ ቢሆንም ሙሉ ለሙሉ ለመተግበር የበጀት ፍላጎቱ ከፍተኛ በመሆኑና በሃገራችን ያለው የአደጋ ስፋትና መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ የሰው ህይወት ማዳን ላይ ትኩረት በመደረጉ ፍሬም ወርኩን በተፈለገው ደረጃ ለማካሄድ ያልተቻለ መሆኑን የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

28.ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ይህ ስራ የሚወሰነው የአደጋ ስጋት ሥራ-አመራር በሴክተሮች ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ ፕሮግራም፣ ውስጥ እንዲሰርፅ (mainstream) ከማድረግ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ከማስረፅ በኋላ የሚታይ ጉዳይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

29. ይሁን እንጂ የአደጋ ስጋት ፖሊሲና ስትራቴጂን ተፈፃሚ ለማድረግ አስፈላጊ ህጎች፣ መመሪያዎችና ማዕቀፎችን በማዘጋጀት እና የአፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘረጋት

ተግባራዊ የማድረግ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊነት መሆኑ በግልፅ እየታወቀ እነዚህ ጉዳዮች ባልተተገበሩበት ሁኔታ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂን በሴክተር መ/ቤቶች ከማስረፅ ጋር ብቻ የሚያያዝ ተደርጎ መገለፁ በኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች የተሰጠውን ምላሽ መሉ በሙሉ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

30.በመሆኑም ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂን ስራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ህጎች፣ መመሪያዎችና ማዕቀፎችን አለማዘጋጀቱ እና የአፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት አለመዘርጋቱ የኮሚሽኑን ፖሊሲና ስትራቴጂ ስራ ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዳይሆን እንዲሁም ስራዎች ያለ ህግና መመሪያ እንዲሰሩና ለብልሹ አሰራር በር እንዲከፈት ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ የአደጋ ምላሽ እና የአደጋ ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞችን በተመለከተ፡-

31.ኮሚሽኑ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 363/2008 ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መካከል የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ የአደጋ ምላሽ እና የአደጋ ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞችን ሊያስተባብር፣ ሊከታተል፣ ሊገመግም፤እንዲሁም ማንኛውንም መሪ ሴክተር መስሪያ ቤትን የማይመለከት ወይም ከመሪ ሴክተር መ/ቤት አቅም በላይ የሆነ ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥም የምላሽ ስራውን ሊሰራ፣ ሊመራ እና ሊያስተባብር ይገባል፡፡

32.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ከኮሚሽኑ በናሙና ተመርጠው በታዩ የኦሮሚያ፣ የደቡብ ብ/ብ/ህ፣ የሐረሪ፣ የሶማሌ የክልሎች እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርና የጌዲኦ ዞን አደጋ ስጋት ቢሮዎች የስራ ኃላፊወች ጋር በተደረጉ ቃለ-መጠይቆች እንዲሁም በተከለሱ ማስረጃዎች መሰረት ኮሚሽኑ በሀገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች በተከሰቱ እና ከክልሎች እና ከመሪ ሴክተር መ/ቤቶች አቅም በላይ የሆኑ ድንገተኛ አደጋዎች ሲያጋጥሙ የአደጋ ምላሽና የአደጋ ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞችን በሚፈለገው ደረጃና ፍጥነት ያላስተባበረ፤ ያልተከታተለ እና ያልገመገመ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

33.ከዚህ በተጨማሪ ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው መሪ ሴክተር መ/ቤቶች ጋር የጋራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ተግባራዊ አለማድረጉን ከኮሚሽኑ የ2010 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ አመት የፕሮግራም በጀት ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ተገልፀዋል፡፡ በክልሎች የነበረው አፈፃፀም እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

- ከሶማሌ ክልል ተፈናቅለው በድሬዳዋ የመጠለያ ጣቢያ የሚኙ 4,247 ያህል ተፈናቃይ ተረጂዎች የሚያስፈልጋቸው እርዳታ እና እየቀረበ ያለው ድጋፍ ተመጣጣኝ ካለመሆኑም

በተጨማሪ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ስር ተጠልለው የሚገኙ ተፈናቃዮች የዕርዳታ አቅርቦት ፍላጎት ከሚቀርበው ዕርዳታ አንፃር ሲታይ እየጨመረ መምጣቱን የኦዲት ቡድኑ ባደረገው የመስክ ምልከታ ለተፈናቃዮች የሚቀርበው የዕርዳታ ዓይነት ውስንና አንድ ዓይነት (ሩዝ) ብቻ ከመሆኑ በተጨማሪም ለህፃናት አልሚ ምግብ እየቀረበ እንዳልሆነ ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን ኮሚሽኑ ለተፈናቃዮች አስፈላጊ ምላሾችን እያደረገ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም፡፡

- በሀረሪ ክልል በክልሉ ተጠልለው ለሚገኙ 667 አባወራ ተፈናቃዮች የሚደረገው ድጋፍ በሚፈለገው ልክና አይነት እንዳልሆነና በስታንዳርዱ መሰረት እየተሰራ አለመሆኑን የክልሉ የአደጋ ስጋት ቢሮ የገለፁ ሲሆን በዚህ ዙሪያ ክልሉ ለተፈናቃዮቹ ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልጉ የቤት ቁሳቁስ ድጋፍ በዝርዝር 23 ዓይነት ቁሳቁሶች እንዲቀርቡለት በቀን 14/10/2010 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ለኮሚሽኑ ቢያሳውቅም ለአደጋ ምላሽ መሰረታዊ ናቸው የተባሉ የቁሳቁስ አይነቶች ያልተላኩ መሆኑንና የተላኩት ከተጠየቁት ውስጥ በቁጥር አራት(4) ዓይነት ዕቃዎች ብቻ መሆናቸውን ማለትም በተለምዶ የሚቀረቡት (ሰሃን ትንሹ፣ ጆክ፣ የውሃ ኩባያና ብረት ድስት መካከለኛ) ቁሳቁሶች ብቻ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለተፈናቃዮች የሚከናወነው የአደጋ ምላሽ ፕሮግራም በዖታ የተለየ መፀዳጃ ቤትና መጠለያ አለመኖሩን በኮሚሽኑ በተጠና ጥናት የተረጋገጠ ቢሆንም ኮሚሽኑ ጥናቱን መሰረት አድርጎ በመከታተልና በመገምገም የመፍትሄ እርምጃ ስለመውሰዱ የሚያመላክት የሰነድ ማስረጃ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡
- በደቡብ ክልል በጌዲኦ ዞን ተጠልለው ለሚገኙ ከ77ሺህ በላይ ተፈናቃዮች በኮሚሽኑ የሚቀርበው ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ድጋፍ በቂ አለመሆኑንና በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚዘገይ ታውቋል፡፡ በተለይ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በዋናነት የቤተሰብ አባላት ቁጥር በርካታ በመሆኑ ሳቢያ የብርድልብስ እጥረት መኖሩና ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ የቀጠለ ችግር መሆኑን የክልሉና የዞኑ የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- በተመሳሳይ በኦሮሚያ ክልል በቦረና፣ በባሌ እና በምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች ከነሀሴ 2009 ዓ.ም ጀምሮ በተከሰቱ ግጭቶች 431ሺህ 859 ተፈናቃዮች በተለያዩ መጠለያ ጣቢያዎች ተጠልለው ያሉ ሲሆን በ37 የውሃ ተቋማት ላይ በከፊልና ሙሉ በሙሉ ጉዳት በመድረሱ ለተፈናቃይ ወገኖች የውሃ አቅርቦት፣ የውሃ ማጣሪያና ማከሚያ ኬሚካሎች በበቂ ሁኔታ አለመቅረባቸውን በ2010 ዓ.ም በኮሚሽኑ በተደረገ የመስክ ጥናት ሪፖርት ላይ ቢገለፅም ኮሚሽኑ በጥናቱ ውጤት መሰረት የሰራና የመፍትሄ እርምጃ የወሰደ ስለመሆኑ የሚያመላክት የሰነድ ማስረጃ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

- በኦሮሚያ ክልል የአደጋ ምላሽ ስራው እስካሁን በማዕከል ማለትም በፌደራል ደረጃ የተያዘ በመሆኑ በተለይም ያልተጠበቁና ቅፅበታዊ አደጋዎች በሚከሰቱበት ጊዜ ሙሉ ፓኬጅ (በስታንዳርዱ መሰረት) ለተረጂዎች በወቅቱ ለማድረስ ችግሮች እንዳሉና የብሔራዊ አደጋ ስራ አመራር ኮሚሽን የአደጋ ምላሽ ፕሮግራሞችን ለተረጂዎች በወቅቱ ለማድረስ ችግሮች እንዳሉበት እንዲሁም የአደጋ ምላሽ ፕሮግራሞችን እስከ ወረዳ ድረስ ባሉ መዋቅሮች ክልሉ በራሱ የመከታተል ስራ እየሰራ ቢሆንም የአደጋ ክስተት ስፋቱ ክልሉ ካለው አቅም ጋር የማይመጣጠን መሆኑንና ኮሚሽኑ የአደጋ ተጎጂዎችን የመለየት (assessment) ስራዎችን ከመስራት ውጪ የአደጋ ምላሽ ፕሮግራዎችን እንዳላስተባበረና እንዳልተከታተለ የክልሉ የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

34. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ኮሚሽኑ አገራዊ የአደጋ ክስተቶችን የማስተዳደር ክፍተቶች ያሉበት መሆኑን አምነው ክፍተቶቹ ባብዛኛው የሚፈጠሩት በሀገሪቱ ባለው የፀጥታ ችግር ምክንያት ሲሆን ይህም የሚጓጓዙ ቁሳቁሶች በወቅቱ እንዳይደርሱ በማድረጉ ለረጅም ጊዜ ቁሳቁስ የጫኑ ተሽከርካሪዎች በመንገድ ላይ የሚቆዩበት ሁኔታ እንደነበር ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኮሚሽኑ የነበረው ክምችት ለገበያ ማረጋጊያ የዋለ በመሆኑና ከተፈናቃዮች ጋር ተቀላቅለው የሚገቡ የህብረተሰብ ክፍሎች በመኖራቸው ምክንያት በተሟላና በስታንዳርዱ መሰረት እርዳት ማቅረብ አለመቻላቸውንና በክምችት የተያዘው ሁሉንም የሚያዳርስ ባለመሆኑና በቂ ስላልሆነ ፓኬጁን አሟልቶ ለማቅረብ አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ለቅፅበታዊ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት የክልሎችን አቅም የማጎልበት ስራ ቢሰራም በኮሚሽኑ ዳይሬክቶሬቶች መካከል ግልፅ የሆነ አሰራርና ቅንጅት ባለመኖሩ ችግሩን በተቀመጠው እስታንዳርድ እና በሚፈለገው መልኩ እንዳይፈታ እንዳደረገው የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች አስረድተዋል፡፡

35. የኮሚሽኑ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጅ የብሔራዊ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚቴ በሚሰጠው አመራር፣ በየሴክተሩ በተቋቋሙት የሴክተር ግብረ ሃይሎች አማካኝነት ቅንጅታዊ አሠራር፣ የክትትልና ግምገማ ሥራ እየተሠራ ያለ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

36. ይህም በመሆኑ በየደረጃው የሚከናወኑ የአደጋ ምላሽ ፕሮግራሞች የተቀናጀ፣ በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተና ያልተማከለ የአሰራር ስርዓትን በመዘርጋት በየደረጃው መወሰድ የሚገባቸውን ተገቢ እርምጃዎች በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ እንዲወሰዱ ለማድረግ አያስችልም፡፡

**ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣**

**ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ**

**ቁሳቁስ ክምችት የሚይዝ መሆኑን በተመለከተ፡-**

37.ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ ክምችት ሊይዝ፣ ሊያስተዳድር እና ለምላሽ ስራ ሊያውል ይገባል፡፡

38.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ዝርዝራቸው በአባሪ በተያያዘ የክልል አደጋ ስጋት ቢሮዎች እና ከተማ አስተዳደር እንዲሁም ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

- ኮሚሽኑ በሚያስተዳድራቸው በሶስቱ ማዕከላዊ መጋዘኖች (አዳማ፤ድሬደዋ እና ኮምቦልቻ) በቂ የሆነ ክምችት መጠን አለመኖሩን፤በሌላ በኩል ደግሞ የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በ2010 ዓ.ም በሀገሪቱ የስንዴ እጥረት በማጋጠሙ ገበያውን ለማረጋጋት በሚል በብሔራዊ አደጋ ስጋት ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት በግዥ እንዲተካ በሚል ከአደጋ ምላሽ ስራ ውጭ ስንዴ ከክምችት ወጥቶ ወደ ገበያ የገባበት አሰራር መኖሩን፤
- ኮሚሽኑ ለምላሽ ስራው የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ ክምችት መያዝ፣ ማስተዳደር እንዲሁም ለምላሽ ስራው ማዋል ቢኖሪበትም አላደረገም፤
- በክልሎች በሚለየው ተረጅ ቁጥር መሰረት እርዳታ እንዲላክላቸው ክልሎች ጥያቄ የሚያቀርቡ ሲሆን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ድልድል የሚደርግ መሆኑን፣ ነገር ግን እንደ አስፈላጊነቱ ከምግብ ዋስትና ፕሮግራም ጋር በማቀናጀት በገንዘብ ድጋፍ የሚደረግበት አሰራር በመኖሩ የገንዘብ ድጋፉ በወቅቱ በማይገኝበት ጊዜ ተረጂውን ለማዳረስ ውሱንነት የሚታይ መሆኑ እና ገንዘቡም የወቅቱን የግዥ/ገበያ ሁኔታ ያላገናዘበ በመሆኑ ቅሬታዎች መኖራቸውን የኮሚሽኑ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ባለሙያዎች ገልፀዋል፡፡
- እንዲሁም ኮሚሽኑ በጥሬ ገንዘብ ለተረጂዎች እርዳታ ማቅረብ እንዳለበት የሚገልጽ አሰራር/መመሪያ ስለመኖሩ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ ያልቀረበ ከመሆኑ በተጨማሪ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ የምግብና ቁሳቁስ አቅርቦት በቂና ወቅታዊ እንዳልሆነ በመስክ በመገኘት ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፣

39. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-ለገበያ ማረጋጋት የዋለበት ሁኔታ ከመንግስት በመጣ አቅጣጫ አሰራር ሊሆን እንደሚችል

ግምታቸውን ያስቀመጡ ሲሆን፤ ክምችት ላይ የቆዩት እንዳይበላሹ የሚሰራበት ሁኔታ ያለ መሆኑን ገልፀው፡ በጥሬ ገንዘብ ለማቅረብ በቅድመ ልየታ (hot spot classification) መሰረት የሚሰጥ መሆኑና ለዚህ አሰራር የሚሆን መመሪያ የሌለ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ነገር ግን በ PSNP(Productive safety Net program) መመሪያ ልኬት መሠረት ተሰልቶ የሚሰጥ መሆኑንና የገንዘብ አቅርቦቱ ቅሸባን ይከላከላል ተብሎ ስለታመነበት እና ወጪንና ጊዜን የሚቆጥብ በመሆኑን አስረድተዋል፤ ነገር ግን ሁኔታዎችን አጥንቶ ምላሽ መሰጠት የሚኖርበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

እንዲሁም ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ፡-

- የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ የመያዝ አቅሙ 673 ሺህ ሜትሪክ ቶን ብቻ መሆኑና የክምችቱ ዓላማም ለገበያ ማረጋጊያ፣ ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ምላሽ የሚሰጥ መሆኑ፤
- በጥሬ ገንዘብ ዕርዳታ የሚቀርበው በአዲሱ “Integrated Cash and Food Plan” መሠረት የሚላከው ገንዘብ በ15 ኪሎ ግራም ስንዴ መግዣ ዋጋ ተሰልቶ እንደሆነ፣ እና ይህም ከልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ጋር በተናበበ አግባብ የሚከናወን መሆኑንና ገንዘብ የሚላከው በአካባቢ ገበያ ላይ በቂ የእህል አቅርቦት ላላቸው አካባቢዎች እንደሆነ፣ አስረድተዋል፡፡
- የአደጋ ጊዜ ፈንድ በአዋጅ የተቋቋመ መሆኑንና አሠራሩም አዋጁ ላይ በተቀመጠው መሠረት መሆኑን አስረድተው፤ ይሁንና ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ የፈንዱ እንቅስቃሴ ከመያድ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ተሸከርካሪ ሽያጭ ከሚገኘው ገቢ ሀያ አምስት በመቶ (25%) እና ከመንግሥት ግምጃ ቤት ሰነድ ግዥ ከሚገኘው ውጭ ሌላ ገቢ የሌለው በመሆኑ በቀጣይነት ጥናት ላይ በመመሥረት አማራጭ ገቢ ለመፈለግ እየተሠራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

40. የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ ደንብ ላይ እንደተቀመጠው ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ ክምችት ሊይዝ፣ ሊያስተዳድር እና ለምላሽ ስራ ሊያውል እንደሚገባ የተገለፀ በመሆኑ እንዲሁም በጥሬ ገንዘብ የሚቀርበው ዕርዳታ በተመለከተ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ በመመሪያ የተደገፈ አሰራር ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ እና በተጨማሪም በኮሚሽኑ መጋዘኖች ለረጅም ጊዜ ክምችት ላይ የቆዩ ምግብ ነክ ቁሳቁሶች ለገበያ መዋል እንዳለባቸው የተወሰነበት ውሳኔ ወይም የአሰራር ስርዓት በሌለበት ሁኔታ የተሰጠውን ምላሽ መሉ በሙሉ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

41.በመሆኑም የአደጋ ጊዜ ፈንድ መመሪያ እና የክምችትና ስርጭት መመሪያ ባለመኖሩ ለምላሽ ስራው የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ ክምችት ለመያዝ፣ ለማስተዳደር እንዲሁም ለምላሽ ስራው ለማዋል በክልሎች በሚለየው ተረጅ ቁጥር መሰረት እርዳታ እንዲላክላቸው ክልሎች ጥያቄ በሚያቀርቡበት ወቅት በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ድልድል ለማድረግ እና ተረጂውን ለማዳረስ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## ኮሚሽኑ የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ምግብ ዕርዳታ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ከስትራቴጂክ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት በመውሰድ የሚያሰራጭ መሆኑን በተመለከተ፡-

42.ኮሚሽኑ የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ምግብ ዕርዳታ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ስትራቴጂክ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችትን ከሚያስተዳድር የሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት የዕርዳታ እህል በመውሰድ የዕርዳታ እህል በወቅቱ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

43.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ከተከለሱ ማስረጃዎች ኮሚሽኑ የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችትን በአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ እንደሌለው የኮሚሽኑ የ2010 ዓ.ም የውጤት ተኮር ዕቅድ ሰነድ በተከለሰበት ወቅት የታወቀ ሲሆን፣ እጥረት ሲያጋጥም በቂ ክምችት ካላቸው ከሌሎች እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ጋር በመዋዋስ እንደሚሰሩ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ወቅት በቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ኮሚሽኑ ከእስትራቴጅክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንስ ከግንቦት 2007 እስከ ጥቅምት 2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ አራት መቶ ሀያ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባት ነጥብ ስልሳ ሶስት ሜትሪክ ቶን (428,907.63 ሜ/ቶ) እህል በመውሰድ ለዕለት ደራሽ እርዳታ ማዋሉን ከሚገልፅ ማስረጃ የታወቀ ቢሆንም አሰራሩን የሚያሳይ የህግ ማዕቀፍ ስለመኖሩ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

44.ከዚህ በተጨማሪኮሚሽኑለኢትዮጵያንግድሥራዎችኮርፖሬሽን ለገቢያ ማረጋጊያነት እንዲውል በሚል ለምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስፈፀሚያ እና ለተጎጂዎች የምግብ እርዳታ ለማዋል በኮሚሽኑ መጋዘኖች ከተከማቸው ስንዴ ውስጥ ሰላሳ አምስት ሺህ ሜትሪክ ቶን (35,000 ሜ/ቶ) በብድር የሰጠ በመሆኑ የኮሚሽኑ ሎጂስቲክስ ዳይሬክቶሬት በብድር የሰጠው ስንዴ እንድመለስለትበ2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥርH16-910/763 ለኮርፖሬሽኑያሳወቀ ቢሆንም ኮሚሽኑ በምን አይነት የአሰራር መመሪያና ስልጣን እንደሰጠ የሚያመላክት የሰነድ ማስረጃ የኦዲት ቡድኑ አላገኘም፡፡ እንዲሁም በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ ደምብ ቁጥር 363/2008 በተቀመጠው

ስልጣንና ተግባር መሰረት ኮሚሽኑ በብድር የሚሰጥበት የአሰራር ያልተመላከተ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

45.ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት መልስ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚሰጠው ዋስትና የመጠባበቂያ ክምችቱ ቦርድ ሲፈቅድ የሚወጣና ኮሚሽኑና ኤጀንሲው በሚዋዋሉት ውል መሠረት ተመላሽ የሚደረግ ስለመሆኑ ቢገልፁም፣ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ይህ አሰራር የህግ ማዕቀፍ እና ኮሚሽኑ ከኤጀንሲው ጋር የተዋዋለበትን ውል የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡ ነገር ግን በመውጫ ስብሰባ ወቅት የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች የብድር መመሪያ መኖሩን እና ማቅረብ እንደምቻል ቢገልፁም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

46.ይሁን እንጂ የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችትን በአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ በሌለበት እና ኮሚሽኑ ከኤጀንሲው ጋር የተዋዋለበትን ውል የሚያሳይ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ምላሹን ለመቀበል ያዳግታል፡፡

47.በመሆኑም በኮሚሽኑ የእህል ክምችት እጥረት በሚያጋጥምበት ወቅት የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ምግብ ዕርዳታ እህል በወቅቱ ለማሰራጨትና የምግብ ክፍተቱን ለመሙላት እና ተጎጂዎችን ከከፋ ጉዳት ለመታደግ እንዲሁም በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተ አሰራር እንዳይኖር ያደርገዋል፡፡

## ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በአገር አቀፍ ደረጃ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ዝግጅትና ክለሳ ስራን በተመለከተ፡-

48.ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በአገር አቀፍ ደረጃ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ዝግጅትና ክለሳ ስራን ሊመራ እና ሊያስተባብር ይገባል፡፡

49.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው በአባሪ በተያያዙ የክልል አደጋ ስጋት ቢሮዎች እና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

- የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ በኮሚሽኑ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ባቀረበው ቃለመጠይቅ መሰረት ኮሚሽኑ ወቅታዊ የአደጋ ስጋት መረጃዎችን ለህብረተሰቡና ለአጋር ድርጅቶች አጠናቅሮ ለማቅረብ የ454 ወረዳዎች የወረዳ አደጋ ስጋት ተጋላጭነት ጥናት መረጃ በማሰባሰብ የ346ቱ (76.2%) ወረዳዎች ፕሮፋይል መጠናቀቁን እና የአደጋ ስጋት ፕሮፋይላቸው ከተጠናቀቀው ከ346 ወረዳዎች ውስጥ ደግሞ የ232ቱ (67%) ወረዳዎች የመጠባበቂያና የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዕቅድ መዘጋጀቱን ለማወቅ ተችሏል፤

- እንዲሁም ፕሮፋይላቸው ያለቀላቸው ወረዳዎች በዌብሳይት በመልቀቅ በመረጃ መረብ ለተጠቃሚው የማሰራጨት ስራ የተሰራ ቢሆንም  የወረዳ አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም መረጃ ማሰባሰብ ከተጀመረ ከ5 ዓመት በላይ በማስቆጠሩ የመረጃ ክለሳ ስራ ቢያስፈልግም በበጀት እጥረት ምክንያት መከለስ አለመቻሉን፤ ከዚህም በተጨማሪ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር በሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች ባለመካተቱና ባለመስረፁ ምክንያት መ/ቤቶችና ክልሎች በራሳቸው መንገድ እንዳይከልሱ ማድረጉን የኮሚሽኑ ሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

50.የኦዲት ቡድኑም በኦዲቱ ወቅት በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር፣ በደቡብ፣ በሶማሌ እና በኦሮሚያ ክልሎች የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ቢሮዎች በመገኘት የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ዝግጅትና ክለሳ እንዳልተሰራ አረጋግጧል፡፡

- በሀረሪ ክልል የአደጋ ፕሮፋይል ዝግጅት ቢሰራም ወደ ተግባር ለማዋል ተስማሚ የማድረግ ዕቅድ/adaptation plan/ ስለሚያስፈልግ እስካሁን አለመሰራቱንና የአደጋ ፕሮፋይል ጥናቱ የመተግበሪያ ጊዜም ማለፉን፣ ይኸውም በየአምስት አመቱ መከለስ ቢኖርበትም እንዳልተከለሰና በክልል ደረጃ አቅምና ባለሙያ ባለመኖሩ ሊሰራ እንዳልቻለ የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በደቡብ ክልል በአደጋ ጥናት ፕሮፋይል ጥናት መሰረት እየተሰራ እንዳልሆነ የክልሉ የአደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የከተማው የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል አለመሰራቱን የከተማ አስተዳደሩ የአደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲትቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በኦሮሚያ ክልል በአጠቃላይ ከ215 ወረዳዎች ውስጥ በ113 (52.56%) ወረዳዎች ብቻ የፕሮፋይል ጥናት የተሰራ መሆኑን እና የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ዝግጅት ክለሳው በየአምስት አመቱ ይደረጋል ቢባልም አለመከለሱን ይህም በመሆኑ የተረጂዎችን መረጃ ማጠናቀር እንዳልተቻለ የክልሉ የአደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

51.ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ለቀጣይ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ሥራ ወሳኝ በመሆኑ ቅድሚያ የሚሰጠው በድርቅና በጐርፍ ተደጋጋሚ ጉዳት በሚደርስባቸው ወረዳዎች መሆኑንና ሥራው የሚሰራው በመንግሥት በጀት ሳይሆን በአጋር አካላት የገንዘብ ድጋፍ በመሆኑ ገንዘብ በሚፈለገው መጠን ማግኘት ያልተቻለ መሆኑንና ክልሎች የራሳቸውን አማራጭ ከመፈለግ ይልቅ ሙሉ በሙሉ የፌዴራል መንግሥትን መጠበቅ እንደሚታይባቸው ገልፀዋል፡፡

52. የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ ደንብ ላይ እንደተቀመጠው ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በአገር አቀፍ ደረጃ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ዝግጅትና ክለሳ ስራን ሊመራ እና ሊያስተባብር እንደሚገባ የተገለፀ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ መሉ በሙሉ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

53.በመሆኑም ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በአገር አቀፍ ደረጃ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ዝግጅትና ክለሳ ስራን በሚፈለገው መጠን ባለመምራቱ እና ባለማስተባበሩ እንዲሁም የአደጋ ስጋት ስራ አመራር በሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች ባለመካተቱና ባለመስረፁ ምክንያት ወቅታዊ የሆነ አገር አቀፍ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል እና እሱንም መሰረት አድርጎ የሚዘጋጅ አገር አቀፍ የመጠባበቂያና የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዕቅድ እንዳይዘጋጅና የተጠናቀረና ወቅታዊ የአደጋ ስጋት መረጃዎች ለህብረተሰቡና ለአጋር ድርጅቶች እንዳይደርስ ያደርጋል፡፡

## ኮሚሽኑ የአደጋ ጥናት መረጃ ላይ ያተኮረ ምላሽ የሚሰጥ መሆኑን በተመለከተ፡-

54.ኮሚሽኑ የአደጋ ጥናት መረጃ ላይ ያተኮረ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡

55.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው በአባሪ በተያያዘ የክልል አደጋ ስጋት ቢሮዎች እና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ሁኔታወች ታይተዋል፡-

- በኦሮሚያ ክልል በተለያየ ግጭቶች ምክንያት ተፈናቃዮች በመጨመራቸው በዕለት ዕርዳታ እና በምግብ ነክ ባልሆኑ ድጋፎች ያልተካተቱ መሆኑና ለተፈናቃዮች የሚደረገው ድጋፍ ሙሉና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች ያላከተተ መሆኑን በኮሚሽኑ በመጋቢት 2010 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል በተደረገ የመስክ ጥናት የተገለፀ መሆኑ፣
- በሶማሌ ክልላዊ መንግስት አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ተጎጂዎች እንዳሉና ከፍተኛ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ፣ በየጊዜውም ቁጥራቸው እየጨመረ የሚገኝበት ሁኔታ በመኖሩ የሚደረገው ድጋፍ በቂ አለመሆኑን የክልሉ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በመረጃ ላይ ተመርኩዞ የአደጋ ምላሽ ለመስጠት የስርዓተ-ምግብ የቴክኒክ ቡድን በጤና ቢሮ ቢኖርም እየተሰራ አለመሆኑን፣ ይሁን እንጂ በቅድመ ማስጠንቀቂያ ባለሙያዎች አማካኝነት ስራው እየተከናወነ ቢገኝም ውጤታማ እንዳይሆን የሚያደርግ በመሆኑ የራሱ የሆነ አደረጃጀት እንዲኖር መደረግ እንዳለበት ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የስርአተ-ምግብ ጥናት አለመኖሩንና ክሊኒካል የሆኑ ስራዎች ወደ ሃኪም ቤት ለመጡት ብቻ እየተሰራ እንደሚገኝ እና ስራው ባለመሰራቱ በጥናት ያልተደገፈና ባህላዊ

የሆነ አሰራር እንዲከተሉ ማድረጉንና በተለይ አዋቂ ሰዎች ለልጆቻቸው ሲሉ ውሃ ጠጥተው ስለሚውሉ ለሞት እየተጋለጡ መሆኑን በተጨማሪም የሚደረጉ ውሳኔዎችንና የምላሽ ስራዎችን ሊያዛባ የሚችል መሆኑን የከተማ አስተዳደሩ የአደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

- በኦሮሚያ ክልል የአደጋ ስጋት ምላሽ በአደጋ ጥናት መረጃ ላይ ተመርኩዞ እየተሰራ እንዳልሆነ የክልሉ የአደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ከሌሎች ለመለየት እጅግ አስቸጋሪ ሥራ በመሆኑ እና የአደጋ ሥራ ዛሬ በተጠና ጥናት ላይ ብቻ የሚመሰረት ባለመሆኑ በቂ ክትትል የሚያስፈልገው እንደሆነና በኮሚሽኑ ለሚደረጉ ድጋፎች ሁሉ ስታንዳርዱ እንደገና መታየትና መጠናት የሚገባው መሆኑን የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባካሄደው ቃለ-መጠይቅ መሰረት ኮሚሽኑ የጋራ የሆነና ሁሉን አቀፍ ዘርፈ ብዙ አደጋ ላይ ያተኮረ ሀገር አቀፍ ፕላን (National Disaster Plan) ያላዘጋጀ መሆኑን ነገር ግን መዘጋጀት እንዳለበት የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

56.ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- በዓመት ሁለት ጊዜ (የበልግና የመኸር) ጥናት የሚደረግ መሆኑን፤ በዚህ መሠረትም ዓመታዊ ዕቅድ/Annual Disaster Response Plan) የሚዘጋጅ መሆኑን፤ይህም የተረጂ ቁጥር የሚያስፈልገውን ምግብና ምግብ - ነክ ያልሆነ አቅርቦት መጠንና የሚያስፈልገውን ገንዘብ እና የምላሽ ሥራው በማን እንደሚከናወን የሚያሳይ መሆኑን፤ በዚሁ መሠረትም በመንግሥት፣ በዓለም ምግብ ፕሮግራም እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚቀርብ መሆኑን፤
- በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን በዓመታዊ ዕቅድ የተላከ መሆኑንና አዳዲስ ተፈናቃዮች ግን ከክልል በሚቀርብ ጥያቄ እየተስተናገዱ መሆኑንና ዕቅዱ በበልግ ጥናት ወቅት የሚከለስና (mid Year plan) ተብሎ እንደሚወጣና ተጨማሪ ቁጥር ካለም በየጊዜው ምላሽ እየተሰጠበት የሚሄድ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

57. የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ጥናት ሙሉ በሙሉ ባልተሰራበትና ወቅታዊ ክለሳ ባልተደረገበት ሁኔታ እንዲሁም ወቅታዊና የተሻሻለ መረጃዎች ባልተቀናጀበት ሁኔታ ምላሹን መሉ በሙሉ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

58. በመሆኑም የአደጋ ጥናት መረጃ ላይ ያተኮረ ምላሽ ባለመሰጠቱ በተለያዩ ግጭቶች ምክንያት በዕለት ዕርዳታ እና በምግብ ነክ ባልሆኑ ድጋፎች እንዳይካተቱና ለተፈናቃዮች የሚደረገው ድጋፍ ሙሉና ሁሉንም ተጎጂ የህብረተሰብ ክፍሎች ያላከተተ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

### ኮሚሽኑ በቅድመ-አደጋ፣ በአደጋና በድህረ-አደጋ ወቅት የአደጋ ስጋት ትንበያን ጨምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ ጥናቶችንና ግምገማዎችን በተመለከተ፡-

59.ኮሚሽኑ በቅድመ-አደጋ፣በአደጋና በድህረ-አደጋ ወቅት የአደጋ ስጋት ትንበያን ጨምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ ጥናቶችንና ግምገማዎችን ሊመራ እና ሊያስተባብር ይገባል፡፡

60.ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

- ኮሚሽኑ የአደጋ ተጋላጭነት ጥናት እያከናወነ እንደሚገኝ በዚህም መነሻ የወረዳ የአደጋ መጠባበቂያ ዕቅድ መመሪያና የማቅለልና ተጣጥሞ የመኖር ዕቅድን በማዘጋጀት በየትኛውም ደረጃ አስፈላጊነት ያላቸውንና በመንግስት በሚሰጠው ምላሽ የተቀናጀ እንዲሆን የሚያግዙ የ454 ወረዳዎች የአደጋ ስጋት ቅነሳ መረጃዎች በመሰብሰብ፣ ከዚህ ውስጥ የ232ቱን ወረዳዎች የአደጋ ስጋት ቅነሳና ተጣጥሞ የመኖር ዕቅድና የወረዳ መጠባበቂያ ዕቅድ በመስራት ለተጠቃሚው እንዲደርስ ማድረጉን የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ የገለፁ ቢሆንም ስራው ስለመሰራቱ የሚያስረዳ ማስረጃ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ኮሚሽኑ Early warning every action የሚል ጥናት ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ማጥናቱን እንዲሁም የስልጠና ፍላጎት ጥናት(training need assessment) መጠናቱን በተጨማሪም በዓመት ሁለት ጊዜ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ወረዳዎችን ጥናት በማከናወን በጥናቱ መሰረት መግለጫዎች (bulletins) የሚዘጋጁ መሆኑን እንዲሁም ከብሔራዊ ሜትሮሎጂና ከክልል ሪፖርቶች እና መረጃዎችን በመሰበሰብ ለህብረተሰቡ ማስጠንቀቂያዎችን እየተሰጠ መሆኑን፣ ነገር ግን የመረጃ ጥራት ችግሮች እንደሚስተዋሉና በአጠራጣሪ ጉዳዮች ላይ ኮሚሽኑ ማጣራት እንደሚያደርግ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ ቢሆንም በሀገር አቀፍ ደረጃ በኮሚሽኑ አስተባባሪነት ጥናት ስለመጠናቱ፣የጥናት ሂደቱን ስለመምራቱና ጥናቶችን ስለመገምገሙ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፡፡

61.ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ በኮሚሽኑ አስተባባሪነት በዓመት ሁለት ጊዜ የሚደረጉ የምግብና ምግብ-ነክ ያልሆኑ የፍላጐት ጥናት እንደሚከናወን የጥናት መረጃዎችን ያቀረቡ መሆኑንና በጥናቶች መሰረት የተዘጋጀ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል መኖሩን የገለፁ ቢሆንም፣

62. ነገር ግን ኮሚሽኑ ከነዚህ ጥናቶች ውጪ በሀገር አቀፍ ደረጃ ጥናቶችን በማጥናትና በማስተባበር የመፍትሄ እርምጃ ስለመውሰዱ የሰነድ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ በመሆኑ በኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች የተሰጠውን ምላሽ መሉ በሙሉ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

63.ይህም በመሆኑ ኮሚሽኑ በቅድመ-አደጋ፣ በአደጋና በድህረ-አደጋ ወቅት የአደጋ ስጋት ትንበያን ጨምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ ጥናቶችንና ግምገማዎችን በአግባቡ ለመምራት እና ለማስተባበር እንዲሁም በጥናቶች መሰረት አዳዲስ አሰራሮችና የመፍትሄ እርምጃዎችን ለመውሰድ እና የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎችን ለማቀላጠፍና ለማዘመን አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## ኮሚሽኑ የፌደራል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከልን ስራ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን በተመለከተ፡-

64.ኮሚሽኑ የፌደራል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከልን ስራ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ ሊያስተዳድርና ሊመራ ይገባል፡፡

65.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

- ኮሚሽኑ የአስቸኳይ ጊዜ አደጋ ማስተባበሪያ ማዕከል ቢያቋቁምም በሚፈለገው መጠን ስራ ላይ አለመዋሉን በኮሚሽኑ የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን (2010 - 2012) የውጤት ተኮር ዕቅድ ላይ የተገለፀ መሆኑ፤
- ኮሚሽኑ የፌደራል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከልን ስራ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ከማድረግ አንፃር፤
  - ለኮሚሽኑ የመረጃ ማዕከል መረጃዎችን የሚተነትን ሶፍትዌር (Data Analysis software)ያለ መሆኑ፤
  - አምስተርዳም ከሚገኝ ሳተላይትና ሰርቨር መረጃ እንደሚቀበልና ከጂኦኔት ካስት ኢንፍራስትራክቸር (GEONET Cast) የሚገኝ መረጃ መኖሩን፤

- ሊፕ (Livelihood Early Assessment Protection/LEAP/) የሚባል ቴክኖሎጂ እንዲሁም የተለያዩ statistical models የሚጠቀሙ እንደሆነና ነገር ግን ለማዕከሉ የሚያስፈልጉ ኬብሎች ባይኖሩም ለኮሚሽኑ እንደ መረጃ ማእከል ሆኖ እያገለገለ እንደሚገኝ፤
- በተጨማሪም ከሳተላይት የተገኙ መረጃዎችን እንደሚያሰራጩ ነገር ግን የመረጃዎች ጥራት ላይ ጥያቄ የሚነሳበት መሆኑንና ችግሩ እንደ ኮሚሽን ብቻ ሳይሆን እንደ አገር ተፅዕኖ እንደሚያስከትል የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

  - የሶፍትዌሮች አጠቃቀምን በተመለከተ ለሰራተኞች ስልጠና እየተሰጠ መሆኑንና ሁለት ባለሞያዎች እየሰሩ እንደሚገኙ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
  - የኦዲት ቡድኑ በኦዲቱ ወቅት ለኮሚሽኑ ካቀረባቸው እና ከከለሳቸው ማስረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው እ.ኤ.አ የጁን 2018 የሶስተኛው አስር ቀናት እንዲሁም የኦክቶበር 2018 የመጀመሪያው አስር ቀናት የእፅዋት ሽፋን ሁኔታን የሚያሳየው ከGEONET Cast ኢንፍራስትራክቸር የሚገኘውን የSPOT-VGT ግርድፍ የሳተላይት መረጃዎችን መቀበል ያለመቻሉን ከኮሚሽኑ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

66.ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ኮሚሽኑ ጥቃቅን የሆኑ ቁሳቁሶችን በግዥ ባለሟሟላቱ ምክንያት ያሉትንም ቴክኖሎጂዎች መጠቀም አለመቻሉንና ያለው ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ ደረጃ በቂ መሆኑን፤ በስፋት በስድስት ክልሎች ላይ ስራዎችንም በዚህ ዙሪያ ለመስራት የተሞከረ ቢሆንም በኮሚሽኑ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን እና በግዢ ዳይሬክቶሬቶች ዙሪያ ችግሮች በመኖራቸው በሚፈለገው ደረጃ ተግባራዊ አለመሆኑን የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

67.በመሆኑም የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ አለመደርጉ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር በአግባቡ እና በሚፈለገው መጠን እንዳይወጣ እንዲሁም ጥራት ባለው መረጃና በተቀላጠፈ አኳኋን ምላሽ እንዳይሰጥ ያደርገዋል፡፡

## ኮሚሽኑ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከልን በፌደራል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ መስተዳድሮች በሚገኙ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች መመስረቱን በተመለከተ፡-

68. ኮሚሽኑ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከልን በፌደራል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ መስተዳድሮች በሚገኙ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች እንዲመሰረት ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

69. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው በአባሪ በተያያዘ የክልል አደጋ ስጋት ቢሮዎች እና ከተማ አስተዳደር እንዲሁም ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

- በክልሎች ወጥ የሆነ እና ከፌደራሉ አደረጃጀት ጋር የሚናበብ የቢሮ አደረጃጀትና ተዋረድ አለመኖሩን ከኮሚሽኑ የ2010 ዓ.ም የውጤት ተኮር ዕቅድ ለማወቅ መቻሉ፤
- በሀረሪ ክልል የስርአተ-ምግብ ማስተባበርያ ቡድን እንዲሁም ባለሙያዎች በመዋቅር ደረጃ የሌለ መሆኑና ኮሚሽኑም በዚህ ዙሪያ ድጋፍ አለማድረጉን፤ ይህም የስርአተ-ምግብ ማስተባበርያ ቡድን ባለመቋቋሙ ምክንያትም በስርዓተ-ምግብ ዙሪያ መሰራት ያለባቸው ስራዎች አለመሰራቱን የክልሉ የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- በደቡብ ክልል የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎችን የሚሰራ በርዕሰ መስተዳድር የሚመራ ካውንስል የተደራጀ መሆኑንና እቅዶቹ በካውንስሉ የሚፀድቁ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ የክልሉ ጤና ቢሮ ከሚመራው የስርዓተ-ምግብ(የኒውትሪሽን) ኮሚቴ እና ትምህርትን በተመለከተ በክልሉ ትምህርት ቢሮ ከሚመራው ኮሚቴ ውጪ እንደ ክልል የአደጋ ስጋት ቢሮ የተቋቋሙ ኮሚቴዎች አለመኖራቸውን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በተጨማሪም በክልሉ በጌዲኦ ዞን በፌደራል ደረጃ እና በክልሉ በጋራ የሚመራ የአደጋ ጊዜ ማስተባበሪያ ማዕከል EOC(Emergency Operation Center) እንደነበር እንዲሁም በደቡብ ክልል ሴክተር መስሪያ ቤቶች የብሔራዊ ካውንስል አባላት ከመሆናቸው ውጭ በአደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲ ዙሪያ በስልጠናም ይሁን ግንዛቤ በመስጠት ወደስራ አለመግባታቸውን የክልሉና የዞኑ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

- የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎችን ጭምር የሚመሩ እና የሚያስተባብሩ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚቴዎችን በዘላቂነት ለማቋቋም ዝግጅት ከማድረግ ባለፈ እንዳልተሰራና የተቋቋሙት ኮሚቴዎችም ስራቸውን እንደማይሰሩና ኮሚሽኑም በዚህ ዙሪያ ድጋፍ አለማድረጉን የአስተዳደሩ የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በኦሮሚያ ክልል መሪ ሴክተር መ/ቤቶችን የመለየት ስራ መሰራቱንና በየሁለት ሳምንቱ በታስክ ፎርስ (task force) አማካኝነት ውይይት እንደሚደረግና በመሪ ሴክተር መ/ቤቶች መካተት ስላለባቸው ተግባራት እቅድ በማውጣት እንደላኩና ኮሚሽኑም መመሪያ የሰጠበት ሁኔታ መኖሩን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች የገለፁ ቢሆንም የኦዲት ቡዱኑ ክልሉ ከኮሚሽኑ በተሰጠ መመሪያ መሰረት ስላከናወነው ስራ የሚያስረዳ ማስረጃ ጠይቆ ሊቀርብ አለመቻሉ፤

70. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ላይ የተለያዩ ሥልጠናዎች ለክልሎች የተሰጠ መሆኑን፤ በUSAID ድጋፍ NIMS (National Incident Management System) በሚባለው ሥርዓት ስለ የአደጋ ጊዜ ማስተባበሪያ ማዕከልEOC ተደጋጋሚ ሥልጠና የተሰጠና አንዳንድ ክልሎች የአደጋ ጊዜ ማስተባበሪያ ማዕከል EOC (Emergency Operation Center) ያቋቋሙ መሆኑንና ባልተማከለ አስተዳደር የፌዴራል መንግሥት በክልል ጉዳይ ገብቶ አደረጃጀት የማይወስን መሆኑንና ሁሉም ክልል የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚቴ ያላቸው መሆኑና እንቅስቃሴያቸው በክልሉ በሚከሰተው የአደጋ ዓይነት መጠንና ድግግሞሽ የሚወሰን እና የሚለያይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

71. ይሁን እንጂ የስራ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ ደንብ ላይ እንደተቀመጠው ኮሚሽኑ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከልን በፌደራል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ መስተዳድሮች በሚገኙ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች እንዲመሰረት ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባ በግልፅ የተቀመጠ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ መሉ በሙሉ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

72. በመሆኑም በየደረጃው ባሉ የአስተዳደር እርከኖች ወጥ የሆነ እና የሚናበቡ የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከላት ባለመመስረታቸው በክልሎች እና መሪ ሴክተር መ/ቤቶች ወጥነት እንዳይኖራቸው ከማድረጉ በተጨማሪ ስራዎችን በአግባቡ ለመምራት አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

**ኮሚሽኑ የመረጃና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ**

**ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር በስፋት ጥቅም**

**መዋሉን በተመለከተ፡-**

73.ኮሚሽኑ የመረጃና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል ሁኔታዎችን ሊያመቻችና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

74.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው በአባሪ በተያያዘ የክልል አደጋ ስጋት ቢሮዎች እና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ሁለቱ የኮሚሽኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ሁኔታወች ታይተዋል፡-

- የኮሚሽኑ መረጃዎች በተማከለ ቦታ የማይያዙ መሆኑንና ወቅቱን የጠበቀና የተናበበ የኢንፎርሚሽን ቴክኖሎጂ ሲስተም ተግባራዊ አለመደረጉን ከኮሚሽኑ የ2010 ዓ.ም የውጤት ተኮር ዕቅድ ላይ ለማወቅ መቻሉ፣
- የአገልግሎት አሰጣጥ በስራ ፍሰት አለመተሳሰሩንና በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ መሆኑን እንዲሁም ወቅታዊ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው አካላት በጥራት፣ በስፋትና በቀጣይነት ለማስተላለፍ የታቀደ ቢሆንም በሰርቨር መዘግየት ምክንያት መረጃዎችን በዌብ ሳይት ላይ መልቀቅና ለተጠቃሚ ማድረስ እንዳልተቻለና በተጨማሪም የአደጋ ስጋት ስራ አመራር መረጃ ስርዓቱ ዘመናዊና በቴክኖሎጂ የተደገፈ አለመሆኑንና የኮሚሽኑ ዳይሬክቶሬቶች እርስ በርስ የሚናበቡበትና የአደጋ ስጋት መረጃዎችን ለመለዋወጥ የሚያስችል በቴክኖሎጂ የተደገፈ (Wide Area Network) አለመኖሩን ከአደጋ ስጋት ቅነሳ ዳይሬክቶሬት የ2010 ዓ.ም የሁለተኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ለማወቅ መቻሉ፣
- የኮሚሽኑ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና አስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ዳይሬክቶሬት አሰራርን ለማሻሻል በLEAP እና Geonet Cast software የዝናብ እና የእፅዋት ሁኔታን እንዲሁም ሌሎች መረጃዎችን ከሳተላይት በማግኘት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃዎችን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ እየዋለ እንደሚገኝና በተጨማሪም ከመ/ቤቱ የመረጃ ቋት የተለያዩ ጠቃሚ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃዎችን በመውሰድ ለተለያዩ አላማዎች እንዲውሉ እያደረገ እንደሚገኝ፣ ይሁን እንጂ የኮሚሽኑ የወረዳ ኮኔክቲቪቲ በወረዳ ደረጃ እየተደራጀ ወቅታዊ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር የማድረግ፣ የእርዳታ ስርጭትን መረጃ የማደራጀት (Commodity Allocation and Tracking System-CATS) የድንገተኛ አደጋ ማስተባበሪያ ማዕከል መሰረቶች የተጣሉ ቢሆንም በአቅም ውስንነት፣ በሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣

በቴክኖሎጂው እድገትና ውስብስብነት፣ በልምድና በመሳሰሉት ምክንያቶች የተፈለገውን ውጤት እንዳላመጣ የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

- በሀረሪ ክልል ኮሚሽኑ ወረዳ ኔት እንዲገባ ያደረገ ቢሆንም ሶፍት ዌር እየቆመ መሆኑንና ክልሉ አቅም የሌለው በመሆኑ አለመጠገኑንና ከዞንና ወረዳዎች ጋር በስልክ ብቻ የሚገናኙ በመሆኑ ኮሚሽኑ ወደ ክልል በማውረድ እንዲተገበሩ ሊያደርግ እንደሚገባ የክልሉ የአደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በሶማሌ ክልል ከክልሉ ከተማ በስተቀር በወረዳዎች አካባቢ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት አለመኖሩን የክልሉ የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በደቡብ ክልል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሳሪያን ለአደጋ ምላሽ የመጠቀም ስራ ተጀምሮ መቋረጡን በተለይ ወረዳ ኔት (Woreda Net) ተጀምሮ የተቋረጠ በመሆኑ በተሟላ መልኩ የመረጃና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለአደጋ ምላሽ ስራ ጥቅም ላይ እየዋለ አለመሆኑንና በተጨማሪም በዘርፉ አቅምና ክህሎት ያለው የሰው ኃይል በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚያስፈልግ የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ኮሚሽኑ ወረዳ ኔት እንዲቋቋም ቢያደርግም መቋረጡን የከተማ አስተዳደሩ የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- የኦሮሚያ ክልል የመረጃ ማእከል ለመገንባት በሂደት ላይ መሆኑንና ወረዳ ኔት (Woreda Net) በክልሉ ባሉ 12 ወረዳዎች ላይ ብቻ ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑን እንዲሁም ሌሎች የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች በጅምር ላይ በመሆናቸው በክልሉ ካሉ መዋቅሮች ጋር በአብዛኛው በኢሜል(email) የመገናኘት አሰራር ብቻ መኖሩን፣ በዚህ ዙሪያ ኮሚሽኑ ምንም ድጋፍ አለማድረጉን ቴክኖሎጂው ባለመኖሩ የመረጃ ፍሰቱ ላይ ችግር እየፈጠረ መሆኑን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኮሚሽኑ በኩል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መገልገያዎች ግዢ እንደማይከናወንና ጊዜያቸው ያለፈባቸው እንዲሁም ያረጁ መሳሪያዎች አልፎ አልፎ ለቅርንጫፉ የሚላኩበት ሁኔታ መኖሩን በዚህ ምክንያት የኮምፒውተር፣ የፕሪንተር፣ የባክ አፕ ቁሳቁስ ችግሮች መኖሩን፣ በተጨማሪም በቅርንጫፉ ያሉት ቁሳቁሶችም በዕርዳታ ያገኙዋቸው እንደሆኑና የጥገና ባለሙያም ባለመኖሩ በክፍያ ከውጭ ባለሙያ በማስመጣት የሚያስጠግኑ መሆኑን የቅርንጫፉ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከኢንተርኔት አገልግሎት ባለፈ ዴስክቶፕ፣ ኮምፒተር፣ስካነር መሳሪያዎች አለመኖሩን እንዲሁም መሰረታዊ የኮምፒውተር ስልጠና ባለመሰጠቱ በስራ

ላይ ክፍተት መፍጠሩንና በተጨማሪም መጋዘኖች አካባቢ የሚሰሩ ሰራተኞች የኢንተርኔትና የመብራት አገልግሎት የሌላቸው መሆኑን የቅርንጫፉ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

75.ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ከግዥ ጋር በተያያዘ ያሉት ቴክኖሎጂዎችን ጥቅም ላይ ለማዋል ችግሮች መፈጠራቸው ማለትም በኬብል ግዥ ችግር ምክንያት የተስተጓጎለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

76.እንዲሁም የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ኮሚሽኑ አዲስ የተቋቋመ ስለሆነ ገና መረጃ እያደራጀ መሆኑን፣ በቢሮ ለውጥ ምክንያት ሰርቨር/server/ በአዲስ መልክ እየተተከለ መሆኑንና እንዲሁም የኮሚሽኑ ቢሮዎች ሶስት ቦታዎች ተበታትነው የሚገኙ በመሆኑ እና በተጨማሪም ክልሎች ፌዴራል መንግሥትን መጠበቅ ሳይኖርባቸው በራሳቸው ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ገልፀዋል፡፡

77. በመሆኑም የኮሚሽኑ መረጃዎች በተማከለ እና ባግባቡ ለመያዝ ወቅቱን የጠበቀና የተናበበ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሲስተም በክልሎች እና በወረዳዎች ተግባራዊ ባለመደርጉ እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጡ በስራ ፍሰት ባለመተሳሰሩ ምክንያት በቴክኖሎጂ የተደገፈና እንዲሁም ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው አካላት በጥራት፣ በስፋትና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማስተላለፍ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## ኮሚሽኑ በየደረጃው የሚቋቋሙ የአደጋ ክስተት ማስተባባሪያ መዋቅሮች በአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል አስተማማኝና የማያቋርጥ የመገናኛ መሳሪያዎችን በተመለከተ፡-

78.ኮሚሽኑ በየደረጃው የሚቋቋሙ የአደጋ ክስተት ማስተባባሪያ መዋቅሮች በአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉ አስተማማኝና የማያቋርጡ የመገናኛ መሳሪያዎች እንዲኖሩ ሊያደርግ ይገባል፡፡

79.ይሁን እንጅ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው በአባሪ በተያያዘ የክልል አደጋ ስጋት ቢሮዎች እና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ሁለቱ የኮሚሽኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

- በኦዲቱ ወቅት ኮሚሽኑ በአደጋ ጊዜ በየደረጃው ካሉ የአደጋ ክስተት መዋቅሮች ጋር ለመገናኘት የሚያስችል የተሻለ የመገናኛ አማራጭ ባለመኖሩ በኢሜል እንዲሁም በስልክ ብቻ መረጃዎችን እንደሚለዋወጡና አልፎ አልፎ ከግለሰቦች ቅንነት ጋር ተያይዞ ስልክ የማይነሳበት ሁኔታ መኖሩን የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

- ኮሚሽኑ በዚህ ዙሪያ ስለሰራው ስራ የሚያመላክት በሰነድ የተደገፈ ማስረጃ የኦዲት ቡድኑ አላገኘም፡፡

80. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ወረዳኔት (Werda Net) ለመተግበር በእንቅስቃሴ ላይ የነበረ ቢሆንም የተለያዩ ችግሮች ያሉበት በመሆኑ እየሰራ አለመሆኑን፣የሰው ኃይል እጥረት መኖሩን እንዲሁም በቴሌ ዙሪያ ችግሮች የሚስተዋሉ መሆኑንና በአጠቃላይ በተለመደው የመገናኛ መሳሪያ ማለትም በስልክ፣ በኢሜይልና በፋክስ በመጠቀም ስራዎች የሚሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
   - እንዲሁም የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ይህ ከአደጋ ጊዜ ማስተባበሪያ ማዕከል (Emergency Operation Center /EOC/) መቋቋም ጋር ተያይዞ እንደ አንድ ፓኬጅ የሚፈጸም መሆኑን ገልፀዋል፡፡

81. የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ የኦዲት ቡድኑ በደ/ብ/ብ/ህ ክልላዊ መንግስት በጌዲኦ ዞን ከተቋቋመው የአደጋ ጊዜ ማስተባበሪያ ማዕከል (Emergency Operation Center /EOC/) በስተቀር በናሙና ተመርጠው በታዩ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በሀረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣በደ/ብ/ብ/ህ ክልላዊ መንግስት እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ በሁሉም በየደረጃው ባሉ የአስተዳደር መዋቅሮች (ክልል፣ ዞኖች እና ወረዳዎች) የአደጋ ጊዜ ማስተባበርያ ማዕከል ያልተቋቋመ በመሆኑ እና በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ ደንብ ላይ እንደተቀመጠው ኮሚሽኑ በየደረጃው የሚቋቋሙ የአደጋ ክስተት ማስተባባሪያ መዋቅሮች በአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል አስተማማኝና የማያቋርጥ የመገናኛ መሳሪያ እንዲኖር ሊያደርግ እንደሚገባ የተገለፀ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ መሉ በሙሉ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

82. በመሆኑም በየደረጃው ካሉ የአደጋ ክስተት መዋቅሮች ጋር በአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል አስተማማኝና የማያቋርጥ የመገናኛ መሳሪያ አማራጭ አለመኖሩ በመረጃ ፍሰቱና በአደጋ ምላሽ አሰጣጡ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

**ኮሚሽኑ አደጋ በይፋ መገለፁን ተከትሎ**
**የአደጋ ስራ አመራር ምክር ቤት ሲወስን**
**ከአገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ሀብት ያሰባሰበ**
**እና ለአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ስራን በተመለከተ፡-**

83. ኮሚሽኑ አደጋ በይፋ መገለፁን ተከትሎ የአደጋ ስራ አመራር ም/ቤት ሲወስን ከአገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ሀብት ሊያሰባስብ እና ለአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ስራ ጥቅም ላይ እንዲውል ሊያደርግ ይገባል፡፡

84. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው በአባሪ በተያያዘ የክልል አደጋ ስጋት ቢሮዎች እና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ሁለቱ የኮሚሽኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ኮሚሽኑ ሃብት ለማሰባሰብና ለማስተዳደር የሚያስችል ተግባርና ኃላፊነት ያለው ቢሆንም የኮሚሽኑ ደንብ ወጥቶ ተግባራዊ ከተደረገ ገና ሁለት አመቱ በመሆኑና አሰራሩ የተደራጀ ባለመሆኑ እንዲሁም ቀድሞ የነበረውን የብሔራዊ አደጋ ምላሽ ፈንድ ጽ/ቤትና የአደጋ መከላከልና ዝግጁነትን በአንድ መዋቅር እንዲዋሃድ በመወሰኑና አሰራሩ በአዲሱ ደንብ መሻሩን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሃብት ማሰባሰብ፣ አስተዳደር፣ የፕሮጀክት አደረጃጀትና ሂደት፣ የፈንድ ግንባታና ጠቀሜታ፣ የድጋፍ ግንኙነትን በተመለከተ ሁለቱ ተቋማት እንዲጠቀሙበት ታስቦ የነበረውን የሁለቱን ተቋማት ከሃያ ዓመት በፊት የተጠና ጥናት በማቀናጀትና ከአዲሱ ደንብ ጋር አስተሳስሮ ለመሄድ ህጋዊ የሆነና መንግስታዊ እውቅና ያለው የአሰራር መመሪያ ለማዘጋጀት የሚረዳ ጥናት እንዲጠና ታስቦ ለጥናቱ መነሻ የሚሆን ቢጋር (Terms of Reference) ተዘጋጅቶ ወደ አንድ ዓመት ጊዜ ለጥናት የሚያስፈልገውን የሃብት ፍለጋ እያካሄደ የሚገኝ መሆኑን የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ የገለፁ ቢሆንም የኦዲት ቡድኑ በዚህ ዙሪያ ስለተሰራው ስራ በሰነድ የተደገፈ ማስረጃ አላገኘም፡፡

85. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ጥናት እንዲጠና የቀረበው ቢጋር በሀብት አሰባሰብና ፈንድ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እጅ እንደሚገኝ የገለፁ ቢሆንም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

86. በመሆኑም ኮሚሽኑ አደጋ በይፋ መገለፁን ተከትሎ የአደጋ ስራ አመራር ም/ቤት ሲወስን ከአገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ሀብት በማሰባሰብ ለአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ስራ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የሃብት ማሰባሰብ፣ አስተዳደር፣ የፕሮጀክት አደረጃጀትና ሂደት፣ የፈንድ ግንባታና ጠቀሜታ፣ የድጋፍ ግንኙነትን በተመለከተ ህጋዊ የሆነና መንግስታዊ እውቅና ያለው የአሰራር

መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆን አለማድረጉ ለአደጋ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል በቂ ሀብት እንዳይፈጠር ከማድረጉ በተጨማሪ አደጋ በሚከሰትበት ወቅት መወሰድ የሚገባቸውን ተገቢ እርምጃዎች በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ እንዳይወሰድ ያደርጋል፡፡

## ኮሚሽኑ ውጤታማ የሆነ የሀብት አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት የዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፡-

87. ኮሚሽኑ ውጤታማ የሆነ የሀብት አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

88. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው በአባሪ በተያዘ የክልል አደጋ ስጋት ቢሮዎች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና ሁለቱ የኮሚሽኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲሁም ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

- የኮሚሽኑ አደጋ ምላሽ ዝግጁነት አቅም በሚፈለገው ደረጃ ሳይደርስ የለጋሽ ድርጅቶች እርዳታ መቀነስ ችግር መኖሩን በኮሚሽኑ የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የሶስት ዓመታት (2010-2012) የውጤት ተኮር ዕቅድ ላይ መገለፁ፡፡
- ኮሚሽኑ በዚህ ዙሪያ አሰራሩ በህግ ማዕቀፍ፣ በመመሪያና ደንብ የአሰራር ስርዓቶችን በማበጀት ረገድ ስራዎችን እንዳልሰራና የሃብት ማሰባሰብና ፈንድ አስተዳደር መመሪያን ለማዘጋጀት እንዲረዳ ከዘጠኝ ወራት በፊት ቢጋር ተዘጋጅቶ በአለም አቀፍ ኮንሰልታንቶች ጥናት ለማስደረግ እንዲረዳ ሃብት የማፈላለግ ስራ መጀመሩን እንዲሁም ኮሚሽኑ ሃብት እንዴት ይገኛል፣ እነማን ምን ያህሉን ያስተዳድሩት፣ ለምን ተግባር፣ እንዴት ክትትል ይደረግበት፣ በምን የህግ ማዕቀፍ ይከናወን፣ ከለጋሽ ድርጅቶችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በምን ላይ በተመሰረተ መርህ ግንኙነት ይደረግ እና የመሳሰሉትን ሥራዎች እንዳልሰራና በተጨማሪም የሃብት ብክነትንና ስርጭትን፣ የግዥ አሰራርን እና ውጤታቸውን ቋሚ በሆነ አሰራር ለመገምገም የሚያስችል አሰራር አለመዘርጋቱን የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡
- በሀረሪ ክልል ለሚከሰቱ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል ክልሉ የመጠባበቂያ ፈንድ አሰባሰብ ደንብ በማዘጋጀት በ2010 ዓ.ም ሀብት የማሰባሰብ ስራዎች የተጀመሩ መሆኑንና ኮሚሽኑ ችግር ካልተፈጠረ በቀር የክልሉን የዝግጁነት አቅም ለማጎልበት የሚያደርገው ምንም ዓይነት ድጋፍ አለመኖሩን፣ እንዲሁም በክልሉ ወደ ህብረተሰቡ በመውረድ ሀብት በማሰባሰብ የማስቀመጥ ስራ ታቅዶ፡›‹ እየተሰራ እንደሆነ የክልሉ የአደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

- የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በየዓመቱ ቆጠራ የሚያከናውን ቢሆንም ኦዲት የማይደረግ መሆኑንና ኦዲት ባለመከናወኑ የሚፈጠሩ ችግሮችን እና ስህተቶችን በወቅቱ ማስተካከልና ግንዛቤ እንዲወሰድ አለማድረጉን እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ ስጋት ያለበት ስራ በመሆኑ የውስጥ ኦዲት ስራ መከናወን እንደሚያስፈልግ የቅርንጫፉ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ከቦታ ጥበት አንጻር አንድ ላይ የሚቀመጡበት ሁኔታ በመኖሩ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ሰፊ ቦታ ስለሚይዙ ከፍተኛ የሆነ የቦታ መጣበብ መፍጠሩን የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በየአመቱ ከሚከናወነው የንብረት ቆጠራ ውጪ የኦዲት ስራ የማይከናወን መሆኑን በመዋቅር የውስጥ ቁጥጥርና ኦዲት ዘርፍ የተቀመጠ ቢሆንም እስካሁን ምደባ ያልተደረገለት መሆኑን እንዲሁም ከኮሚሽኑ አልፎ አልፎ ባለሙያዎች ቢመጡም በየጊዜው ክትትልና ኦዲት የሚያደርግ አካል እንደሌለና ከስራው ብዛትና ስፋት እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ ሀብት የሚንቀሳቀስበት ከመሆኑ አንፃር የውስጥ ቁጥጥርና ኦዲት ማድረግ አስፈላጊ ቢሆንም እየተደረገ እንዳልሆነና አመታትን ጠብቆ ኦዲት ማድረግ አግባብ ባለመሆኑ ችግሩ ሊቀረፍ እንደሚገባ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ተለይተው የሚቀመጡ ቢሆንም ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ማስቀመጫ ቦታ ጥበት በመኖሩና አላስፈላጊና መወገድ የሚገባቸው እቃዎች መጋዘኑን ያጣበቡ መሆኑና ምግብ ነክ የሆኑ ቁሳቁሶችን ከብልሽት ለመታደግ የሚያስፈልግ የመድኃኒት አቅርቦት በኮሚሽኑ በኩል በወቅቱ ባለመቅረቡ የመድኃኒት ርጭትና የማከም ስራ የሚከናወነው በዓለም ምግብ ፕሮግራም በኩል በሚሰጥ ድጋፍ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ በአቅራቢያው የዓለም ምግብ ፕሮግራም ድርጅት ባይኖር ኖሮ ከፍተኛ የሆነ ብልሽትና ውድመት ሊያስከትል የሚችልበት ሁኔታ ሰፊ መሆኑን የቅርንጫፉ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- ከድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወደ ኮሚሽኑ የሚላኩ ሰነዶች (የክፍያ ሂሳብ) በወቅቱ የማይወራረዱ በመሆኑ ለረጅም ዓመታት የቆዩ ሰነዶችን ወደኋላ ተመልሶ የሚጠየቅበት ሁኔታ መኖሩን የቅርንጫፉ የሥራ ኃላፊዎች በተጨማሪ ገልፀዋል፡፡

89.ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ፡-

- የፋይናንስ ሀብት አስተዳደርና ግዥ የፋይናንስ አዋጅ ተከትሎ እየተፈፀመ ያለ መሆኑን፣

- ከለጋሽ ድርጅቶችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ያለው ግንኙነት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ስምምነት ላይ በተደረሰባቸው የግንኙነት መስኮች የሚከናወንና ስምሪታቸውም ከኮሚሽኑ ጋር በአገር አቀፍ ደረጃ ከገቡት ስምምነት ጋር ተያይዞ የሚመራ መሆኑን፤
- የሀብት ማሰባሰብ ሥራ የህግ ማዕቀፍ የሚፈልግና የህብረተሰቡ የግል ባለሀብቱን ሙሉ ይሁንታ የሚጠይቅ መሆኑን፡
- የሀብት ብክነትና ስርጭትን በተመለከተ ከክልሎች ከፀጥታ አካላት ጋር በመገናኘት የመስክ ምልከታ በማድረግና ወንጀል ሲፈጸምም ለህግ በማቅረብ እየተሠራ ያለ ጉዳይ መሆኑን፤
- የዓለም ምግብ ፕሮግራም ከኮምሽኑ ጋር አብሮ የሚሠራና እርስ በርስ የሚደጋገፍ መሆኑን፤
- የውስጥ ኦዲት በመዋቅር ላይ የሌለ ስለሆነ በአዲሱ አደረጃጀት ለሁሉም ማዕከላዊ መጋዘኖች የውስጥ ኦዲት መዋቅር እንዲፈጠር የሚደረገ መሆኑን፤ለጊዜው ግን ከዋና መሥሪያ ቤት በመስክ ኦዲት እየተደረገ መሆኑን፤
- ከመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጋር በመሆን ያረጁ ንብረቶች የማስወገድ ሥራ እየተሠራ ሲሆን፣ በማዕከላዊ መጋዘኖች ያለው ተጠንቶ በሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝር ውስጥ የተካተተ መሆኑንና ማንሳት ብቻ የቀረው መሆኑን እዲሁም ሂሳብ ለማወራረድ ከፍተኛ የሥራ ጫና ስላለ ተጨማሪ የሰው ኃይል መመደብ የሚጠይቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

90. የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ በኮሚሽኑ ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ እንደተቀመጠው ኮሚሽኑ ውጤታማ የሆነ የሀብት አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባው የተገለፀ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ የተሰጠውን ምላሽ መሉ በሙሉ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

91. በመሆኑም ኮሚሽኑ በዚህ ዙሪያ አሰራሩን በህግ ማዕቀፍ፣ በደንብና በመመሪያ የተደገፈ የአሰራር ስርዓቶችን በማበጀት ረገድ ስራዎችን ባለመስራቱ እንዲሁም የሃብት ማሰባሰብና ፈንድ አስተዳደር መመሪያን ባለማዘጋጀቱ የአደጋ ምላሽ ዝግጁነት አቅም በሚፈለገው ደረጃ እንዲደርስ ካለማስቻሉ በተጨማሪ የሃብት ብክነትንና ስርጭትን፣ የግዥ አሰራርን እና ውጤታማነትን ቋሚ በሆነ አሰራር ለመገምገምና ለመቆጣጠር አያስችለውም፡፡

## ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ሀብት ከውጭ ሀገር የማሰባሰብና የመጠቀም አሰራርን በተመለከተ መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡-

92.ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ሀብት ከውጭ ሀገር የማሰባሰብና የመጠቀም አሰራርን በተመለከተ መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

93.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩና ዝርዝራቸው በአባሪ በተያያዘ የክልል አደጋ ስጋት ቢሮዎች እና ከተማ አስተዳደር እንዲሁም ሁለቱ የኮሚሽኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ሁኔታወች ተገኝተዋል፡-

- የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ-መጠይቅ መሰረት ኮሚሽኑ ለተረጂዎች ድጋፍ ለማድረግ የሀብት እጥረት በተለይም ምግብ ነክ ባልሆኑ ቁሳቁሶች ላይ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት(NGOs) እና አለም አቀፍ ድርጅቶችን(UN Agencies) በማስተባበር የሐብት ክፍተቱን እየሞላ መሆኑን እንዲሁም የሃብት ማሰባሰብና ፈንድ አስተዳደር መመሪያን ለማዘጋጀት እንዲረዳ ከዘጠኝ ወራት በፊት ቢጋር ተዘጋጅቶ በዓለም አቀፍ ኮንሰልታንቶች ጥናት ለማስደረግ ሃብት የማፈላለግ ስራ መጀመሩን የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- ለአደጋ ምላሽ ሀብት ከውጭ ሀገር ለማሰባሰብና ለመጠቀም ፈንድ ሬይዚንግ (Fund Raising) መመሪያ ሊኖር እንደሚችል የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች የገለፁ ቢሆንም ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ከውጭ ሀገር ሀብት ለማሰባሰብና ለመጠቀም የሚያስችል አሰራርና መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ስለማድረጉ የሚያመላክት በሰነድ የተደገፈ ማስረጃ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

94.ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ከውጭ ሃብት የሚሰባሰበው በዓመት ሁለት ጊዜ በሚዘጋጀው የሰብዓዊ ድጋፍ ፍላጐት ሰነድ /Humanitarian requirement document/ መሠረት መሆኑን፤ ከውጭ የሚገኘው ሀብት በቀጥታ ለመንግሥት የማይሰጥ መሆኑን፤ በ(United Nations Office for the Coordination of Humanitarian Affairs) UNOCHA፣ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት (UN) እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (NGO) አማካኝነት ሥራ ላይ የሚውል መሆኑን፤ ለመንግሥት በቀጥታ የሚሰጡ የDepartment for International Development(DFID) ቻይናና ህንድ ሲሆኑ ግንኙነታቸውም በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በኩል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

95.የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ በኮሚሽኑ ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ እንደተቀመጠው ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ሀብት ከውጭ ሀገር የማሰባሰብና የመጠቀም አሰራርን በተመለከተ መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የተገለፀ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ መሉ በሙሉ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

96.በመሆኑም ለአደጋ ምላሽ ሀብት ከውጭ ሀገር ለማሰባሰብና ለመጠቀም መመሪያ ባለመኖሩ ለተረጂዎች ድጋፍ የሚውል ሀብት ወጥነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ለማሰባሰብ እንዳይቻል ከማድረጉም በላይ በቂ የሀብት ክምችት እንዳይያዝና እንዳይሰበሰብ ያደርጋል፡፡

## ኮሚሽኑ የሚያስፈልገውን የሰው ሀይል ማሟላቱን እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ማብቃቱን በተመለከተ፡-

97.ኮሚሽኑ በመዋቅሩ መሰረት የሰው ሀይል ሊያሟላ እና በአደጋ ክስተት ስራ አመራር የተሰማራ የሰው ኃይል እውቀቱንና ክህሎቱን በስልጠና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማዳበር እንዲያስችል የስልጠና ማዕከል በማቋቋም ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

98.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ጉዳዩን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረጉ ቃለ-መጠይቆች መሰረት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በኮሚሽኑ የተፈቀደ መዋቅር መሰረት ወሳኝ የሚባሉ ስራዎችን በሰው ኃይል ለማሟላት የደመወዝ በጀት እጥረት በመኖሩ ምክንያት የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል በቂ ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎች እጥረት መኖሩን ከኮሚሽኑ የ2009 ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ መቻሉ፣
- የኮሚሽኑ ሰራተኞች የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ የክህሎት ውስንነት መኖሩን በኮሚሽኑ የ2010 ዓ.ም የውጤት ተኮር ዕቅድ ለማወቅ መቻሉ፣
- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመዋቅር 64 ሰራተኞች የተፈቀደለት ቢሆንም በመዋቅር ከተፈደቀው ውስጥ 47% ወይም 30 ሰራተኞች ቅጥር አለመከናወኑን በተለይም የሰው ሀብት፣ የመጋዘን ኃላፊዎች፣ የንብረት ቁጥጥርና የኦዲት ዘርፎች ቅጥር ባለመሟላቱ ሰራተኞችን በኮንትራት ቀጥረው ለማሰራት የተገደዱ እንደሆነና ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የቢሮ ዕቃዎች ግዢ እንደማይከናወንና ከፍተኛ የቁሳቁስ እጥረት መኖሩ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመዋቅር 115 ሰራተኞች የተፈቀደለት ቢሆንም በመዋቅሩ ከተፈቀደው ውስጥ 83 ሰራተኛ ብቻ ቅጥር መፈፀሙ እንዲሁም የሰው ኃይል ለመቅጠር

በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የቢሮ ጥበት መኖሩን የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

- የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በክፍት የስራ መደቦች ላይ ሰራተኞች እንዲቀጠሩ በቀን 28/12/2009 ለኮሚሽኑ ሰው ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ቢጠይቅም ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ ሰራተኞች የተመደቡ አለመሆኑን ለማወቅ መቻሉ፤
- በዚህ ዙሪያ ኮሚሽኑ የስልጠና ማዕከል በማቋቋም ቀጣይነት ባለው መልኩ የሰው ኃይል ክህሎትና ዕውቀትን በስልጠና እየሞላ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ድረስ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

99. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ፡-

- በበጀት እጥረት ምክንያት ክፍት መደቦች ማሟላት ያልተቻለ መሆኑና በአዲሱ መዋቅር የሚታይ መሆኑን፤
- የሥልጠና ማዕከሉ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር የተቋቋመ ሲሆን የተወሰኑ ባለሙያዎችን በኢትዮጵያና በጐረቤት አገሮች እንዲሰለጥኑ መደረጉ እና ወደፊት የሚጠናከር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

100. ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ በጡረታ የተገለሉ ሰራተኞችን ብዛት ባለው ሁኔታ በኮንትራት የሚቀጠሩበት አሰራር እያለ እንዲሁም ከአጠቃላይ የሰው ኃይሉ ውስጥ 136 የኮንትራት ሰራተኞች ሆነው ሳለ በበጀት ዕጥረት ማሟላት አለመቻሉ የሚለው ምላሽ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

101. በመሆኑም ለኮሚሽኑ በተፈቀደ መዋቅር መሰረት የሰው ኃይል ባለመሟላቱና የአቅም ግንባታ ስራ ባለማከናወኑ በቂ ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎች እጥረት እንዲኖር እና የተቋሙን ተልዕኮ በሚፈለገው ደረጃ ለማሳካት ያስቸግራል፡፡

## የኮሚሽኑ የባለብዙ ዘርፍ ስራዎችን በተመለከ፡-

102. ኮሚሽኑ በአደጋ ክስተት ስራ ዙሪያ የሚወጡ ህጎች፣ መመሪያዎች፣ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች እንዲሁም የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎች ውስጥ ለሴቶች፤ ለህፃናት፣ ለአረጋዊያን፣ ለአካል ጉዳተኞችና ኤች.አይቪ. ኤድስ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ ትኩረት ስለመሰጠታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

103. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ጉዳዩን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የኮሚሽኑ የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረጉ ቃለ-መጠይቆች መሰረት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ኮሚሽኑ በዚህ ዙሪያ ክትትልና ግምገማ እያደረገ እንዲሁም በመመሪያ፣ በፕሮግራምና በዕቅዶች ውስጥ ተካቶ በየደረጃው ተፈፃሚ ስለማድረጉ የሚያመላክት በሰነድ የተደገፈ ማስረጃ ተጠይቆ ለኦዲት ቡድኑ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ አልቀረበም፡፡
- የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎችን በተመለከተ ለእናቶችና ለህፃናት የሚደረገው ልዩ ድጋፍ/አልሚ ምግብ/ በቂ እንዳልሆነና የእናቶችና የህፃናት ሰውነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱ ከዞን የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ጽ/ቤት የተገኙ መረጃዎች ያመላከቱ መሆኑንና  የህፃናት ምግብ (የወተትና አልሚ ምግብ) ከሚጠየቀው የምግብ ሬሽን ጎን ለጎን ተሟልቶ አለመቅረቡን ኮሚሽኑ በመጋቢት 2010 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ የተለያዩ ዞኖችና ከተሞች ባደረገው የመስክ ጥናት ላይ ታውቋል፡፡
- በዚህ ዙሪያ ኮሚሽኑ የስርጭት ሂደቱ ለአቅመ ደካሞች (አረጋውያን)፣ ነፍሰ ጡርና አጥቢ እናቶች፣ ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ ለሚገኙ ትኩረት አድርጎ እንደሚከናወንና እርዳታ በሚሰጡ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በራሳቸው የመስክ ክትትል በማድረግ፣ በመንግስት የሚሰጠው ድጋፍ በክልል ደረጃ እስከ ዝቅተኛው አስፈጻሚ ባለው የመንግስት መዋቅር እንዲሁም ከፌዴራል በሚንቀሳቀስ የቴክኒክ ቡድን አማካኝነት ክትትል እንደሚደረግ የኮሚሽኑ  የሥራ ኃላፊዎች የገለፁ ቢሆንም የኦዲት ቡደኑ ከክልል የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም የስራ ኃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ-መጠይቆች ከኮሚሽኑ ኃላፊዎች አስተያየት በተለየ መልኩ እንደሚከተለው ገልፀዋል፣
  - የሀረሪ ክልል የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎች ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ ለአካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ያካተተና ቅድሚያ የሰጠ ዕቅድ በማቀድ እየሰራ አለመሆኑን እና የምላሽ ስራዎች እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ የሚያደርግ አለመሆኑን የክልሉ የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
  - በደቡብ ብ/ብ/ህዝቦች ክልል እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ያደረገ ምላሽ ለመስጠት በእቅድ ተይዞ የሚሰራ ቢሆንም በተግባር በተለይም ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ከማካተትና መረጃን ከመሰብሰብ አንፃር ችግሮች መኖራቸውን ከተደራሽነት አንፃርም ክፍተቶች እንዳሉና የምላሽ ስራዎች የመዘግየት ችግር እንዳለ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በተሟላ መልኩ ፓኬጆች ክልሉ ጋር የማይደርሱ መሆኑን የክልሉ የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
  - በኦሮሚያ ክልል የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራ እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች ቅድሚያ የሚሰጥ እንዲሆን እየተሰራ ቢሆንም ሙሉ ነው ለማለት እንደማያስችልና በአቅም

ውስንነት ምክንያት በተገቢው ሁኔታ ተደራሽ የማድረግ ችግሮች መኖራቸውን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

104. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ማካተትን (mainstreaming) ተከትሎ የሚታይ መሆኑን እና በአሁኑ የዕርዳታ ስርጭቱ እነዚህን ወገኖች ተደራሽ ማድረጉን በኮሚሽኑ የሴቶችና ወጣቶች ህጻናት ዳይሬክቶሬት ክትትል እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ ለተጠቀሱት የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ስለመድረጉ ክትትል የተደረገበት በሰነድ የተደገፈ ማስረጃ ተጠይቆ ለኦዲት ቡድኑ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ማቅረብ አልቻለም፡፡ እንዲሁም የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋምን በተመለከተ እንደገለፁት ስራው በዕርዳታ አቅርቦት ተሚልቶ መገኘት ያለመገኘት ጋር የተያያዘ ቢሆንም በየደረጃው ባለው መዋቅር ከላይ የተጠቀሱ የህብረተሰብ ክፍሎች ቅድሚያ እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ያለ መሆኑን የዕርዳታ አቅርቦት በተለያዩ ምክንያቶች በማይሟላበት ወቅት ቅድሚያ ለእነዚህ ወገኖች የመስጠት ሁኔታ የተለመደ መሆኑና ይህ በየጊዜው ከክልል ከሚመጣ ሪፖርት የሚታወቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

105. ይሁን እንጂ እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች በተሟላ መልኩ ተደራሽ ያደረገ የአደጋ ምላሽ ስለመሰጠቱ በየጊዜው ክትትል በማድረግ ችግሮች ስለመቀረፋቸው የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ ባልቀረበበት ሂደት እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ በአካል በመስክ ምልከታ ተጎጂዎች ጋር በመድረስ ምላሹ እየቀረበ አለመሆኑን ባረጋገጠበት ሁኔታ እንዲሁም በኮሚሽኑ ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ እንደተቀመጠው ኮሚሽኑ በአደጋ ክስተት ስራ ዙሪያ የሚወጡ ህጎች፣ መመሪያዎች፣ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች ውስጥ ለሴቶች፤ ለህፃናት፣ ለአረጋዊያን፣ ለአካል ጉዳተኞችና ኤች.አይቪ. ኤድስ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ ትኩረት ስለመሰጠታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊከታተል ይገባ የነበረ ቢሆንም ይህ ሁኔታ በሚፈለገው ደረጃ ስለመፈፀሙ ተጨባጭ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ በኮሚሽኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

106. በመሆኑም ኮሚሽኑ በአደጋ ክስተት ስራ ዙሪያ የሚወጡ ህጎች፣ መመሪያዎች፣ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች እንዲሁም የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎች ውስጥ ለሴቶች፤ ለህፃናት፣ ለአረጋዊያን፣ ለአካል ጉዳተኞችና ኤች.አይቪ. ኤድስ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ ትኩረት ስለመሰጠታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር ካልዘረጋ እና ተግባራዊ መሆናቸውን ካልተከታተለ እነዚህ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ለከፋ ጉዳት ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡

## ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር ስርዓትን ለመዘርጋትና ለመተግበር የሚያስችሉ የአቅም ግንባታን በተመለከተ፡-

107. ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር ስርዓትን ለመዘርጋትና ለመተግበር የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በየደረጃው ሊያከናውን ይገባል፡፡

108. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ቃለ-መጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

- በብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂዎች እንዲሁም ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ለአመራሩና ለፈፃሚዎች ግንዛቤ ለማዳበር ታቅዶ በበጀት እጥረት/አለመገኘት በሚል እንዳልተከናወነ ከኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዳይሬክቶሬት የ2010 ዓ.ም የሁለተኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖረት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ኮሚሽኑ በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና በአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ አሰራር ላይ በፌደራል፣ በክልል እንዲሁም በወረዳ ለሚገኙ እና በዚህ ስራ ለሚሳተፉ አካላት በየጊዜው ሥልጠና የመስጠት ስራ እንደሚከናወን እንዲሁም የተቋማትን አቅም በመገንባትና የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ምን መምሰል እንዳለበት ከየሴክተሩ ለሚመለከታቸው ከሃገር ባለፈ ዓለም አቀፍ ልምድ እንዲቀስሙ የማድረግ፣ በሃገር ውስጥ የአቅም ግንባታ ስራዎችን የማከናወን፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን የመስራት ተግባራት እና disaster mainstreaming guideline, hotspot classification guideline, መዘጋጀቱን የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- ኮሚሽኑ ለምክር ቤትና አስፈጻሚ አካላት ስለተቋሙና ስለአደጋ በቂ ግንዛቤ ማስጨበጥ እንደሚያስፈልግ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- የሀረሪ ክልል ኮሚሽኑ በተለያዩ ጊዜ ስልጠናዎችን ለክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ ባለሙያዎች የሰጠ ቢሆንም በቴክኖሎጂ ሶፍትዌሮች (softwares) ለምሳሌ ካት (CAT) በሚባል ሶፍትዌር ዙሪያ የሚሰጡት ስልጠናዎች ወደተግባር አለመቀየራቸው፣ በሳይንሱ መሰረት ስራዎችን ለመስራትና አሰራሮችን ለማዘመን ክፍተቶች እንዳሉ፣ እንዲሁም የተለያዩ ፕሮጀክቶች ዲዛይን ቢደረጉም ተግባራዊ አለመደረጉን፣ ለምሳሌ Woreda Net እና ስፒፍ የተሰኙ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ አለመደረጋቸውን እና ለክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ

የተሸከርካሪ ድጋፍ ባለመኖሩ ከሌሎች የክልል ሴክተር መ/ቤቶች ተሸከርካሪዎችን በመዋዋስ ለመስራት መገደዳቸውን፤

- እንዲሁም የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ስራዎችን በተሟላ መልኩ ለመተግበርና የማስፈፀም አቅምን ለመገንባት ኮሚሽኑ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅና እስከታች ድረስ በማውረድ አልፎ አልፎ ከሚሰጣቸው ስልጠናዎች ውጭ እየሰራ አለመሆኑንና ዕርዳታን ከማከፋፈል ውጭ በቴክኖሎጂ፣ በቁሳቁስና በዕውቀት ዙሪያ እስከታች ድረስ በመውረድ የሰራበት ሁኔታ አለመኖሩን፤በተጨማሪም በክልል ላሉ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የግንዛቤ ስራዎች መሰራት እንዳለበትና ስለአደጋ መከላከል ክልል ላይ እንደ አጀንዳ በቅንጅት እንዲሰራ ኮሚሽኑ ስራውን የማሰተዋወቅ ስራ ሊሰራ እንደሚገባ የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በሶማሌ ክልል በኮሚሽኑ በኩል የሚሰጡ የስልጠናና የአቅም ግንባታ ስራዎች ውስን መሆናቸውን፣ ከፍተኛ የሆነ የአቅም ግንባታ ስራዎች በወረዳና በዞኖች እንደሚያስፈልግና ለስራው አጋዥ የሆኑ የቴክኖሎጂ ድጋፍ እንደማይሰጣቸው የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በደቡብ ክልል ኮሚሽኑ በተለያየ ጊዜ ስልጠናዎች የሚሰጥ ቢሆንም ከፍተኛ የሆነ የሰው ሃይል ፍልሰት በመኖሩ ተከታታይነት ያለው ስልጠና ሊሰጥ እንደሚገባና ለኢንዱስትሪዎች መስፋፋት የሚመጥን አደረጃጀትና አቅም መፈጠር እንዳለበትና የተጠናከረ የሎጂስቲክ አቅም ሊገነባና ሊደራጅ እንደሚገባ፣ የአደጋ ምላሽ ስራዎችን ለመስራት የሚያሰችሉ ዘመናዊ አደረጃጀት፣ ገለልተኛና ሰብአዊ ድጋፍ የሚያደርግ የተጠናከረ የሎጂስቲክ ድጋፍ ሊኖረው እንዲሁም ማንነቱ የሚለይ አለባበስና ተሸከርካሪ ሊኖር እንደሚገባ፤
- እንዲሁም አሰራሩን ለማመዘን የአየር ንብረት ተለዋዋጭነት የፈጠረው ችግር ቀድሞ በመተንበይና ቴክኖሎጂን መሰረት በማድረግ ቢሰራና የወረዳ ኔት ተደራሽነትና አገልግሎት ተግበራዊ መደረግ እንዳለበትና ፌደራልን የተከተለ መዋቅር እንደ ክልል ሊዘረጋ እንደሚገባና ተጠሪነታቸውን ጠብቀው መደራጀት እንዳለባቸው እና የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ በሎጂስቲክስ የተሟላ እንዳልሆነና እንደ ክልል ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አቅምና አደረጃጀት እስከ ታች ድረስ በማጠናከርና የዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም አደጋን ለመተንበይ እንዲቻል ተቋማዊና የባለሞያ አቅም ሊጠናከር እንደሚገባ የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ኮሚሽኑ በተቋም ደረጃ የአቅም ግንባታ እና የምላሽ ስራው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የሚያደርገው ስራ በቂ አለመሆኑን እና የተሸከርካሪና

የኮምፒውተር አጥረት በመኖሩ ፈጣን ምላሽ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑን እንዲሁም በአስተዳደሩ የአቅም ግንባታ ስራ ቢሰራም በኮሚሽኑ በኩል የተደረገ ድጋፍ አለመኖሩን እና የሚጠበቅበትን ድጋፍ እያደረገ አለመሆኑን በተጨማሪም ኮሚሽኑ በመረጃ አያያዝ በአደጋ ስጋት ዙሪያ የአሰልጣኞች ስልጠና የተሰጣቸው ቢሆንም ስልጠናውን ለሁሉም የከተማ አስተዳደር ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ለማድረግ ከኮሚሽኑ የበጀት ድጋፍ ባለማድረጉ አለመከናወኑንና በኮሚሽኑ የሚሰጡት ስልጠናዎች ተደጋጋሚና ከሚፈልጓቸው ውጭ እንደሆኑ ገልፀዋል፣

- የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት 35 ሰራተኞች ለስልጠና የሰልጣኞች ዝርዝር እንዲላክ በቀን 05/05/2009 ዓ.ም ኮሚሽኑ ሰው ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ተጠይቆ የሰራተኞቹ ዝርዝር ከስልጠና ፍላጎታቸው ጋር ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ቢላክም ስልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑን ለማወቅ መቻሉ፣
- ኮሚሽኑ ለኦሮሚያ ክልል ከ(United Nations International Children’s Emergency Fund) UNICEF ጋር በመተባበር በተለይም በሶፍት ዌር በመታገዝ ለክልሉ ባለሙያዎች በመረጃ አያያዝ በድንገተኛ አደጋ ዙሪያ ስልጠና እየሰጠ ቢሆንም የሰለጠኑትን ያህል ተግባራዊ ለማድረግ የሰው ኃይል ፍልሰት በመኖሩና የማቀናጀት ስራ ባለመሰራቱ ተግባራዊ እንዳልሆነ የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

109. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በሁለተኛው በጀት ዓመት ሪፖርት ላይ ቢቀመጥም ቀደም ሲል ለክልል መዋቅር ሥልጠና የተሰጠ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ የሥርዓት ዝርጋታ ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑን፣ የአቅም ግንባታ የማያቋርጥ መሆኑን፣ የፋይናንስና ቴክኖሎጂ አቅም ውስንነት መኖሩንና ክልሎችም ባላቸው አቅም ኮምሽኑን ሳይጠብቁ መሥራት እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

110. የኮሚሽኑ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ሥርዓት ዝርጋታ ያልተከናወነ መሆኑ እንዲሁም ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ለአመራሩና ለፈፃሚዎች ግንዛቤ ለማዳበር ስልጠና የተሰጠ ቢሆንም በቴክኖሎጂ ሶፍትዌሮች (soft wares) ዙሪያ የሚሰጡት ስልጠናዎች ወደተግባር አለመቀየራቸውን በናሙና ተመርጠው በታዩ ክልሎችና ከተማ አስተዳደር የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

111. በመሆኑም በተከታታይ የአቅም ግንባታ ስራዎች ባለመከናወኑ በአደጋ ክስተት ስራ አመራር ዙሪያ ያለውን የአሰራር ቅልጥፍናና ዘመናዊነት እንዲሁም ተጎጂን ከከፋ ጉዳት የመታደግ ስራዎችን ያደናቅፋል፡፡

## ኮሚሽኑ በክልሎች መካከል በአደጋ ጊዜ ተደጋግፎና ተባብሮ የምላሽ ስራን ለመስራት የሚያስችል አሰራርን በተመለከተ፡-

112. ኮሚሽኑ በክልሎች መካከል በአደጋ ጊዜ ተደጋግፎና ተባብሮ የምላሽ ስራን ለመስራት የሚያስችል አሰራር ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

113. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ጉዳዩን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የኮሚሽኑ እና የክልል የስራ ሃላፊወች ጋር በተደረጉ ቃለ-መጠይቆች መሰረት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በሀረሪ ክልል የተፈናቀሉ ሰዎችን ከመቀበል ውጪ ችግሮችን ከሌሎች ክልሎች ጋር በጋራ ለመፍታት እንደ አደጋ መከላከል የተሰራበት ሁኔታ አለመኖሩንና ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖሩን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በሶማሌ ክልል ከሌሎች ክልሎች ጋር በስብሰባዎች ከመገናኘት ውጪ በአደጋ ጊዜ ተደጋግፎና ተባብሮ የምላሽ ስራን ለመስራት የሚያስችል አሰራር ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑንና ከክልሎች ጋር በእንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች የመደጋገፍ እና የልምድ ልውውጥ አስፈላጊ መሆኑን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በደቡብ ብ/ብ/ እና ህዝቦች ክልል ከሌሎች ክልሎች ጋር አደጋን ተባብሮ ምላሽ ለመስጠት ጅምሮች ቢኖሩም የተጠናከረ አለመሆኑን ስራው እስከ ህብረተሰቡ ድረስ ወርዶ እንዲሰራ ማድረግ እንደሚገባ የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በተለይ የጎርፍ ስጋትን አስመልክቶ ከአጎራባች ክልሎች ጋር የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ ቢኖርም የተጠናከረ ባለመሆኑ ምክንያት የሶማሌ ክልል ተፈናቃዮችን በለሊት በአይስዙ እየጫኑ አራግፈው መመለሳቸውን ማለትም ያለምንም መረጃ የተፈናቀሉትን ተረክቡን እንኳን ሳይባል ሜዳ ላይ ጥለዋቸው መሂዳቸውን የከተማ አስተዳደሩ የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በኦሮሚያ ክልል የአደጋ ምላሽ ስራ ሰብአዊነትን ተከትሎ የሚሰራ እንጂ ድንበርን መሰረት አድርጎ የሚሰራ ባለመሆኑ እንደ ክልል ተባብሮ እየተሰራ መሆኑን ነገር ግን ባለው የፖለቲካ ችግር ምክንያት አልፎ አልፎ እርዳታዎችን ለማድረስ ችግሮች የሚፈጠሩ መሆኑ እና ኮሚሽኑ በዚህ ዙሪያ አሰራር የሌለው መሆኑን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

114. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ይህ ሥራ በቀጣይነት የክልል-ክልል ትብብር ምን መልክ እንደሚኖረው በፌዴራልና በክልል መንግሥታት መካከል በመነጋገር የሚፈጸም መሆኑን፣ በአሁኑ ወቅት ግን ክልሎች በራሳቸው ተነሳሽነት እርስ በርስ የመደጋገፍ ሥራ እየሠሩ መሆኑን፤ ለምሳሌ፡- አፋር - ለሶማሌ፣ ሶማሌ - ለአፋር፣ ትግራይ፣ አማራ ኦሮሚያ ለሶማሌ ክልል ያደረጉት ድጋፍ የሚጠቀስ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

115. የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት ክልሎች አሰራሩ የተጠናከረ ካለመሆኑም በተጨማሪ አሰራሩን ተግባራዊ ለማድርግ የሚያስችል ሁኔታ ባልተዘረጋበት በኮሚሽኑ ኃላፊዎች የተሰጠውን ምላሽ መሉ በሙሉ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

116. ይህም ባለመሆኑ የተጎጂዎችን የጉዳት መጠን እንግልትና በአደጋ ውስጥ የመቆየት ጊዜን ሊያባብሰውና የሰብአዊነት ምላሹን በማስተጓጎል በተለይም አካልጉዳተኞች፣ ህፃናት፣ አረጋዊያን፣ ሴቶችና የተለየ ትኩረትና ክብካቤ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን የአደጋ ጊዜ ቆይታን በማራዘምና በማባባስ የከፋ ጉዳት ላይ ሊጥል ይችላል፡፡

## ኮሚሽኑ የመረጃ አስተዳደርና ኮሙኒኬሽን ስርዓት በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና በአደጋ ክስተት ስጋት ፕሮፋይል ላይ የተመሰረተ መሆኑን በተመለከተ፡-

117. ኮሚሽኑ የመረጃ አስተዳደርና ኮሚኒኬሽን ስርዓት በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና በአደጋ ክስተት ስጋት ፕሮፋይል ላይ የተመሰረተ ሊያደርግ ይገባል፡፡

118. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ቃለ-መጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

- የኮሚሽኑ የስራ አመራር መረጃ ስርዓት ዘመናዊ በቴክኖሎጂ የተደገፈና ተጠያቂነትን መሰረት ያደረገ አለመሆኑን ከኮሚሽኑ የ2010 ዓ.ም የውጤት ተኮር ዕቅድ ለማወቅ ተችሏል፡፡

119. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ኮሚሽኑ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስርዓትን ከመገንባት አኳያ የተሰሩት 347 የወረዳ አደጋ ተጋላጭነት ፕሮፋይል መረጃዎችን በባለሙያዎች በመተንተንና በማደራጀት በዌብሳይት ተለቀው ህብረተሰቡና አጋር ድርጅቶች እየተጠቀመባቸው እንደሆነና ቀሪ ወረዳዎች በመረጃ መረብ ለተጠቃሚው ለማሰራጨት

ዝግጅት የተደረገ ቢሆንም የኮሚሽኑ የቢሮ አደረጃጀት ችግር በመኖሩ እና የመረጃ ቋት የያዘው ሰርቨር በዋናው መ/ቤት በአንደኛው ሕንፃ ላይ በመገኘቱና በሥራ ክፍሉ የኔትወርክ የመስመር ዝርጋታ ባለመደረጉ እንዲሁም ከዋናው መ/ቤት ጋር ባለመገናኘቱ የተሰሩ የአደጋ ስጋት ቅነሳ መረጃዎችን በወቅቱ በዌብሳይት መልቀቅ ካለመቻሉም ሌላ በሰርቨር ላይ ያሉ መረጃዎችም ለማየትና ለመፈተሽ አለመቻሉን የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

120. በመሆኑም የኮሚሽኑ የመረጃ አስተዳደርና ኮሙኒኬሽን ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና በአደጋ ክስተት ስጋት ፕሮፋይል ላይ ያልተመሰረተ እንዲሁም ወቅታዊ እና ለሁሉም ተደራሽ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

## ኮሚሽኑ ከውጭ በዕርዳታ መልክና በግዥ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባቸውን ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውሉ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎችን በተመለከተ፡-

121. ኮሚሽኑ ከውጭ በዕርዳታ መልክና በግዥ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባቸውን ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውሉ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች በወቅቱ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

122. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የዶክመንት ክለሳዎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ መሰረት፡-

- የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በቀን 17 ነሀሴ 2009 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር Our Ref ዮሞአ/367/2009 በኮሚሽኑ ስም የተመዘገበ 44 ሺ ቶን ስንዴ ጭና ጅቡቲ ላይ በማራገፍ ላይ ያለች ሱዛን የተባለች መርከብ በመቋጠሪያ ጆንያ እጥረት ምክንያት ማራገፍ በሚጠበቅባት ያህል እያራገፈች አለመሆኑን በተለያዩ ጊዜያት ለኮሚሽኑ ያሳወቁ ቢሆንም ችግሩ ያልተፈታ መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአስቸኳይ የመቋጠሪያ ጆንያ በመላክ መርከቧ በወቅቱ አራግፋ ልትወጣ የምትችልበትን ሁኔታ ኮሚሽኑ እንዲያመቻች ያሳሰቡበት ሁኔታ መኖሩ ለማወቅ መቻሉ፣
- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በቀን 2 ነሐሴ 2009 ዓ.ም በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ለመሰንግስት ሂሳቦች ዳይሬክቶሬትና ለብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን በፃፈው ደብዳቤ ኮሚሽኑ በሐምሌ ወር 2009 ዓ.ም በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ታክሱ ብር 12 ሚሊዮን 118 ሺ 108.29 ብር ፣ በሐምሌ ወር 2009 ዓ.ም በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት 2 ሚሊዮን 758 ሺ 152.45 ብር እና በሐምሌ ወር 2009 ዓ.ም በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት 27 ሚሊዮን 110 ሺ 541.20 ብር

ከበጀታቸው ተቀናሽ የሚሆን የቅድሚያ አገልግሎት እንዲሰጣቸው በጠየቁት መሰረት ከቀረጥ ነፃ የሆነ አገልግሎት የተሰጣቸው በመሆኑና ምዝገባው የተከናወነ በመሆኑ በናንተም በኩል ምዝገባ እንዲደረግ በሚል ያሳወቀ መሆኑ ታውቀቋል፡፡

123. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በ2008 ዓ/ም ከፍተኛ የዕርዳታ ስንዴ በጅቡቲ ወደብ የገባበትና የጅንያ እጥረት ያጋጠመ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

124. በመሆኑም ኮሚሽኑ ከውጭ በዕርዳታ መልክና በግዥ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባቸውን ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውሉ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች በወቅቱ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ አለማድረጉ የሃብት ብክነትን ሊያስከትልና ስርጭትን በማዛባት ተረጂዎችን ችግር ላይ ሊጥል ይችላል፡፡

## ኮሚሽኑ የክምችት መጋዘኖች የሚገቡ፣ በክምችት ያሉና የሚወጡ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች የጥራት ደረጃን በተመለከተ፡-

125. ኮሚሽኑ የክምችት መጋዘኖች የሚገቡ/በክምችት ያሉና የሚወጡ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች የተቀመጠውን የጥራት ደረጃ ያሟሉ ስለመሆናቸው ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

126. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የዶክመንት ክለሳዎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልል እና የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎቸ ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ መሰረት፡-

- በሀረሪ በ2010 ዓ.ም ከኮሚሽኑ መጋዘኖች የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት ሳሙና በክልሉ ላሉ ተጠቃሚዎች የተሰራጨ በመሆኑ ክትትል በማድረግ ስርጭቱ እንዲቆምና ለሌላ ጥቅም እንዲውል መደረጉን እንዲሁም የጥራት ደረጃዎችን ለመፈተሽ የላብራቶሪና የባለሙያ አቅርቦት እንደሌላቸውና የሚመጣውን ቁሳቁስ ጥራቱን የጠበቀ አይደለም በሚል በሚመልሱበት ወቅት ጫናዎች እንደሚደርሱባቸውና የመፈተሽ አቅም፣ መሳሪያና ባለሙያ አስፈላጊ መሆኑን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በሶማሌ ክልል አልፎ አልፎ የጥራት ችግሮች እንዳሉ በተለይም የፕላስቲክ ድንኳኖች ጥራታቸው ዝቅተኛ በመሆኑ እየተሰነጣጠቁና እየተጎዱ መሆኑና አንድ ፕላስቲክ ለሶስት አመት እንዲያገለግል ታስቦ ቢሰራጭም በአጭር ጊዜ እየተበላሸ መሆኑን እንዲሁም

ቁሳቁሶች ሲመጡ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው ስለመሆናቸው ከማየት ባለፈ ናሙና ተወስዶ የማረጋገጥ ስራ እንደማይሰራ የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

- በደቡብ ብ/ብ/ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ቁሳቁሱ ከአንድ ማዕከል ስለሚመጣና የጥራትን ቁጥጥር የሚደረግበት ሁኔታ ስላለ በሚል ክልሉ የቁጥጥርና ፍተሻ ስራ እንደማይሰራና ጥራትን ለመከታተል የተመደበ ባለሙያ አለመኖሩንና በመዋቅር ውስጥ ያልተካተተ መሆኑን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- በደቡብ ብ/ብ/ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በጌዲኦ ዞን ለተጎጂ ማህበረሰብ ምግብ ነክ የሆኑ ቁሳቁሶችን ህብረተሰቡ ራሱ ባመጣው መለኪያ(ጆግ) የማከፋፈል ስራ መኖሩና ትክክል ነው ብለው እንደማያምኑ እንዲሁም አልፎ አልፎ ነቀዝ የበላው እህል የሚመጣ መሆኑና አማራጭ ስለሌለ እንዲሰራጭ መደረጉንና የጥራት ቁጥጥር የሚደረግበት አግባብ አለመኖሩን የዞኑ የአደጋ ስጋት ቢሮ  የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በክምችት ያሉ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ጥራትና ደህንነት ለማረጋገጥ ፍተሻና ክትትል በማድረግ ችግር ሲኖር መጋዘኖችን በማሸግ የማከም ስራ የሚሰራ ቢሆንም አልፎ አልፎ የመድኃኒት እጥረት እንደሚያጋጥማቸው፣ በኮሚሽኑ በኩል ባለሙያ ተልኮ በየጊዜው ቁጥጥር እየተደረገ ባለመሆኑና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ አንድ ባለሙያ ብቻ በመኖሩ ኮሚቴ በማዋቀር የጥራትና የደህንነት ቁጥጥር እያደረጉ መሆኑን የቅርንጫፉ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጥራትና ቁጥጥር ባለሙያና የጥራት ቁጥጥር መስፈርት በመኖሩ ቁሳቁሶች ሲገቡና ሲወጡ ፍተሻ እንደሚደረግና መጋዘኖች ውስጥ ተባዮች በሚታዩበት ወቅት የተባይ መቆጣጠሪያ የሚጠቀሙ መሆኑና ከተስማሚነትና ምዘና ድርጅት ጋር አብረው እየሰሩ ቢሆንም ለብልሽት የተዳረጉ ቁሳቁሶችን ለማከም የሚያገለግል የተባይ መቆጣጠሪያ መድኃኒት ኮሚሽኑ በወቅቱ ገዝቶ የማያቀርብ በመሆኑና በጥራት ቁጥጥር ባለሙያዎች የክህሎት ክፍተት በመኖሩ በስራው ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ መሆኑ እና ከ2009 ዓ.ም በፊት የጥራት ቁጥጥር ማድረጊያ መሳሪያ እንዳልነበረ በቅርንጫፉ ካሉት መጋዘኖች መካከል አንዳንዶቹ ጣራቸው እያፈሰሰ በመሆኑ ለእቃዎች ብልሽት መንስኤ እየሆነ መምጣቱን የቅርንጫፉ ስራ ኃላፊዎች የገለፁ መሆኑን እና የኦዲት ቡድኑም በመስክ ምልከታ ወቅት አረጋግጧል፡፡
- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተበላሹ ቁሳቁሶችን በመለየት ለኮሚሽኑ እንዲወገዱ ጥያቄ አቅርበው ምላሽ አለመሰጠቱን የቅርንጫፉ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

- በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚሰራጩ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ጥራት ለመፈተሽ ልማዳዊ ከሆነ የማረጋገጥ ሂደት በስተቀር የተለየ ዘመናዊ አሰራር አለመኖሩን እንዲሁም እርጥበትና ተባይ መመርመሪያ መሳሪያዎች አለመኖራቸውን የከተማ አስተዳደሩ የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት የአየሩ ሁኔታ ሞቃት በመሆኑ በመጋዘን ውስጥ ያሉ እህሎች በተባይ እየተጠቁ በመሆኑ የእህል ማከሚያ መድኃኒት (ፎስቶክሲን በጣሳ -60 እና አክትሊክ በጣሳ 6) ግዥ ተፈፅሞ እንዲላክላቸው በቀን 24/09/2009 ዓ.ም የኮሚሽኑ ሎጂስቲክስ ዳይሮክቶሬት ቢጠየቅም ምላሽ አለመሰጠቱን በኦዲት ወቅት ከተከለሰ ማስረጃ ታውቋል፡፡

127. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በኮሚሽኑ ዋና መ/ቤት የጥራት ቁጥጥር ባለሙያ ያለው በማዕከላዊ መጋዘን መሆኑና በቀጣይ በአዲሱ ድርጅታዊ መዋቅር በኮሚሽኑ እንዲኖር የሚደረግ መሆኑን ነገር ግን የሌሎች ተቋማት ባለሙያዎች ለምሳሌ የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ክምችት ኤጀንሲና የተስማሚነት ምዘና የመጠቀም ልምዱ ያለ መሆኑን እንዲሁም የተባይ መቆጣጠሪያ መድኃኒት በጀት በኮሚሽኑ እያለ መድኃኒቶችን በገበያ ላይ ማግኘት ባለመቻሉ ምክንያት እንደ አማራጭ የዓለም ምግብ ፕሮግራም በመጠቀም እየተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

128. በተጨማሪም በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጡት አስተያየት በኮሚሽኑ የጥራት ተቆጣጣሪ አደረጃጀት ተግባር ላይ መዋሉን የገለፁ ሲሆን በነባራዊ ሁኔታ ከሰጡት ምላሽ የሚቃረንና በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

129. ይሁን እንጂ የሌሎች ተቋማት ባለሙያዎችን ለመጠቀም የተፈራረሙት የጋራ መግባቢያ ሰነድ ወይም የአሰራር ስርዓት በሌለበት ሁኔታና የተባይ መቆጣጠሪያ ገበያ ላይ በሚገኝበት ወቅት በመግዛት ወይም በአስመጪዎች በኩል በማስመጣት ለመጠባበቂያ ባልተቀመጠበት ሁኔታ የዓለም ምግብ ፕሪግራምን ብቻ በመተማመን በሚሰራበት ሂደት ምላሹን ለመቀበል ያዳግታል፡፡

130. በመሆኑም ኮሚሽኑ ወደ ክምችት መጋዘኖች የሚገቡ/በክምችት ያሉና የሚወጡ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች የተቀመጠውን የጥራት ደረጃ ያሚሉ ስለመሆናቸው ባለመከታተሉ እና ባለመቆጣጠሩ ጥራቱን እና ደረጃውን የጠበቀ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ለተረጂዎች እንዳይደርስ እና የሀገር ሀብት ለብክነት እንዲጋለጥ እንዲሁም በህብረተሰብ ጤና ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡

## የኮሚሽኑ ቅርጫፍ ጽ/ቤቶችን

## (ማዕከላዊ መጋዘኖችን) በተመለከተ፡-

131. ኮሚሽኑ ቅርጫፍ ጽ/ቤቶችን (ማዕከላዊ መጋዘኖችን) ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል አደረጃጀት እና የግባት አቅርቦት በሚሟላት ባግባቡ ሊመራ፣ሊያስተባብርና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

132. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ በተካሄዱ የዶክመንት ክለሳዎች ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረጉ ቃለመጠይቆች እና የመስክ ምልከታዎች መሰረት የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡-

- የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነቱን ለመወጣት የሰው ሀይል ዕጥረት መኖሩን እንዲሁም ለቅርንጫፉ ተግባና ኃላፊነት ተለይቶ ያልወረደለት መሆኑና በተደጋጋሚ በቃል ቢጠይቁም ምላሽ ያላገኙ መሆኑና የሰራተኞችና የጽ/ቤቱ የስራ መዘርዝር ባለመኖሩ ስራዎች በልምድ ብቻ ለመስራት በመገደዳቸው ሰራተኞችን በስራቸው ተጠያቂ ለማድረግና ኃላፊነት ለመስጠትና ለመቀበል መቸገራቸውን የቅርንጫፉ የሥራ ኃላፊዎች ለ ኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- እንዲሁም በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ሰራተኞች በአንድ ወር ውስጥ ከመደበኛው የስራ ሰዓት ውጭ 64 ሰዓት የሚሰሩ ቢሆንም የትርፍ ጊዜ ክፍያ የሚከፈለው የ32 ሰዓት ብቻ መሆኑ ያለምንም ህግና መመሪያ እንዲሁም ህጋዊ ውሳኔ 32 ሰዓት በነፃ እንዲሰሩ የተገደዱ መሆኑን፣ የ44 ሰዓት የትርፍ ሰዓት ክፍያ ይከፈል የነበረ ቢሆንም የሰራተኞች ደሞዝ አድጓል በሚል ምክንያት ወደ 32 ሰዓት ዝቅ እንዲል መደረጉ ህጋዊ የሆነ የአሰራር መሰረት የሌለው መሆኑና ይህ በመሆኑ ሰራተኞች የሚከፈላቸውን የ32 ሰዓት ስራ ከሰሩ በኋላ በተቀረው 32 ሰዓት ጊዜ ውስጥ በተለያየ ሰበብ ስራቸው ላይ እንዳይገኙ ማድረጉን እንዲሁም የሰራተኞች የደንብ ልብስ በወቅቱ የማይገዛ መሆኑ፣ የተለያዩ የመገልገያ ቁሳቁሶችና ተሽከርካሪዎች የማይቀርቡና ያሉትም ያረጁና ለመስክ ስራዎች የማይሆኑ በመሆኑ በስራቸው ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ መሆኑን የቅርንጫፉ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- ከዚህ በተጨማሪ የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በየጊዜው የስልጠና ጥያቄዎች፣ የተለያዩ የግዢ ጥያቄዎችን (ሚዛን፣ የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር) ለኮሚሽኑ ያቀረበ ቢሆንም እስካሁን ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ትኩረት ባለመስጠቱ ምላሽ አለማግኘቱ በተጨማሪም በኮሚሽኑ ዋና

መ/ቤት የሚሰራበት የሰራተኛ የደሞዝ ፔሮል አሰራር በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሰራተኞች ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑን የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

- እንዲሁም በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መጋዘኖች አካባቢ ያለው የጭነት ማውረጃና ማራገፊያ ሜዳ ከፍተኛ አቧራ ያለበት በመሆኑ እና መጋዘኖቹ ወደ ጅቡቲ የሚጓጓዙ ከባድ ተሽከርካሪዎች መንገድ ዳር በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የአቧራ ብናኝ ወደመጋዘኑ ውስጥ ዘልቆ በመግባት የተከማቹ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ለብልሽት እያጋለጠና የጭነት ስራውን እየረበሸ መሆኑን፣ እንዲሁም ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች የሚከማቹበት መጋዘን ውስጥ ለረጅም ዓመታት የተከማቹና አገልግሎት የማይሰጡ ጀሪካኖች፣የፕላስቲክ ኩባያዎች፣ የተለያዩ ቧንቧዎች፣ ልዩ ልዩ ብረታብረቶች፣ ፕሪንተሮች ቦታ ማጣበባቸውንና ሌሎች ቁሳቁሶችን ለብልሽት እያጋለጡ መሆኑና ኮሚሽኑ በመጋዘኑ ያሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ቆጠራ በማከናወንና በመለየት ጥቅም ላይ እንዲውሉና እንዲወገዱ ያላደረገ መሆኑ እንዲሁም የመጋዘኖች ጣራ ዝናብ የሚያፈስ በመሆኑ በክምችት ላይ ያሉ ቁሳቁሶችን ለብልሽት እየዳረገ እንደሚገኝና ጥገና ያልተደረገለት መሆኑን በተጨማሪም ለረጅም ጊዜ የተቀመጡና አገልግሎት የማይሰጡ የተለያዩ ተሽከርካሪዎች አለመወገዳቸውና ብርድልብስና የፕላስቲክ ጆኮች ከመጠን በላይ በመሆናቸውና ለረጅም ዓመት የተከማቹ በመሆናቸው ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑን የቅርንጫፉ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡ የኦዲት ቡድኑም በመስክ ምልከታ ወቅት የተገለፀውን አረጋግጧል፡፡
- የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ትልቁ መጋዘን ፕላሰቲክ ቆርቆሮ በተለይም በክረምት ወቅት እያፈሰሰ ስላሰቸገረ ቆርቆሮው በአስቸኳይ እንዲቀየር በቀን 23/12/2009 ዓ.ም ለኮሚሽኑ ሎጂስቲክስ ዳይሬክቶሬት ቢጠየቅም ምንም አይነት ምላሽ አለመሰጠቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የመጋዘን እና ቢሮ አካባቢ ሜዳው በከፍተኛ ሁኔታ ለአቧራ የተጋለጠ በመሆኑ ከጤና አኳያ ችግር ከማስከተሉም በላይ መጋዘን ውስጥ ባሉ እህሎች ላይ ብልሽት በመፍጠሩ የኮብልስቶን ንጣፍ እንዲሰራ እንዲሁም ለወዛደሮች የሚሆን መፀዳጃ ቤት፤የሻወር ቤት በርና ጣራ እንዲሰራ በቀን 03/07/2010 ዓ.ም በተደጋጋሚ ለኮሚሽኑ ጽ/ቤት ጥያቄ ቢቀርብም እስካሁን ድረስ አለመሰራቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት የእቃ ገቢና ወጪ ማድረጊያ ደረሰኝ ከዚህ በፊት በግብርና ሚኒስቴር ስር በነበረበት ወቅት ባሳተመው የገቢና ወጪ ደረሰኝ እየተጠቀመ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ባደረገው ምልከታና የማስረጃዎች ክለሳ ለማወቅ መቻሉ፣
- የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካሉት ቅርንጫፎች ትልቁ ሲሆን በአምስት ክልሎች ቁሳቁሶችን የማሰራጨት የማከማቸት ስራ እየሰራ መሆኑ እና በኮሚሽኑ ትዕዛዝና በክልሎች ጥያቄ

መሰረት የማሰራጨት ስራ እያከናወነ ቢሆንም ኃላፊነቱን ለመወጣት በመዋቅሩ ከተመደበው የሰው ሀይል ያነሰ ሰራተኛ በመኖሩ በስራው እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ መሆኑን የቅርንጫፉ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

- የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኮሚሽኑ የተባይ መከላከያና ማጥፊያ መድኃኒቶች በጊዜው የማይቀርቡ በመሆኑ የተባይ መከላከያና ማጥፊያ መድኃኒት ከዓለም የምግብ ፕሮግራም (WFP) እርዳታ በመጠየቅ እየሰሩ ቢሆንም ችግሩ እስካሁን እየቀጠለ መሆኑንና WFP መድኃኒቱን ባይሰጥ ብዙ ብልሽትና ሀገራዊ የኢኮኖሚ ሃብት ክስረት ሊያጋጥም እንደሚችል የቅርንጫፉ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

133. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያለው የንብረት አያያዝ ትኩረት የሚያስፈልግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

- በዚህ ዙሪያ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ፡- በማዕከላዊ መጋዘኖች ቀደም ሲል ከነበረው አሠራር የተለወጠ ሥራ ስለሌለና ማዕከላዊ መጋዘኖቹ ለሎጂስቲክ ዳይሬክቶሬት ተጠሪ ሲሆኑ የፋይናንስና የሰው ኃይል አመራር በኮሚሽኑ በጀትና ፋይናንስና በሰው ሃብት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት የሚመራ መሆኑን እንዲሁም የትርፍ ሰዓት ክፍያ ቋሚ ሳይሆን የሥራ ብዛትንና ውስብስብነትን ተከትሎ የሚፈጸም መሆኑንና አጠቃላይ የማዕከላዊ መጋዘኖችን አቅም ለማሳደግና የተሟሉ ግብዓቶችን ለሟሟላት እየተሠራ ያለ መሆኑን ገልጸዋል::

134. በመሆኑም ኮሚሽኑ ቅርጫፍ ጽ/ቤቶችን (ማዕከላዊ መጋዘኖችን) ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል አደረጃጀት እና የግብአት አቅርቦት በሟሟላት ባግባቡ ባለመምራቱ ባለማስተባበሩና ባለመቆጣጠሩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሙሉ አቅማቸው በአደጋዎች ስፋትና ደረጃ ልክ የምላሽ ስራውን ለማቀላጠፍ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ሊያጓትተው፣ ሊያስተጓጉለው እና ውጤታማ እንዳይሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ኮሚሽኑ የክምችትና የስርጭት መመሪያ

## በማውጣት ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡-

135. ኮሚሽኑ የክምችትና የስርጭት መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ሊያደርግ እና በየደረጃው ተፈፃሚ ስለመሆኑ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

136. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የዶከመንት ክለሳወች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የኮሚሽኑ እና የ ክልል የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ እና የመስክ ምልከታ መሰረት የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡-

- ለእለት እርዳታ እንዲውል ለክልሎች የሚላክ ምግብ በአንዳንድ ቦታዎች በወቅቱ ያለመከፋፈል ችግር መኖሩን ከኮሚሽኑ የ2009 ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ታውቋል፡፡
- በሶማሌ ክልል እርዳታዎች በወቅቱ የማይደርሱ መሆኑን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- በደቡብ ብ/በ/ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የአደጋ ምላሽ ትራንስፖርተሮች ያለ አቅማቸው ጨረታ በማሸነፍ በተፈለገው ጊዜ የማይደርስበት ሁኔታ እየተፈጠረ እንደሚገኝና ችግሮችን ለመፍታት ለኮሚሽኑ በደብዳቤ አሳውቀው የማያውቁ ቢሆንም ከትራንስፖርተሮች ጋር በመነጋገር የሚፈታበት አግባብ መኖሩን የክልሉ አደጋ ስጋት የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በደቡብ ብ/በ/ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የጌዴኦ ዞን የዕርዳታ ቁሳቁሶችን በተቀመጠው መጠን መሰረት ቆጥሮ የመረከብ ሁኔታ ደካማ መሆኑንና በ2010 ዓ.ም ለዞኑ የመጣው በቆሎ ከ100 ኪ.ግ የጎደለና ለተረጂዎች ለማሰራጨት ልኬቱ እኩልና በተቀመጠው ልክ ገቢ ያልተደረገ መሆኑንና እንዲሁም የቁሳቁስ አቅርቦት ችግር ከፍተኛ መሆኑ፤የምግብ አቅርቦቶች ወቅቱን/በየወሩ ጠብቆ እየቀረቡ አለመሆኑንና አልሚ ምግብ፤ጥራጥሬና ዘይት አሟልቶ እየተላከ እንዳልሆነ የዞኑ የአደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ገቢና ወጪ የሚደረጉ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን መጠን ለማወቅ የሚያስችል የምድር ሚዛን የማይጠቀም መሆኑና ምዝገባ ብቻ በማከናወን ከኮሚሽኑ በሚመጡ ማዘዣዎች መሰረት ወጪ በማድረግ እየተሰራ መሆኑን እንዲሁም አስፈላጊውን የጨረታ ሰነድ ላሟሉ አጓጓዥ ድርጅቶች ቁሳቁሶችን ቆጥሮ በማስረከብ ወደ ክልሎች እንዲጫኑ የሚያደርግ ቢሆንም በአጓጓዥ ሹፌሮችና ክልል ላይ ካሉ የመጋዘን ተቆጣጠሪዎች(store keeper) መካከል ያለውን አሰራር ቁጥጥር የሚደረግበት አሰራር አለመኖሩንና ክልሎች ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው የቅርንጫፉ የስራ ኃለፊዎች ገልፀዋል፡፡
- እንዲሁም ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኮሚሽኑ በስርጭትና ክምችት መመሪያ መሰረት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን በግንባር በመሄድ ክትትል እነደማያደርግና በስልክ ግንኙነት ብቻ የኦፕሬሽን ስራዎችን እንዲሰሩ እንደሚያደርግና ክትትል ባለማድረጉ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ክፍተት ለይቶ እልባት ለመስጠት እንዳልተቻለና ለስርጭትና ክምችት ስራው አስፈላጊ የሆኑ የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር ግዥ ባለመፈፀሙ የጭነት ስራ የሚሰሩ የጉልበት ሰራተኞች የሚጠጡትና የሚታጠቡበት ውሃ በማጣታቸው ስራ የሚያቆሙበት

ሁኔታ በመኖሩ በስርጭቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እየፈጠረ እንደሚገኝ የቅርንጫፉ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

- ከ7ኛ ዙር ጀምሮ ለኦሮሚያና ለአማራ ክልል ከተላከው ውስጥ 7749.8 ሜ/ቶን ኦሮሚያ 6826 ሜ/ቶን አማራ ክልል በድምሩ 14575.8 ደርሶ ለተረጂው እንዳልተከፋፈለ ክልሎቹ ሪፖርት ሲያቀርቡ 617.3 ሜ/ቶን ደግሞ ኦሮሚያ ክልል እንደጠፋ ሪፖርት የቀረበ መሆኑን በኮሚሽኑ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ዳይሬክቶሬት የ2009 ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ታውቋል፡፡
- በደቡብ ብ/በ/ህዝቦች ክልላዊ መንግስት አስቸኳይ ጊዜ የምግብ አቅርቦት እና ስርጭት ሁኔታን በተመለከተ በሲዳማ ዞን ከጥር እስከ ሰኔ 2010 ዓ.ም ድረስ የዕለት ዕርዳታ እንዲረዱ ለተፈቀዳለቸው በ11 ወረዳዎች ለሚገኙ 150,735 ተረጂዎች እስካሁን ድረስ እርዳታ ባለመቅረቡ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወገኖች በችግር ላይ መሆናቸውን ከሰኔ 19-25/2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ ከክልሉ ለኮሚሽኑ ከተላከ ሪፖርት ለመመልከት ተችሏል፡፡
- በእርዳታ አቅርቦትና ስርጭት አፈፃፀምን በተመለከተ የተላከውን የእለት ዕርዳታ ድጋፍ በአማራ ክልል አንዳንድ ወረዳዎች ላይ ሙሉ በሙሉ ከሰኔ 19-25/2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ ተሰራጭቶ ያላለቀ መሆኑን ከክልሉ ለኮሚሽኑ ከተላከ ሪፖርት ለመመለከት ተችሏል፡፡
- በኦሮሚያ ክልል የኮሞዲቲ ማኔጅመንት መመሪያ (guideline) ከመጠቀም ውጭ ከኮሚሽኑ የወረደ የስርጭትና የክምችት መመሪያ እንደሌለ የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

137. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ፡-የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ችግር ግዙፍ ስለሆነ መፍትሔ ለመስጠት ከአጋር አካላት ጋር ምክክር እየተደረገ መሆኑ በተለይም የዓለም ምግብ ፕሮግራም እንዲያሟላ ምክክር እየተደረገ መሆኑ፤

- የዕርዳታ ስርጭት ሙሉ ለሙሉ የክልሎች ኃላፊነት መሆኑንና ኮሚሽኑ የመከታተል ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ለዚህም በየጊዜው ክልሎችን በተለያዩ መንገዶች በመጠቀም የማረጋገጥ ሥራ እየሠራ መሆኑን፤
- ኮሚሽኑ ስራዎች በሚደራረቡበት ወቅት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው አካባቢዎች ቅድሚያ ስለሚሰጥ አልፎ አልፎ ክፍተቶች ሊኖሩ እንደምችሉ ገልፀዋል፡

138. ይሁን እንጂ የስርጭት መመሪያ በሌለበት ሁኔታና በስርጭቱ ዙሪያ ስለሚስተዋሉ ክፍተቶች ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ባልተዘረጋበት ሁኔታ በኮሚሽኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

139. በመሆኑም ኮሚሽኑ የክምችትና የስርጭት መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ባለማድረጉና በየደረጃው ተፈፃሚ ስለመሆኑ ባለመከታተሉና ባለቆጣጠሩ በእርዳታ ቁሳቁሶች ስርጭት ላይ ተፅዕኖ ከማሳደሩም በተጨማሪ ለብልሹ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

## ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውል ሀብትን በተመለከተ፡-

140. ኮሚሽኑ ለምላሽ ስራ የሚውል መጠባበቂያ በጀት ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች እንዲሁም  በመንግስት የሚመደብና በእርዳታ የሚሰበሰብ ሀብት በአግባቡ ለምላሽ ስራ ጥቅም ላይ መዋሉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

141. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የዶክመንት ክለሳዎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የኮሚሽኑ እና የክልል የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረጉ ቃለ-መጠይቆች መሰረት የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡-

- በኮሚሽኑ የተሟላ የበጀትና ፋይናንስ አሰራርና አጠቃቀም አለመኖሩን ከኮሚሽኑ የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የሶስት ዓመታት (2010-2012) የውጤት ተኮር ዕቅድ አፈፃፀም ታውቋል፡፡
- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በየአመቱ ከሚከናወነው የንብረት ቆጠራ ውጭ የኦዲት ስራ የማይከናወን መሆኑን እንዲሁም በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ መዋቅር የውስጥ ቁጥጥርና ኦዲት ዘርፍ ቢኖርም እስካሁን ምደባ ያልተደረገለት መሆኑና በየጊዜው ከትትልና ኦዲት የሚያደርግ አካል አለመኖሩ ከስራው ብዛትና ስፋት እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ ሀብት የሚንቀሳቀስበት ከመሆኑ አንፃር የውስጥ ቁጥጥርና ኦዲት ማድረግ አስፈላጊ ቢሆንም አለመደረጉ፣ እንዲሁም አመታትን ጠብቆ ኦዲት ማድረግ አግባብ ባለመሆኑ ችግሩ ሊቀረፍ እንደሚገባ የቅርንጫፉ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በየዓመቱ ቆጠራ የሚያከናውን ቢሆንም ኦዲት የማይደረግ መሆኑና ኦዲት ባለመከናወኑ የሚፈጠሩ ችግሮችን እና ስተቶችን በወቅቱ ማስተካከል እንዲሁም ግንዛቤ እንዲወስድ አለማድረጉንና ከፍተኛ የሆነ ችግርና ስጋት ያለበት ስራ በመሆኑ ኦዲት መደረግና የውስጥ ኦዲት አስፈላጊ መሆኑን  የቅርንጫፉ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

142. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት ምላሽ፡-

- የፋይናንስና ግዥ ሥርዓቱ በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደርና የግዥ መመሪያ የሚፈፀም በመሆኑ ኮሚሽኑ የተለየ የፋይናንስ አሠራር የሌለው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

○ በውስጥ ኦዲትና በዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኦዲት የሚደረግ መሆኑ፤

○ የለጋሾችን ስምምነት ተከትሎ እየተፈጸመ የሚገኝ መሆኑ ገልፀዋል፡

143. ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ ለምላሽ ስራ የሚውል መጠባበቂያ በጀት፣ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ እንዲሁም በተጨማሪ በመንግስት የሚመደብና በዕርዳታ የሚሰበሰብ ሀብት በአግባቡ ለምላሽ ስራው ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የሚያስችል ግልፅ የሆነ አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ እያደረገ ስለመሆኑ የሚገልፅ የሰነድና የኦዲት ግኝት መስተካከያ እርምጃዎችን የሚያመላክት ሰነድ ለኦዲት ቡድኑ ባልቀረበበት ሁኔታ እና በመስክ ምልከታ ወቅት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ኦዲት ተደርገው እንደማያውቁ በገለፁበት ሁኔታ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

144. በመሆኑም ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ የሚውል ሀብት ባግባቡ ክትትል እና ቁጥጥር አለማድረጉ ሀብት ላይ ጉዳትና ጉድለት በማስከተል ላልተፈለገ ወጪና ብክነት እንዲሁም ለብልሹ አሰራር ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

## ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይልን መነሻ ያደረገ የመጠባበቂያ ዕቅድ በየጊዜው በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡-

145. ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይልን መነሻ ያደረገ የመጠባበቂያ ዕቅድ በየጊዜው ሊያዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

146. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የዶክመንት ክለሳወች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ መሰረት፡-

○ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይልን መነሻ በማድረግ ቦታ ተኮር ዘርፈ ብዙ የአደጋ መንስኤ ሴክተር ተኮር የአደጋ ስጋት ቅነሳ ስርዓት እንዲዘረጋ እና እንዲጠናከር ለማድረግ ታቅዶ አለመከናወኑን እንዲሁም የአደጋ ስጋት ፕሮፋይልን መነሻ በማድረግ የአደጋ መንስኤና ተያያዥ የአደጋ ተፅዕኖን ለማቃለልና ለማስወገድ የኑሮ መሰረት የሆኑ የገቢ ምንጮችን ለመጠበቅ በቅድመ አደጋ ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመለየት ታቅዶ አለመከናወኑን ከኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዳይሬክቶሬት የ2009 ዓ.ም የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ተገልፀዋል፡፡

○ የአደጋ ስጋት ቅነሳና የወረዳ ፕሮፋይል መረጃ የተሰበሰበላቸው ወረዳዎች በአብዛኛው የሴፍትኔት ወረዳዎች ስለሆኑና ድጋፍ የሚሰጡ አጋር ድርጅቶች ትኩረታቸው በሴፍትኔት ወረዳዎች በመሆኑ ከሴፍትኔት ውጪ የሆኑ ወረዳዎች መረጃ ለመሰብሰብና የአደጋ ስጋት

ቅነሳ ስራ ለመስራት አለመቻሉን ከአደጋ ስጋት ቅነሳ ዳይሬክቶሬት የ2010 በጀት ዓመት አፈፃፀም ሪፖርት ታውቋል፡፡

147. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ የሴፍቲኔት ወረዳዎች ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና እጦት ያለባቸው ወረዳዎች በመሆናቸው ቅድሚያ ስለሚሰጥ የተገኘውን ሀብት ለእነዚህ ወረዳዎች ማዋሉ አስፈላጊ በመሆኑና ተግባራዊ ስለመደረጉ ገልፀዋል፡፡

148. በዚህ ዙሪያ ከአደጋ ስጋት ቅነሳ ዳይሬክቶሬት መረጃ ማግኘት ይቻላል ቢባልም ኮሚሽኑ በአደጋ ስጋት ፕሮፋይል መነሻነት መጠባበቂያ ዕቅድ በማቀድ ተግባራዊ ስለማድረጉ መረጃ ተጠይቆ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ ሲሆን የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ክለሳ እንደማይደረግና በሁሉም ወረዳዎችና ክልሎች ላይ አለመሰራቱን በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎችና ከኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

149. በመሆኑም የአደጋ ስጋት ፕሮፋይልን መነሻ በማድረግ ዕቅዶች ባለመታቀዳቸው የአደጋ ምላሽ አሰጣጡን ድንገታዊና በዘፈቀደ መልኩ እንዲሆን የሚያስገድድና በመረጃ ላይ ያልተመረኮዘ የምላሽ አሰጣጥ በማስፈን ላልተፈለገ ወጪና ብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡

## ኮሚሽኑ ቅፅበታዊ ለሆኑ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ቀልጣፋ የሆነ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡-

150. ኮሚሽኑ ቅፅበታዊ ለሆኑ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ቀልጣፋ የሆነ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

151. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅትበተካሄዱ የዶክመንት ክለሳዎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ እና የመስክ ምልከታ መሰረት ኮሚሽኑ ቅፅበታዊ ለሆኑ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ቀልጣፋ የሆነ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ እንዳላደረገ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ቅፅበታዊ ለሆኑ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልጉ ዋናዋና ጉዳዮች መካከል፡- ቅፅበታዊ አደጋዎች ሲያጋጥሙ ወዲያውኑ እርዳታውን በማቅረብ ጊዜያዊ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ማዕከል እንዲቋቋም ማድረግ፣ ከሌሎች የስራ ክፍሎችና አካላት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ፣ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና አስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማዕከል በአስፈላጊ የኮምንኬሽን መሳሪያዎች እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ግብአቶች መደራጀቱን በመከታተል ማረጋገጥ እንዲሁም ቅፅበታዊ አደጋዎች ሲከሰቱ በሚመለከታቸው መሪ ሴክተር መስሪቤቶችን እና በሌሎች ባለድርሻ

አካላት የተቀናጀ አስቸኳይ ምላሽ እንዲሰጥ ማስተባበር እንዳለበት የሚሉት የሚጠቀሱ ሲሆን በጉዳዩ ዙሪያ የሚከተሉት ዋናዋና ጉዳዮች ታይተዋል፣

- የኦሮሚያ፣የደቡብብ/ብ/ህ እና የሶማሌ ክልል የአደጋ ስጋት እና መልሶ ማቋቋም ቅፅበታዊ ለሆኑ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ቀልጣፋ የሆነ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ እንዳልተደረገ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- እንዲሁም በሀረሪ ክልል ቅፅበታዊ አደጋን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት አሰራር እንደሌለ የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በተመሳሳይ መልኩ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቅጽበታዊ አደጋ ሲያጋጥም ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የተዘረጋ አሰራር አለመኖሩን አልፎ አልፎ የከተማ አስተዳደሩ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ጽ/ቤቱ ብቻውን እየሰራ መሆኑን የአሰተዳደሩ የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለቅፅበታዊ አደጋ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል በቂ የሰው ኃይል አለመኖሩን የቅርንጫፉ የስራ ኃፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ በኮሚሽኑ ባካሄደው የዶክመንት ክለሳ ለእርዳታ አቅርቦት ስራ በአንዳንድ አካባቢዎች በመንገድ መበላሸት ምክንያት እርዳታው በወቅቱ እንዳይደርስ እንቅፋት መሆኑን ከኮሚሽኑ የ2009 ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ መቻሉ እንዲሁም የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች በመበራከታቸው ችግር ወደ ተከሰተባቸው ቦታዎች ለመድረስ የመንገድ ችግር በመኖሩ በፈጣን ምላሽ አሰጣጥ ላይ ችግር ማስከተሉን ከኮሚሽኑ የ2010 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ አመት የፕሮግራም በጀት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ታውቋል፡፡
- የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ዳይሬክቶሬት በኩል ቅፅበታዊ ለሆኑ አደጋዎች የሚሰጠው ምላሽ ምግብ ነክ ባልሆኑ ቁሳቁሶች ላይ አዲስ የአሰራር ሥረዓት በመዘርጋቱና አሰራሩ የኢንተርኔት አገልግሎት ስለሚያስፈልገውና የክልሎችን ጥያቄ በአፋጣኝ ለመመለስ ውስንነት የሚታይበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡
- የኦዲት ቡድኑ ስለጉዳዩ ለኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ጥያቄ በሰጡት መልስ ቅፅበታዊ ለሆኑ አደጋዎች በተቀመጠው በ72ሰዓት ጊዜ መሰረት የእርዳታ ድጋፍ ለማድረስ በመንገዶች ምቹ ያለመሆን፣ የፀጥታ ችግር፣ በእያንዳንዱ የምግብ ማራገፊያ ጣብያዎች ለማድረስ የሎጂስቲክስ እጥረት በመኖሩ፣ በአጓጓዥ ድርጅቶች ችግር ወይም ያለአቅማቸው ጨረታ በማሸነፍ (በመውሰድ) ችግሮች በመፈጠራቸው ምክንያት መሆኑንና የተዘረጋው የምላሽ አሰጣጥ ስርዓት በተዋረድ ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

152. የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች ጉዳዩን አስመልክቶ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ አዳዲስ አሠራር ለመዘርጋት ክፍተቶችን በመለየት ወደፊት የሚፈጸም መሆኑን ገልጸዋል፡፡

153. በመሆኑም ለቅፅበታዊ አደጋ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ቀልጣፋ አሰራርና የሎጂስቲክስ አገልግሎት በመዘርጋት ተግባራዊ ያልተደረገ በመሆኑ የምላሽ አሰጣጥ ስርዓቱ ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

## የኮሚሽኑን የንብረት አስተዳደር በተመለከተ፡-

154. ኮሚሽኑ አስፈላጊ ቋሚ ንብረቶችንና መገልገያ መሳሪያዎችን ሊያሟላ መወገድ የሚገባቸውንም በወቅቱ ሊያስወግድ እና ንብረቱን ባግባቡ ሊስተዳድርና ለአደጋ ምላሽ ስራና መልሶ ማቋቋም ሊያውል ይገባል፡፡

155. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የዶክመንት ክለሳዎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ መሰረት የሚከተሉት ዋናዋና ችግሮች ታይተዋል፡-

- ጉዳዮን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ በኮሚሽኑ ባካሄደው የዶክመንት ክለሣ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በተጠናከረና በተፈለገው መጠን አለመወገዳቸውን ከኮሚሽኑ የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የሶስት ዓመታት (2010-2012) የውጤት ተኮር ዕቅድ ታውቋል፡፡
- በሀረሪ ክልል ለምላሽ ስራ የሚያገለግሉ ምንም አይነት ቋሚ ንብረቶች ተሰጥቶ እንደማያውቅ ለአብነትም የፕላስቲክ ድንኳኖችና ለስርጭት የሚያስፈልጉ የሞተር ሳይክሎች አቅርቦት አለመኖሩን የክልሉ አደጋ ስጋት የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተተከለው የምድር ሚዛን አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑና የመለዋወጫ ዕቃ አልተገኘለትም በሚል ምክንያት ጥገና አለመደረጉ እንዲሁም ቁሳቁሶችን በናሙና ለመመዘን በውስጥ ሚዛን በመጠቀም እየተሰራ ቢሆንም በቅርንጫፉ ላሉት መጋዘኖች ሁሉ አንድ የውስጥ ሚዛን ብቻ በመኖሩ ከመጋዘን መጋዘን በማዘዋወር ለመስራት መገደዳቸውንና በስራ ቅልጥፍና ጥራት ላይ ችግር እንደሚያስከትል ለስራ ኃላፊዎቹ በቀረበ ቃለ-መጠይቅና በመስክ ምልከታ ታውቋል፡፡
- በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምድር ሚዛን ቢኖርም አገልግሎት የማይሰጥ በመሆኑ የእህል ንግድ ድርጅት የምድር ሚዛን በኪራይ ክፍያ እየተጠቀሙ እንደሚገኙና ከፍተኛ የሆነ ወጪ ማስከተሉ በተጨማሪም በክፍያ የሚጠቀሙት አንድ የምድር ሚዛን በመሆኑ ከፍተኛ መጉላላት እየፈጠረ መሆኑንና ለሚዛን ኪራይ የሚከፈለው የአመት ክፍያ ሚዛኑን

መግዛት የሚያስችል ወጪ የተጠጋ እንደሆነ የቅርንጫፉ የሥራ ኃላፊዎችለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

- ከዚህ ጋር በተያያዘ በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት የምድር ሚዛን ባለመኖሩ ምክንያት ለምድር ሚዛን ኪራይ ለኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የእህልና ቡና ንግድ ስራ ዘርፍ ያልተከፈለ የምድር ሚዛን አገልግሎት ከጥቅምት 2009 እስከ ጥር 2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ ለነበረበት ውዝፍ ክፍያ ብር አምስት መቶ ሺ ዘጠኝ ብር ከሰማኒያ ሳንቲም ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ እንዲሁም ከማጋቢት 04/2009 እስከ ሚያዚያ 3/2009 ዓ.ም ብር አስራ ሶስት ሺ ስድስት መቶ አርባ ሶስት (13,643) ብር አጠቃላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ለሚዘን ኪራይ ብቻ ብር 513 ሺ 653 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች ተገጥመው ቢገኙም አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም ይህን ያህል ንብረት እያንቀሳቀሰ የእሳት አደጋ መከላከያ ባለመኖሩ ከፍተኛ ስጋት ውስጥ መሆናቸውን የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡ የኦዲት ቡድኑም በመስክ ባካሄደው ጉብኝት የእሳት አደጋ መሳሪያዎች አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- የድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት ሪባግ አድርጎ ለመመዘን ያለው አንድ ሚዛን ብቻ በመሆኑ የመጫንና የማውረድ ስራው በአምስት መጋዘኖች ላይ እየተሰራ በመሆኑ ምክንያት የሚዛን እጥረት በመከሰቱ ቅድሚያ ተሰጥቶ ሁለት ባለ ሀምሳ ኪሎ ግራም ሚዛን እንዲላክ በቀን 12/07/2010 ዓ.ም ለኮሚሽኑን የሎጂስቲክስ ዳይሮክቶሬት ቢጠይቅም እስካሁን ምላሽ ያልተሰጠው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት ለሚገኙ ወዛደሮች ለመጠጥ እና ለገላ መታጠቢያ ማጠራቀሚያ የሚሆን ባለ አስር ሺ ሊትር ውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር እንዲገዛላቸው በተደጋጋሚ በቀን 24 /04/2009 ዓ.ም እና 19/06/2010 ዓ.ም ለኮሚሽኑ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ እና ሎጂሰቲክስ ዳይሮክቶሬት ቢጠየቅም እስካሁን ምላሽ አለመሰጠቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የኮሚሽኑ አቅርቦትና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በአገልግሎት ላይ ያሉና አገልግሎት የማይሰጡ ተሽከርካሪዎችን ዝርዝር በቀን 16/02/2010 ዓ.ም ለመንግስት ግዥና አሰተዳደር ኤጀንሲ እንዲልክ ተጠይቆ ቢልክም በድሬዳዋና አዳማ ማእከላዊ መጋዘኖች የሚገኙ አገልግሎት የማይሰጡ ተሽከርካሪዎች፣ ጎማዎችና ብረታብሮች አለማሰወገዱን የኦዲት ቡድኑ በኦዲቱ ወቅት ባካሄደው የመስክ ጉብኝት አረጋግጧል፡፡

- የብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲ የአደጋ ምላሽ ስራ decentralize መደረግ አለበት በሚል ቢያስቀምጥም እስካሁን centralize የሆነ አሰራር መኖሩን እና የብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ለአደጋ ምላሽ ማቴሪያሎችን በራሱ ብቻ በማዕከል በመያዝ ክልሎች ነገሮችን የማሳለጥ (facilitate) ስራ እንዲሰሩ ብቻ መገደዳቸውን በተለይም በክልሎች የሎጂስቲክስና የበጀት ችግር ያለባቸው በመሆኑ ኮሚሽኑ በተቀመጠው ፖሊሲ መሰረት መስራት እንዳለበት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- እንዲሁም የብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ለአደጋ ምላሽ የሚያስፈልግ የዝግጁነት አቅም በሀገር አቀፍ ደረጃ፣ በፌደራል መሪ ሴክተር መ/ቤቶች እንዲሁም በክልል፣ በዞን፣ በቀበሌ፣ በብዙሃን ማህበራት፣ በህብረተሰብና ግለሰብ ደረጃ ለማቋቋምና ለማጠናከር የሚያስችሉ እርምጃዎች እንደሚወሰዱ ቢያስቀምጥም እስካሁን በዚህ ዙሪያ ስለተከናወኑት ስራዎች በክልሎችም ይሁን በኮሚሽኑ የሰነድ ማስረጃዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡
- በዚህ ዙሪያ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የኮሚሽኑ የስራ ግዝፈትና ያለው የሰው ኃይል ባለመመጣጠኑ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
- እንዲሁም የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ከመንግሥት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጋር በመነጋገር ቁሳቁሶች እየተወገዱ የሚገኝ መሆኑን የገለፁ ሲሆን፡፡
- ክልሎች በራሳቸው በጀት በመመደብ ቋሚ ንብረቶችን ማሟላት እንዳለባቸውና የፌዴራል መንግሥትን መጠበቅ እንደሌለባቸውና ከክልል አቅም በላይ የሆኑ ብቻ በፌዴራል መንግሥት የሚሟሉ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

156. ይሁን እንጂ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ አገልግሎት የማይሰጡ ተሽከርካሪዎችና ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ግቢ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት ተከማችተው መኖራቸውና አለመወገዳቸውን የኦዲት ቡድኑ በመስክ ባካሄደው ጉብኝት ያረጋገጠ መሆኑ፤ እንዲሁም ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያስፈልጉ ቋሚ ንብረቶች ባልተሟሉበት ሁኔታ በኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

157. በመሆኑም ኮሚሽኑ አስፈላጊ ቋሚ ንብረቶችንና መገልገያ መሳሪያዎችን ባለማሟላቱ መወገድ የሚገባቸውንም በወቅቱ ባለማስወገዱ የአደጋ ምላሽ ስራውን በጥራትና በቅልጥፍና እንዳያካሂድ እና ውጤታማ እንዳይሆን ተፅዕኖ ከማሳደሩም በላይ አላስፈላጊ የቋሚ ንብረት ኪራይ ወጪን ሊያስከትል ይችላል፡፡

**ኮሚሽኑ በአደጋ የተጎዱ ወይም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ እንስሳቶችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር የዘረጋና ተግባራዊ ያደርገ መሆኑን በተመለከተ፡-**

158. ኮሚሽኑ በአደጋ የተጎዱ ወይም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ እንስሳቶችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

159. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የዶከመንት ክለሳወች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ እና የመስክ ምልከታ መሰረት፡-

- ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው ሴክተሮች ጋር በመሆን የአደጋ ስጋት ስራ አመራር (DRM Tecnical working Group) እና የግብርና ግብረ ኃይል (Agricultural Task Force) አማካይነት በሚደረገው ውይይት/ስብሰባ በማስተባበርና በመሳተፍ ድርቅ በሚከሰትባቸው አካባቢዎች የተጎዱ እንስሳቶችን ከጉዳት ለመታደግ በተለይም የእንሰሳት መኖ እና መድኃኒት አቅርቦትን በሚመለከት እየሰራ እንደሚገኝ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- በሶማሌ ክልል ለእንስሳቶች የመኖና የውሃ አቅርቦት እንዲኖር ቢደረግም በቂ አለመሆኑን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- በኦሮሚያ ክልል በዋናነት በባሌና ጉጂ አርብቶ አደሮች አካባቢ በእንስሳቶች ላይ ጉዳት የሚደርስ በመሆኑ የተጎዱ እንስሳቶችን በሙሉ ለማዳን ኮሚሽኑ በችግሩ ስፋት ልክ ተደራሽ ለማድረግ ክፍተቶች ያሉበት በመሆኑ በተለይ በ2008 ዓ.ም ቦረና ላይ ከፍተኛ ጉዳት በእንስሳቶች ላይ በመድረሱ ካሉት አራት ሚሊዮን እንስሳቶች 50%ቱ ላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- ለእንስሳት የሚቀርብ መኖ በኮሚሽኑ ደረጃ ስታንዳርድ ወጥቶለት እየተሰራ አለመሆኑን፣ ኮሚሽኑም የተቻለውን ያህል ድጋፍ ብቻ ሲያደረግ መቆየቱን የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ገልፀዋል፡፡
- በኦዲት ቡድኑ በእንስሳቶች ዙሪያ ከ2008-2010 ዓ.ም ስለደረሰው ጉዳትና ስለተደረገው ድጋፍ የሚገልፅ በሰነድ የተደገፈ ማስረጃ ኦድቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

160. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄና በነባራዊ ሁኔታ በሰጡት ምላሽ የአደጋ ስራው ሌሎችንም መሪ ሴክተር መ/ቤቶችን የሚመለከት በመሆኑ በተሟላ መልኩ ለመስራት አልተቻለም ነገር ግን ሥራው የግብርና ሚኒስቴር ቢሆንም ኮሚሽኑ

የማስተባበርና የመከታተል ኃላፊነት ስላለበት ለእንስሳት የመኖ ግዥ በማከናወን ኃላፊነቱን የተወጣ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

- እንዲሁም የእንስሳት መኖ የሚቀርበው የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር /በግብርና ሚኒስቴር/ ስታንዳርድ ሲሆን የሚቀርበውም በግብርና ሚኒስቴር መሆኑን ነገር ግን ኮሚሽኑ በ2008 ዓ.ም በነበረው ድርቅ ያቀረበ ቢሆንም ከብሔራዊ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ፖሊሲ አንፃር የግብርና ሚኒስቴር ሥራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

161. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ በኮሚሽኑ በማቋቋሚያ ደንቡ ላይ በተቀመጠው መሰረት ኮሚሽኑ በአደጋ የተጎዱ ወይም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ እንስሳቶችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደርገ በመሆኑ እንዲሁም ኮሚሽኑ ስላደረገው ድጋፍ የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ በመሆኑ በኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

162. በመሆኑም ኮሚሽኑ በአደጋ የተጎዱ ወይም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ እንስሳቶችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ በመሆኑ በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ ችግሮች ምክንያት በእንስሳቶች ላይ የሚከሰቱ ችግሮች የከፋ እንዲሆኑ በማድረግ በዜጎች እና በሀገር ኢኮኖሚ የከፋ ጉዳት እንዲደርስ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ኮሚሽኑ የክትትልና ግምገማ ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደርገ መሆኑን በተመለከተ፡-

163. ኮሚሽኑ ያከናወናቸውን የአደጋ ምላሽ ስራዎችን እና የመልሶ ማቋቋም ስራዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትልና ግምገማ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

164. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የዶክመንት ክለሳዎች፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና በመስክ ጉብኝት መሰረት ኮሚሽኑ ያከናወናቸውን የአደጋ ምላሽ ስራዎችን እና የመልሶ ማቋቋም ስራዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

- የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄደው የዶክመንት ክለሳ መሰረት የተጠናከረ ፣ የክትትልና፣ ግምገማ ምዘና ስርዓት አለመኖሩን እንዲሁም በኮሚሽኑ ተከታታይና የተጠናከረ የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓትና ግብረ መልስ አለመኖሩን ከኮሚሽኑ የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የሶስት ዓመታት (2010-2012) የውጤት ተኮር ዕቅድ ታውቋል፡፡ እንዲሁም በኮሚሽኑ የተጠናከረ የመስክ የክትትልና ግምገማ ስራ ለማከናወን

በበቂ ሁኔታ የተደራጀ የትራንስፖርት አቅርቦት እጥረት መኖሩን ከኮሚሽኑ የ2010 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ አመት የፕሮግራም በጀት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ተገልፅዋል፡፡

- የሀረሪ ክልል የመልሶ ማቋቋም ስራዎች እንዲሰሩ ኮሚሽኑ የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል በደረሰው አደጋ መጠን የማይጣጣምና ክትትል የሚያደርግበት አግባብ አለመኖሩን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በሶማሌ ክልል ኮሚሽኑ የመልሶ ማቋቋም ዕቅድ በታሰበው ጊዜ እንዲፈፀም ክትትልና ግምገማ ያደረገበት ሁኔታ በቂ አለመሆኑን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች የገለፁ መሆኑ፤
- በደቡብ ክልል ኮሚሽኑ በመልሶ ማቋቋም ድጋፍና ክትትል የሚያደርግ ቢሆንም ከሴክተር መ/ቤቶች ጋር በመቀናጀት የመልሶ ማቋቋም ስራዎች ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- ከሶማሌና ከኦሮሚያ ክልል ተፈናቅለው በሀረሪ ክልል የሚገኙ ተፈናቃዮች የመልሶ ማቋቋም ስራ ያልተሰራላቸው መሆኑንና እየተደረገ ያለው ድጋፍ በቂና አጥጋቢ ባለመሆኑ ህብረተሰቡ በአእምሮና በስነ-ልቦና በፍጥነት እንዳያገግሙ ማድረጉን በ2010 ዓ.ም ተፈናቃዮችን በማስመልከት ከተካሄደ የጥናት ሪፖርት ላይ የተመለከተ ሲሆን ኮሚሽኑ የተፈናቃዮችን ሁኔታ በተመለከተ ተደጋጋሚ ጥናቶችን ሲያካሂድ የቆየ ቢሆንም የመልሶ ማቋቋም እቅዱ ተግባራዊ አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በሀረሪ ክልል ተጠልለው የሚገኙ ከኢትዮ ሶማሌ ክልል የተፈናቀሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን መልሶ ለማቋቋም ኮሚሽኑ እገዛ እንዲያደርግ ቢጠይቁም ስራውን እናንተ ጀምሩትና ተሞክሮውን ከእናንተ እንወስዳለን የሚል ምላሽ የተሰጣቸው መሆኑንና ለተፈናቃዮች ቀለብ ከመስፈር ባለፈ የመልሶ ማቋቋም ስራዎችን እየገመገመ፣ ክትትል እያደረገና እየሰራ አለመሆኑን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በደቡብ ክልል ጌዲኦ ዞን በ2009 ዓ.ም የተጀመሩ የመልሶ ማቋቋም ስራዎች አስካሁን አለመጠናቀቃቸውንና ኮሚሽኑም የተጀመሩ ስራዎችን ማስፈፀምና መከታተል እንደሚገባው የዞኑ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከሌላ ቦታ የመጡ ተፈናቃዮች በመሆናቸው ምክንያት ምላሽ እንጂ የመልሶ ማቋቋም ስራ አለመከናወኑንና በኮሚሽኑ በኩልም የመልሶ ማቋቋም ስራ አለመሰራቱን የከተማ አስተዳደሩ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች የገለፁ ሲሆን የኦዲት

ቡድኑም ለተፈናቃዮች መልሶ ማቋቋም ስራ እንዳልተሰራ በመስክ ምልከታ አረጋግጠዋል፡፡

- ከኢትዮ ሱማሌ ተፈናቅለው ሀረር ከተማ ተጠልለው ለሚገኙ ዜጎች መልሶ ለማቋቋም እንዲያስችል የሀረሪ ክልል የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራ ምግብ ዋስትና አደጋ መከላከል ጽ/ቤት የሚያስፈልጉ የቤት ቁሳቁሶችን ኮሚሽኑ ድጋፍ እንዲያደርግ 23 ዓይነት ቁሳቁሶችን በቀን 14/10/2010 ዓ.ም በዝርዝር ለኮሚሽኑ ቢልክም ለመልሶ ማቋቋም አሰፈላጊ እና መሰረታዊ ናቸው የተባሉ የቁሳቁስ አይነቶች ያልተላከ መሆኑንና ከተጠየቁት ውስጥ በቁጥር አራት(4) ብቻ በተለምዶ የሚከላኩ ቁሳቁሶች ማለትም ትንሹ ሰሃን፣ ጆክ፣ የውሃ ኩባያና መካከለኛ ብረት ድስት ብቻ መሆኑን ለማወቅ ተችለዋል፡፡
- የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት በወቅታዊ ሁኔታዎች የተፈናቀሉ ዜጎች ያሉበት ሁኔታ በጣም አሳሳቢ መሆኑንና በልማት ስራ ላይ ተፅእኖ እንደፈጠረና ተፈናቃዮቹ ከጊዜያዊ መጠለያቸው መነሳት የሚገባቸው ጊዜ በመርዘሙ ምክንያት ወዳልተፈለገ ድርጊት መግባት፣ የካምፕ ያልተመች ኑሮ መሰልቸት፣ ሴቶችና ህፃናት ያልተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ መሆናቸው እንዲሁም የምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በተገቢው ሁኔታ አለመቅረቡ እና አስተዳደሩ ላይ ከፍተኛ የበጀት ጫና እየፈጠረ በመሆኑ በኮሚሽኑ በኩል ሁኔታዎች እንዲመቻችና ችግሩ እልባት እንዲያገኝ በቀን 22/10/2010 ዓ.ም ለኮሚሽኑ ጥያቄ ያቀረበ ቢሆንም የኦዲት ቡድኑ በመስክ ለማረጋገጥ እንደቻለው ተፈናቃዎቹ ከመስከረም 3/2010 ዓ.ም ጀምሮ የዝርዝር ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መሆናቸውን ለማወቅ መቻሉ፤

165. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ- መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ የአደጋ ምላሽን በተመለከተ በፕራይዮታዜሽን ኮሚቴ በመገምገም እቅጣጫ በማስቀመጥ እየተሰራ መሆኑንና ያሉትን ክፍተቶች በመለየት እንደሚገመገም ነገር ግን ቦታዎች ላይ በመውረድ ክትትል ለማድረግ የባለሞያ እጥረቶች በመኖሩ ቀጣይነት ያለው ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ስትራክቸር የሌለ መሆኑን እንዲሁም ይህን በተመለከተ ራሱን የቻለ መዋቅርና ባለሞያ የሌለ መሆኑን፤ በአዲሱ አደረጃጀት መሠረት መጠናከር የሚገባው የሥራ ዘርፍ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የመልሶ ማቋቋም ስራ ሁሉንም ሴክተር መ/ቤቶች የሚመለከት ስራና ሀብት የሚፈልግ በመሆኑ ጥናት ተጠንቶ በተለይም የኦሮሚያና ሶማሌ ክልል ተፈናቃዮችን ለማቋቋም እንቅስቃሴ መኖሩን ነገር ግን ለመልሶ

ማቋቋም የሚውል አቅም የመፍጠር ስራ መሰራት እንዳለበት እንዲሁም የመልሶ ማቋቋም ስራዎች አዲስ ከመሆኑም አንፃር እየተሰራ ያለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

166. የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ይሄንን ይበሉ እንጅ በፕራዮሪታይዜሽን ኮሚቴ በመገምገም እየተሰራ ነው የሚለው ሁኔታ ቃለ ጉባኤ በመያዝ ውይይት ከማድረግ በዘለለ ኮሚቴው በየጊዜው ክትትል ስለማድረጉ መረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

167. በመሆኑም ኮሚሽኑ ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ በመሆኑ ያከናወናቸው የአደጋ ምላሽ እና የመልሶ ማቋቋም ስራዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ አያስችለውም፡፡ እንዲሁም በተፈናቃዮች ላይ የተራዘመ ስነ-ልቦናዊ ጫና ከመፍጠሩም በላይ ተቋቁመው ራሳቸውን እንዳይችሉ በማድረግና ምግብ በመስጠት ብቻ ከፍተኛ የሐገር ሀብት እየባከነ በሀገር ኢኮኖሚ ብሎም ተፈናቃዮች በሰፈሩበት የህብረተሰብ ክፍል ላይ ጫና ይፈጥራል፡፡

## ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር በመንግስት የልማት ፖሊሲዎች፣ስትራቴጂዎች፣ የልማት ዕቅድና ፕሮግራሞች እንዲሁም በስርዓተ ትምህርት መካተቱን በተመለከተ፡-

168. ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር በመንግስት የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የልማት ዕቅድና ፕሮግራሞች፣ በግል መ/ቤቶች እንዲሁም በስርዓተ-ትምህርት መካተቱን ሊያረጋግጥና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

169. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የዶከመንት ክለሳወች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና የመስክ ጉብኝት መሰረት የሚከተሉት ዋናዋና ችግሮች ታይተዋል፡-

- በኮሚሽኑ የፀደቀውን የአደጋ ስጋት ፖሊሲና ስትራቴጂ ለሴክተር መ/ቤቶች እና ለሚመለከታቸው ሁሉ ለማካተትና ለማስረፅ ታቅዶ አለመከናወኑን እንዲሁም የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ባሉ ደረጃዎች በስርዓተ-ትምህርት ውስጥ እንዲሁም በምርምር ተቋማት እቅድ ውስጥ እንዲካተት ለማድረግ ታቅዶ አለመከናወኑን ከአደጋ ስጋት ቅነሳ ዳይሬክቶሬት የ2010 ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መገለፁ፤

○ የአደጋ ስጋት ፖሊሲና ስትራቴጂን ለሴክተር መ/ቤቶች እና ለሚመለከታቸው ሁሉ ለማካተት እና ለማስረፅ (mainstreaming) ታቅዶ በበጀት እጥረት /አለመገኘት አለመከናወኑን እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አማካኝነት በአደጋ ስጋት ስራ አመራር መስክ ቀጣይነት ባለው መልኩ ሙያተኞችን ማፍራት የሚያስችል እና ጥናትና ምርምርን የሚያጠናክር አሰራር ለመዘርጋት ታቅዶ በበጀት እጥረት አለመከናወኑን ከአደጋ ስጋት ቅነሳ ዳይሬክቶሬት የ2010 በጀት ዓመት አፈፃፀም ሪፖርት ታውቋል፡፡

170. የኦዲት ቡድኑ ለኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ጉዳዩን አስመልክቶ ላቀረበላቸው ቃለመጠይቅበሰጡት መልስ ለእያንዳንዱ ሴክተር መ/ቤት የአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር በዕቅዳቸው ውስጥ እንዲያካትቱ guideline ቢዘጋጅም እስካሁን ሴክተር መ/ቤቶች በተለያዩ ግብረ ሃይሎች ከመሳተፍ ባለፈ በእቅዳቸው ውስጥ አለማካተታቸውንና በሂደት ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

171. እንዲሁም የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ በአሁኑ ወቅት የማስረፅ ማኑዋል የተዘጋጀ ስለሆነ በቀጣይነት ስራው እንደሚፈፀም ገልፀዋል፡፡

172. በመሆኑም ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር በመንግስት የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የልማት ዕቅድና ፕሮግራሞች፣ በግል መ/ቤቶች ዕቅዶች እንዲሁም በስርዓተ-ትምህርት መካተቱን አለማረጋገጡና ድጋፍ አለማድረጉ የአደጋ ምላሽ ስራዎች በሁሉም ተቋማት ተገቢው ግንዛቤ ተወስዶ እንዳይሰራ እና አሰራሩ ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

## ኮሚሽኑ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች ተብሎ የተሰየሙ የፌደራል መንግስት የአስፈፃሚ አካላት በዕቅዳቸው ውስጥ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ማካተታቸውን በተመለከተ፡-

173. ኮሚሽኑ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች ተብሎ የተሰየሙ የፌደራል መንግስት የአስፈፃሚ አካላት በዕቅዳቸው ውስጥ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ማካተታቸውን ሊያረጋግጥና አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

174. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የዶከመንት ክለሳወች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረጉ ቃለ-መጠይቆች እና የመስክ ምልከታወች መሰረት የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡-

○ የአደጋ ስጋት ቅነሳ እቅዶችን በወረዳ ሴክተር መ/ቤቶች ዓመታዊ የልማት እቅድ ለማካተት ታቅዶ አለመከናወኑንና የአደጋ ስጋት ስራ አመራር በሴክተር መ/ቤቶችና

በክልሎች አለመካተቱን ከአደጋ ስጋት ቅነሳ ዳይሬክቶሬት የ2009 እና 2010 በጀት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርትና ከቃለ-መጠይቅ ምላሾች ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዘርፈ ብዙ አደጋዎችና ሴክተሮችን የያዘ አቀራረብ ያለው በመሆኑ የሴክተር መ/ቤቶች ተሳትፎና ኃላፊነት አስፈላጊ ቢሆንም የአደጋ ስጋት ቅነሳ የማስረጽና የማካተት ሂደት በመዘግየቱ ችግር የፈጠረ መሆኑና የድጋፍና በህግ ማዕቀፍ በመደገፍ የክትትል ስራዎች ለማድረግ እንዳልተቻለ ገልፀዋል፡፡
- በሀረሪ ክልል ኮሚሽኑ በፌደራል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ደረጃ እንዲካተት የማድረግ ስራዎችን ባለመስራቱ ከሴክተር ሚኒሰቴር መስሪያ ቤቶች ወደ ክልል የሚወርድበት ሁኔታ መፈጠር አለመቻሉን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በሴክተር መስሪያ ቤቶች እቅድ ውስጥ እስካሁን አለመካተቱንና ክትትል እና ድጋፍ አለመደረጉን የአስተዳደሩ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

175. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የተዘጋጀው ጋይድ ላይን(Guide Line) በቅርብ በመሆኑና ሂደቱ ጊዜ የሚፈጅ መሆኑን በተጨማሪም ወቅታዊ የአገሪቱ ሁኔታ በዘርፈ ብዙ አደጋዎች ምክንያት ስራው በተያዘው ጊዜ እንዳይሰራ ማድረጉንና ከሴክተር መ/ቤቶች ጋር አብሮ ለመስራት ችግሮች መኖራቸው በተለይም እነሱን አካቱ ብሎ ጫና ለማሳደር በቀናነት የመቀበሉና የመምጣቱ እንዲሁም ተወያይቶ የመስራቱ ስራ ደካማ በመሆኑንና ኃላፊነታቸውንም እየተወጡ አለመሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

176. በመሆኑም ኮሚሽኑ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች ተብለው የተሰየሙ የፌደራል መንግስት የአስፈፃሚ አካላት በዕቅዳቸው ውስጥ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ማካተታቸውን አለማረጋገጡ እና አፈፃፀሙን አለመከታተሉ የአደጋ ምላሽ ስራዎች በሴክተር መ/ቤቶች ኃላፊነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ እንዳይከናወንና ምላሹ የአንድ ወገን ብቻ እንዲሆንና የተሟላ እና ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

## ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው መሪ ሴክተር መ/ቤቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፡-

177. ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው መሪ ሴክተር መ/ቤቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጂታዊ አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

178. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የዶክመንት ክለሳዎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ መሰረት፡-

- ኮሚሽኑ ከክልሎች ጋር ያለው የስራ ግንኙነት በአሰራርና አደረጃጀት ያልተጠናከረ መሆኑን እንዲሁም ከሴክተር ሚኒስቴር መ/ቤቶች ጋር የተጠያቂነት አሰራር ጠንካራ አለመሆን ከ2010 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ አመት የፕሮግራም በጀት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ታውቋል፡፡
- ኮሚሽኑ ከተለያዩ ሴክተር ሚኒስቴር መ/ቤቶችና እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ የሥራ ሥምምነት ሰነድ አለመኖሩን እና የDRM mainstreaming በሴክተር መ/ቤቶች የህግ ማዕቀፍ ኖሮት እንዲተገበር ባለመደረጉ በቅንጅት አሰራሩ ላይ በፌደራል፣ በክልል እና በወረዳ አንደተፈለገው እየተተገበረ እንዳልሆነ የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

179. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ

- ቅንጅታዊ አሠራር በመንግሥትና በአጋር አካላት መካከል ያለ መሆኑ፤
- ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚቴዎች መኖራቸውን፤
- ከአጋር አካላት ጋር ቋሚ መድረክ ያለ መሆኑን፤
- ከክልሎች ጋር የግንኙነት ጊዜ የተጀመረ መሆኑንና ከማስረጽ/mainstreaming/ በኋላ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

180. ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ ከመሪ ሴክተር መ/ቤቶችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ወጥ የሆነ ቅንጂታዊ አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ ስለማድረጉ እንዲሁም ቋሚ የሆነ መድረክ በማዘጋጀት ውይይት በማድረግ አቅጣጫ በማስቀመጥ እየተሰራበት ያለውን ሁኔታ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ለኦዲት ቡድኑ የሰነድ ማስረጃ ተጠይቆ ባልቀረበበትና ከሴክተር መ/ቤቶች ጋር ተጠያቂነት ያለው አሰራር ባልተዘረጋበት ሁኔታ በኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

181. በመሆኑም ኮሚሽኑ ከመሪ ሴክተር መ/ቤቶች፣ ከክልሎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው የስራ ግንኙነት በአሰራርና አደረጃጀት ያልተጠናከረ በመሆኑ የተጠያቂነት አሰራር እንዳይኖር ሊያደርግና የአደጋ ምላሽ አሰጣጡ ውጤታማ እንዳይሆን ደርጋል፡፡

## ኮሚሽኑ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴዎች ከአካባቢ ሁኔታ ጋር የሚስማሙ መሆኑን በተመለከተ፡-

182. ኮሚሽኑ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴዎች ከአካባቢ ሁኔታ ጋር የሚስማሙ መሆኑን ሊገመግምና ለአካባቢ ጥበቃ ትኩረት መስጠታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

183. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የዶክመንት ክለሳዎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረጉ ቃለ-መጠይቆች እና የመስክ ጉብኝቶች መሰረት፡-

- በአደጋ ስጋት ስራ አመራር እና በማህበራዊ ጥበቃ ስራዎች ስራ መካከል መናበብ እንዲኖር፣ በአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለመቋቋምና ለዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ትኩረት እንዲሰጥ ክትትል ለማድረግ ቢታቀድም አለመከናወኑና የአደጋ ስጋት ቅነሳ ስራ እንቅስቃስዎች ከአካባቢ ሁኔታ ጋር የሚስማሙ መሆናቸውን በማረጋገጥ፤ለተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና ልማት እንዲሁም ለአካባቢ ጥበቃና የአካባቢ ብክለት ስጋት ቅነሳ ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ አለመከናወኑን ከኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዳይሬክቶሬት የ2009 ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መታወቁ፣
- በሀረሪ ክልል እየተከናወኑ ያሉት የመልሶ ማቋቋም ስራዎች አካባቢ ጥናት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑንና ለጥቃቅን እና አነስተኛ የተሰራ ስፍራ ላይ እንዲሰፍሩ ብቻ መደረጉን እንዲሁም ለኑሮ ምቹ መሆኑን ጭምር የተጠና እንዳልሆነ በኦዲቱ ወቅት ለክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች በቀረበ በቃለ- መጠይቅና በመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በሶማሌ ክልል እየተሰሩ ያሉት የመልሶ መቋቋምና የምላሽ ስራዎች በጥናት የተደገፈና የአካባቢ ሁኔታን የማይጎዱ መሆናቸውን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች በቃል የገለፁ ቢሆንም በዚህ ዙሪያ ከኮሚሽኑ ጋር በመሆን የተጠና ጥናት ስለመኖሩ የቀረበ የሰነድ ማስረጃ የለም፡፡

184. ስለጉዳዩ የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በPSNP (Productive safety Net program) መመሪያ በኩል የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም በቀጣይነት የሚሠራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

185. ይሁን እንጂ በPSNP (Productive safety Net program) መመሪያ በኩል የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች እየተሰራ ስለመሆኑ በክልሎችም ይሁን በኮሚሽኑ በኩል መረጃ ባለመቅረቡ የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

186. በመሆኑም የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎች ለከፋ የአካባቢ መራቆትና ብክለት ሊያጋልጥና በህብረተሰቡ ዘለቄታዊ ኑሮና ጤና ላይ ችግር ሊያስከትል ይችላል፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

187. የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግ በኮሚሽኑ የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን እንረዳለን፤ ከኦዲቱ አላማ አንፃር የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የአደጋ ሚላሽና መልሶ ማቋቋም ስራ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን እና የታሰበውን ዓላማ ማሳካት የተቻለ መሆኑን በተመለከተ የሚከተሉት የአሠራር ግድፈቶች እና ክፍተቶች በመኖሩ የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡-

- ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂን ስራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ህጎች፣መመሪያዎችና ማዕቀፎችን አለማዘጋጀቱ እና የአፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት አለመዘርጋቱ፡፡
- ኮሚሽኑ በየደረጃው የሚከናወኑ የአደጋ ምላሽ ፕሮግራሞች የተቀናጀ፣በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተና ያልተማከለ የአሰራር ስርዓትን በመዘርጋት በየደረጃው መወሰድ የሚገባቸውን ተገቢ እርምጃዎች በወቅቱና በየደረጃው በተሟላ ሁኔታ እንዲወሰዱ ያላደረገ መሆኑ፡፡
- ኮሚሽኑ የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ምግብ ዕርዳታ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ስትራቴጂክ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችትን ከሚያስተዳድር የሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት የዕርዳታ እህል በመውሰድ የዕርዳታ እህል በወቅቱ የማያሰራጭ መሆኑ፡፡
- ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በአገር አቀፍ ደረጃ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ዝግጅትና ክለሳ ስራን በሚፈለገው መጠን ያልሰራና ያልመራ መሆኑ፡፡
- ኮሚሽኑ የአደጋ ጥናት መረጃ ላይ ያተኮረ ምላሽ ባለመስጠቱ በተለያዩ ግጭቶች ምክንያት በዕለት ዕርዳታ እና በምግብ ነክ ባልሆኑ ድጋፎች እንዳይካተቱና ለተፈናቃዮች የሚደረገው ድጋፍ ሙሉና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎችን ያላከተተ መሆኑ፡፡
- ኮሚሽኑ በቅድመ-አደጋ፣ በአደጋና በድህረ-አደጋ ወቅት የአደጋ ስጋት ትንበያን ጨምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ ጥናቶችንና ግምገማዎችን በአግባቡ ያልመራ እና ያላስተባበር መሆኑ፡፡
- ኮሚሽኑ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ አለመደርጉ፡፡

- ኮሚሽኑ በየደረጃው ባሉ የአስተዳደር እርከኖች ወጥ የሆነ እና የሚናበቡ የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከላት ባለመመስረታቸው በክልሎች እና መሪ ሴክተር መ/ቤቶች ወጥነት እንድኖር አለማድረጉ፡፡
- የኮሚሽኑ መረጃዎች በተማከለ ቦታ የማይያዙ መሆኑንና ወቅቱን የጠበቀና የተናበበ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሲስተም ተግባራዊ አለመደረጉ፡፡
- ኮሚሽኑ በየደረጃው ካሉ የአደጋ ክስተት መዋቅሮች ጋር በአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል አስተማማኝና የማያቋርጥ የመገናኛ መሳሪያ አማራጭ አለመኖሩ በመረጃ ፍሰቱና በአደጋ ምላሽ አሰጣጡ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የፈጠረ መሆኑ፡፡
- ኮሚሽኑ አደጋ በይፋ መገለፁን ተከትሎ የአደጋ ስራ አመራር ም/ቤት ሲወስን ከአገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ሀብት በማሰባሰብ ለአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ስራ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የሃብት ማሰባሰብ፣ አስተዳደር፣ የፕሮጀክት አደረጃጀትና ሂደት፣ የፈንድ ግንባታና ጠቀሜታ፣ የድጋፍ ግንኙነትን በተመለከተ ህጋዊ የሆነና መንግስታዊ እውቅና ያለው የአሰራር መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆን አለማድረጉ፡፡
- ኮሚሽኑ ውጤታማ የሆነ የሀብት አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት ዙሪያ አሰራሩን በህግ ማዕቀፍ፣ በደንብና በመመሪያ የተደገፈ የአሰራር ስርዓቶችን በማበጀት ረገድ ስራዎችን ባለመስራቱ እንዲሁም የሃብት ማሰባሰብና ፈንድ አስተዳደር መመሪያን ባለማዘጋጀቱ የአደጋ ምላሽ ዝግጁነት አቅም በሚፈለገው ደረጃ እንዲደርስ እና የሃብት ብክነትንና ስርጭትን፣ የግዥ አሰራርን እና ውጤታማነትን ቋሚ በሆነ አሰራር ለመገምገምና ለመቆጣጠር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፡፡
- ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ሀብት ከውጭ ሀገር የማሰባሰብና የመጠቀም አሰራርን በተመለከተ መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ አለማድረጉ፡፡
- ኮሚሽኑ በመዋቅሩ መሰረት የሰው ሀይል በማሟላት እና በአደጋ ክስተት ስራ አመራር የተሰማራ የሰው ኃይል እውቀቱንና ክህሎቱን በስልጠና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማዳበር እንዲያስችል የስልጠና ማዕከል አለማቋቋሙ፡፡
- ኮሚሽኑ በአደጋ ክስተት ስራ ዙሪያ የሚወጡ ህጎች፣ መመሪያዎች፣ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች ውስጥ ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ ለአረጋዊያን፣ ለአካል ጉዳተኞችና ኤች.አይቪ. ኤዲስ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ ትኩረት ስለመሰጠታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር አለመዘርጋቱ እና ተግባራዊ አለማድረጉ፡፡
- ኮሚሽኑ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ሥርዓት ዝርጋታ ባለማከናወኑ ለአመራሩና ለፈፃሚዎች በቂ የሆነ ስልጠና ያልሰጠ እና በቴክኒለጂ ሶፍትዌሮች

(softwares) ዙሪያ የሚሰጡት ስልጠናዎች ወደተግባር መቀየራቸውንም የማያረጋግጥ መሆኑ፡፡

- ኮሚሽኑ በክልሎች መካከል በአደጋ ጊዜ ተደጋግፎና ተባብሮ የምላሽ ስራን ለመስራት የሚያስችል አሰራር ተግባራዊ አለማድረጉ፡፡
- ኮሚሽኑ የመረጃ አስተዳደርና ኮሙኒኬሽን ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና በአደጋ ክስተት ስጋት ፕሮፋይል ላይ ያልተመሰረተ እንዲሁም ወቀታዊ እና ለሁሉም ተደራሽ ባለመሆኑ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎችን ኢኮኖሚዊ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆናቸውን የማያረጋግጥ መሆኑ፡፡
- ኮሚሽኑ ከውጭ በእርዳታ መልክና በግዥ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባቸውን ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውሉ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች በወቅቱ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ ማድርግ እና የምግብ ነክ የሆኑ ቁሳቁሶችን ከወደብ ለማስነሳት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በማሟላት ሀገር ውስጥ በወቅቱ ማስገባት አለመቻሉ፡፡
- ኮሚሽኑ የክምችት መጋዘኖች የሚገቡ/በክምችት ያሉና የሚወጡ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች የተቀመጠውን የጥራት ደረጃ ያሟሉ ስለመሆናቸው ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር አለማድረጉ፡፡
- ኮሚሽኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን (ማዕከላዊ መጋዘኖችን) ለመምራት፣ ለማስተባበርና ለመቆጣጠር ተግባርና ኃላፊነቱን ለመወጣት በሚያስችል መልኩ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ተግባርና ኃላፊነቶችን ለይቶ በማውረድና የሰው ሀይል ቅጥር በሟሟላት አለመስራቱ፡፡
- ኮሚሽኑ የክምችትና የስርጭት መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ አለማድረጉ እና በየደረጃው ተፈፃሚ ስለመሆኑ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር አለማድረጉ፡፡
- ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውል መጠባበቂያ በጀት፣ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ እንዲሁም በተጨማሪ በመንግስት የሚመደብና በእርዳታ የሚሰበሰብ ሀብት በአግባቡ ለምላሽ ስራው ጥቅም ላይ መዋሉን ባግባቡ የማያረጋግጥ መሆኑ፡፡
- ኮሚሽኑ በአደጋ ስጋት ፕሮፋይል መነሻነት መጠባበቂያ ዕቅድ በማቀድ ተግባራዊ ስለማድረጉ መረጃ ያልቀረበ ሲሆን የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ክለሳ እንደማይደረግና በሁሉም ወረዳዎችና ክልሎች ላይ አለመሰራቱን በናሙና ተመርጠው ከታዮ ክልሎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ኮሚሽኑ ለቅፅበታዊ አደጋ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ቀልጣፋ አሰራርና የሎጂስቲክስ አገልግሎት በመዘርጋት ተግባራዊ አለማድረጉ፡፡

- ኮሚሽኑ አስፈላጊ ቋሚ ንብረቶችንና መገልገያ መሳሪያዎችን ባለማሟላቱ፣መወገድ የሚገባቸውንም በወቅቱ ባለማስወገዱ የአደጋ ምላሽ ስራውን በጥራትና በቅልጥፍና እንዳያካሂድ እና ውጤታማ እንዳይሆን እንዲሁም አላስፈላጊ የኪራይ ወጪን ያስከተለ መሆኑ፡፡
- ኮሚሽኑ በአደጋ የተጎዱ ወይም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ እንስሳቶችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ አለማድረጉ፡፡
- ኮሚሽኑ ያከናወናቸውን የአደጋ ምላሽ ስራዎችን እና የመልሶ ማቋቋም ስራዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትልና ግምገማ ስርዓት ያልዘረጋና ተግባራዊ አለማድረጉ፡፡
- ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር በመንግስት የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የልማት ዕቅድና ፕሮግራሞች፣ በግል መ/ቤቶች ዕቅዶች እንዲሁም በስርዓተ-ትምህርት መካተቱን አለማረጋገጡና ድጋፍ አለማድረጉ፡፡
- ኮሚሽኑ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች ተብለው የተሰየሙ የፌደራል መንግስት የአስፈፃሚ አካላት በዕቅዳቸው ውስጥ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ማካተታቸውን አለማረጋገጡ እና አፈፃፀሙን አለመከታተሉ፡፡
- ኮሚሽኑ ከመሪ ሴክተር መ/ቤቶች፣ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው የስራ ግንኙነት በአሰራርና አደረጃጀት ወጥ የሆነ ቅንጂታዊ አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ አለማድረጉ፡፡
- ኮሚሽኑ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴዎች ከአካባቢ ሁኔታ ጋር የሚስማሙ መሆኑን በመገምገም ለአካባቢ ጥበቃ ትኩረት መስጠታቸውን አለማረጋገጡ ታውቋል፡፡
- በመሆኑም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሃሳቦች

188. የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን  የአደጋ ሚላሽና መልሶ ማቋቋም አስተዳደር ሥርዓትን ተከትለው እንዲተገበሩ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡


- ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂን ስራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ህጎች፣መመሪያዎችና ማዕቀፎችን በማዘጋጀት እና የአፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘረጋት ተግበራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ በየደረጃው የሚከናወኑ የአደጋ ምላሽ ፕሮግራሞች የተቀናጀ፣በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተና ያልተማከለ የአሰራር ስርዓትን በመዘርጋት በየደረጃው መወሰድ የሚገባቸውን ተገቢ እርምጃዎች በወቅቱና በየደረጃው በተሟላ ሁኔታ እንዲወሰዱ ማድረግ ይኖሪበታል፡፡
- ኮሚሽኑ የአደጋ ጊዜ ፈንድ መመሪያ እና የክምችትና ስርጭት መመሪያ በማውጣት ለምላሽ ስራው የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ ክምችት ለመያዝ፣ ለማስተዳደር እንዲሁም ለምላሽ ስራው ለማዋል በክልሎች በሚለየው ተረጅ ቁጥር መሰረት እርዳታ እንዲላክላቸው ክልሎች ጥያቄ በሚያቀርቡበት ወቅት በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ድልድል ለማድረግ እና ተረጂውን ለማዳረስ እንድቻል በጥናት ላይ የተመሰረተና የወቅቱን የግዥ/ገበያ ሁኔታን ያገናዘበ የጥሬ ገንዘብ ዕርዳታ እንዲኖር በማድረግ ለተረጅዎች ወቀታዊ እና ፈጣን ምላሽ እንድያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ምግብ ዕርዳታ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ስትራቴጂክ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችትን ከሚያስተዳድር የሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት የዕርዳታ እህል በመውሰድ የዕርዳታ እህል በወቅቱ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በአገር አቀፍ ደረጃ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ዝግጅትና ክለሳ ስራን በሚፈለገው መጠን በመምራት እና በማስተባበር እንዲሁም የአደጋ ስጋት ስራ አመራር በሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች እንድካተት በማድረግና እንድሰርፅ በማገዝ ወቅታዊ የሆነ አገር አቀፍ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል እና እሱንም መሰረት አድርጎ የሚዘጋጅ አገር አቀፍ የመጠባበቂያና የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዕቅድ እንድዘጋጅና የተጠናቀረና ወቅታዊ የአደጋ ስጋት መረጃዎች ለህብረተሰቡና ለአጋር ድርጅቶች እንድደርስ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ኮሚሽኑ የአደጋ ጥናት መረጃ ላይ ያተኮረ ምላሽ በመስጠት በተለያዩ ግጭቶች ምክንያት በዕለት ዕርዳታ እና በምግብ ነክ ባልሆኑ ድጋፎች እንድካተቱና ለተፈናቃዮች የሚደረገው ድጋፍ ሙሉና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች ያካተተ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ በቅድመ-አደጋ፣ በአደጋና በድህረ-አደጋ ወቅት የአደጋ ስጋት ትንበያን ጨምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ ጥናቶችንና ግምገማዎችን በአግባቡ በመምራት እና በማስተባበር በጥናቶች መሰረት አዳዲስ አሰራሮችና የመፍትሄ እርምጃዎች እንድወሰዱ እና የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎችን ማቀላጠፍና ማዘመን ይኖሪበታል፡፡
- ኮሚሽኑ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር በአግባቡ/በሚፈለገው መጠን በመወጣት ጥራት ያለው መረጃና በተቀላጠፈ አኳኋን ምላሽ እንድሰጥ ማድረግ ይኖሪበታል፡፡
- ኮሚሽኑ በየደረጃው ባሉ የአስተዳደር እርከኖች ወጥ የሆነ እና የሚናበቡ የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከላት በመመስረት በክልሎች እና መሪ ሴክተር መ/ቤቶች ወጥነት ባለው መልኩ ስራዎችን በአግባቡ መምራት ይኖሪበታል፡፡
- ኮሚሽኑ መረጃዎች በተማከለ እና ባግባቡ በመያዝ ወቅቱን የጠበቀና የተናበበ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሲስተም በክልሎች እና በውርዳዎች ተግባራዊ በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጡ በስራ ፍሰት በማስተሳሰር በቴክኖሎጂ የተደገፈና ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው አካላት በጥራት፣ በስፋትና ቀጣይነት ባለው መልኩ ማስተላለፍ ይጠበቅበታል፡፡
- ኮምሽኑ በየደረጃው ካሉ የአደጋ ክስተት መዋቅሮች ጋር በአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል አስተማማኝና የማያቋርጥ የመገናኛ መሳሪያ አማራጭ እንድኖር በማድረግ የመረጃ ፍሰቱንና የአደጋ ምላሽ አሰጣጡን ማዘመን ይኖሪበታል፡፡
- ኮሚሽኑ አደጋ በይፋ መገለፁን ተከትሎ የአደጋ ስራ አመራር ም/ቤት ሲወስን ከአገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ሀብት በማሰባሰብ ለአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ስራ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የሃብት ማሰባሰብ፣ አስተዳደር፣ የፕሮጀክት አደረጃጀትና ሂደት፣ የፈንድ ግንባታና ጠቀሜታ፣ የድጋፍ ግንኙነትን ህጋዊ የሆነና መንግስታዊ እውቅና ያለው የአሰራር መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ ለአደጋ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል በቂ ሀብት እንድፈጠር በማድረግ አደጋ በሚከሰትበት ወቅት መወሰድ የሚገባቸውን ተገቢ እርምጃዎች በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ ሊወስድ ይገባል፡፡

- ኮሚሽኑ ውጤታማ የሆነ የሀብት አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት በመዘርጋት አሰራሩን በህግ ማዕቀፍ፣ በደንብና በመመሪያ የተደገፈ የአሰራር ስርዓቶችን በማበጀት ስራዎችን በመስራት የሃብት ማሰባሰብና ፈንድ አስተዳደር መመሪያን በማዘጋጀት የአደጋ ምላሽ ዝግጁነት አቅም በሚፈለገው ደረጃ እንዲደርስ እና የሃብት ብክነትንና ስርጭትን፣ የግዥ አሰራርን እና ውጤታማነትን ቋሚ በሆነ አሰራር መገምገምና መቆጣጠር ይኖርበታል፡፡
- ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ሀብት ከውጭ ሀገር ለማሰባሰብና ለመጠቀም መመሪያ በማዘጋጀት ለተረጂዎች ድጋፍ የሚውል ሀብት ወጥነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ በቂ የሀብት ክምችት መያዝና መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡
- ኮሚሽኑ በመዋቅሩ መሰረት የሰው ሀይል ሊያሟላ እና በአደጋ ክስተት ስራ አመራር የተሰማራ የሰው ኃይል እውቀቱንና ክህሎቱን በስልጠና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማዳበር እንዲያስችል የስልጠና ማዕከል በማቋቋም ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ በአደጋ ክስተት ስራ ዙሪያ የሚወጡ ህጎች፣ መመሪያዎች፣ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች እንዲሁም የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎች ውስጥ ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ ለአረጋዊያን፣ ለአካል ጉዳተኞችና ኤች.አይቪ. ኤዲስ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ ትኩረት ስለመሰጠታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር ስርዓትን ለመዘርጋትና ለመተግበር የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በየደረጃው ሊያከናውን ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ በክልሎች መካከል በአደጋ ጊዜ ተደጋግፎና ተባብሮ የምላሽ ስራን ለመስራት የሚያስችል አሰራር ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የኮሚሽኑ የመረጃ አስተዳደርና ኮሙኒኬሽን ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና በአደጋ ክስተት ስጋት ፕሮፋይል ላይ የተመሰረተና ወቀታዊ ለሁሉም ተደራሽ በማድረግ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎችን ኢኮኖሚዊ ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንድሆን ማድረግ አለበት፡፡
- ኮሚሽኑ ከውጭ በዕርዳታ መልክና በግዥ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባቸውን ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውሉ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች በወቅቱ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ በማድረግ የሃብት ስርጭትን በተገቢው ጊዜ ለተረጂዎች ሊያደርስ ይገባል፡፡

- ኮሚሽኑ ወደ ክምችት መጋዘኖች የሚገቡ/በክምችት ያሉና የሚወጡ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች የተቀመጠውን የጥራት ደረጃ ያሚሉ ስለመሆናቸው በመከታተል እና በመቆጣጠር ጥራቱን እና ደረጃውን የጠበቀ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ለተረጂዎች እንድደርስ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ ቅርጫፍ ጽ/ቤቶችን (ማዕከላዊ መጋዘኖችን) ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል አደረጃጀት እና የግባት አቅርቦት በሚሟላት ባግባቡ በመምራት፣በማስተባበርና በመቆጣጠር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሙሉ አቅማቸውና በአደጋዎች ስፋትና ደረጃ ልክ የምላሽ ስራውን ለማቀላጠፍ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ውጤታማ እንድሆን መስራት ይጠበቅበታል፡፡
- ኮሚሽኑ የክምችትና የስርጭት መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ በማድረግና በየደረጃው ተፈፃሚ ስለመሆኑ በመከታተልና በመቆጣጠር የእርዳታ ቁሳቁስ ስርጭት ላይ የምፈጠረውን ብልሹ አሰራር ማስወገድ ይኖሪበታል፡፡
- ኮሚሽኑ ለምላሽ ስራ የሚውል መጠባበቂያ በጀት፣ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ እንዲሁም በተጨማሪ በመንግስት የሚመደብና በእርዳታ የሚሰበሰብ ሀብት በአግባቡ ለምላሽ ስራው ጥቅም ላይ መዋሉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይልን መነሻ ያደረገ የመጠባበቂያ ዕቅድ በየጊዜው ሊያዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ ለቅፅበታዊ አደጋ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ቀልጣፋ አሰራርና የሎጂስቲክስ አገልግሎት በመዘርጋት ተግባራዊ በማድረግ የምላሽ አሰጣጥ ስርዓቱን ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንድሆን ማድረግ አለበት፡፡
- ኮሚሽኑ አስፈላጊ ቋሚ ንብረቶችንና መገልገያ መሳሪያዎችን በሚሟላት፣መወገድ የሚገባቸውንም በወቅቱ በማስወገድ የአደጋ ምላሽ ስራውን በጥራትና እንዲሁም የተቀላጠፈና ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡
- ኮሚሽኑ በአደጋ የተጎዱ ወይም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ እንስሳቶችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ በአደጋ የተጎዱ ወይም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ እንስሳቶችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር በመዘርጋትና ተግባራዊ በማድረግ በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ ችግሮች ምክንያት በእንስሳቶች ላይ የሚከሰቱ ችግሮች በዜጎች እና በሀገር ኢኮኖሚ የከፋጉዳት እንዳይደርስ መስራት ይጠበቅበታል፡፡

- ኮሚሽኑ ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘረጋትና ተግባራዊ በማድረግ ያከናወናቸው የአደጋ ምላሽ እና የመልሶ ማቋቋም ስራዎችን ውጤታማነት ማረጋገጥ ይኖሪበታል፡፡
- ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር በመንግስት የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የልማት ዕቅድና ፕሮግራሞች፣ በግል መ/ቤቶች ዕቅዶች እንዲሁም በስርዓተ-ትምህርት መካተቱን በማረጋገጥና ድጋፍ በማድረግ የአደጋ ምላሽ ስራዎች በሁሉም ተቋማት ተገቢው ግንዛቤ ተወስዶ እንድሰራ እና አሰራሩ ውጤታማ እንድሆን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ኮሚሽኑ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች ተብለው የተሰየሙ የፌደራል መንግስት የአስፈፃሚ አካላት በዕቅዳቸው ውስጥ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ማካተታቸውን በማረጋገጥ እና አፈፃፀሙን በመከታተል የአደጋ ምላሽ ስራዎች በሴክተር መ/ቤቶች ኃላፊነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ እንድከናወንና ምላሹ የተሟላ እና ውጤታማ እንድሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ ከመሪ ሴክተር መ/ቤቶች፣ ከክልሎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው የስራ ግንኙነት በአሰራርና አደረጃጀት የተጠናከረ እና የተጠያቂነት አሰራር እንድኖር በማድረግ የአደጋ ምላሽ አሰጣጡ ውጤታማ እንድሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴዎች ከአካባቢ ሁኔታ ጋር የሚስማሙ መሆኑን ሊገመግምና ለአካባቢ ጥበቃ ትኩረት መስጠታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡




አባሪ አንድ :-የኮሚሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር

## አባሪ ሁለት

## <u>የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች</u>

1. ኮሚሽኑ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴዎች ከአካባቢ ሁኔታ ጋር የሚስማሙ መሆኑን ሊገመግምና ለአካባቢ ጥበቃ ትኩረት መስጠታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
2. ኮሚሽኑ ያከናወናቸውን የመልሶ ማቋቋም ስራዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትልና ግምገማ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
3. ኮሚሽኑ የአደጋ ምላሽ ፕሮግራሞችን ሊያስተባብር፣ ሊከታተልና ሊገመግም ይገባል፡፡
4. ኮሚሽኑ ማንኛውንም መሪ ሴክተር መስሪያ ቤትን የማይመለከት ወይም ከመሪ ሴክተር መ/ቤት አቅም በላይ የሆነ ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥም የምላሽ ስራውን ሊሰራ፣ ሊመራ እና ሊያስተባብር ይገባል፡፡
5. ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ ክምችት ሊይዝ፣ ሊያስተዳድር እና ለምላሽ ስራ ሊያውል ይገባል፡፡
6. ኮሚሽኑ የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ምግብ ዕርዳታ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ስትራቴጂክ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችትን ከሚያስተዳድር የሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት የዕርዳታ እህል በመውሰድ የዕርዳታ እህል በወቅቱ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡
7. ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በአገር አቀፍ ደረጃ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ዝግጅትና ክለሳ ስራን ሊመራ እና ሊያስተባብር ይገባል፡፡
8. ኮሚሽኑ የአደጋ ጥናት መረጃ ላይ ያተኮረ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡
9. ኮሚሽኑ በቅድመ-አደጋ፣ በአደጋና በድህረ-አደጋ ወቅት የአደጋ ስጋት ትንበያን ጨምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ ጥናቶችንና ግምገማዎችን ሊመራ እና ሊያስተባብር ይገባል፡፡
10. ኮሚሽኑ የፌደራል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከልን ስራ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ ሊያስተዳድርና ሊመራ ይገባል፡፡
11. ኮሚሽኑ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከልን በፌደራል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ መስተዳድሮች በሚገኙ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች እንዲመሰረት ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
12. ኮሚሽኑ የመረጃና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል ሁኔታዎችን ሊያመቻችና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
13. ኮሚሽኑ በየደረጃው የሚቋቋሙ የአደጋ ክስተት ማስተባባሪያ መዋቅሮች በአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል አስተማማኝና የማያቋርጥ የመገናኛ መሳሪያ እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡

14. ኮሚሽኑ አደጋ በይፋ መገለፁን ተከትሎ የአደጋ ስራ አመራር ም/ቤት ሲወስን ከአገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ሀብት ሊያሰባስብ እና ለአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ስራ ጥቅም ላይ እንዲውል ሊያደርግ ይገባል፡፡
15. ኮሚሽኑ ውጤታማ የሆነ የሀብት አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
16. ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽ ሀብት ከውጭ ሀገር የማሰባሰብና የመጠቀም አሰራርን በተመለከተ መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
17. ኮሚሽኑ ለአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል ምግብ ነክ ያልሆነ ክምችት እና የአደጋ ጊዜ ፈንድ እንዲቋቋምና እንዲጠናከር ሊያደርግ ይገባል፡፡
18. ኮሚሽኑ በመዋቅሩ መሰረት የሰው ሀይል ሊያሟላ እና በአደጋ ክስተት ስራ አመራር የተሰማራ የሰው ኃይል እውቀቱንና ክህሎቱን በስልጠና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማዳበር እንዲያስችል የስልጠና ማዕከል በማቋቋም ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
19. ኮሚሽኑ በአደጋ ክስተት ስራ ዙሪያ የሚወጡ ህጎች፣ መመሪያዎች፣ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች ውስጥ ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ ለአረጋዊያን፣ ለአካል ጉዳተኞችና ኤች.አይቪ. ኤዲስ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ ትኩረት ስለመሰጠታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡
20. ኮሚሽኑ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎች ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ ለአረጋዊያን፣ ለአካል ጉዳተኞችና ኤች አይ ቪ ኤድስ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ ትኩረት ሊሰጥና ሊከታተል ይገባል፡፡
21. ኮሚሽኑ በአደጋ ስጋት ስራ አመራር ዙሪያ ያሉ አለም አቀፍ፣ አህጉር አቀፍ እና ክፍለ-አህጉር አቀፍ ስምምነቶችን፣ ህጎችን እና አሰራሮችን ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በመቃኘት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
22. ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር ስርዓትን ለመዘርጋትና ለመተግበር የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በየደረጃው ሊያከናውን ይገባል፡፡
23. ኮሚሽኑ በክልሎች መካከል በአደጋ ጊዜ ተደጋግፎና ተባብሮ የምላሽ ስራን ለመስራት የሚያስችል አሰራር ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
24. ኮሚሽኑ የመረጃ አስተዳደርና ኮሙኒኬሽን ስርዓት በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና በአደጋ ክስተት ስጋት ፕሮፋይል ላይ የተመሰረተ ሊያደርግ ይገባል፡፡
25. ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂን ስራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ህጎች፣ መመሪያዎችና ማዕቀፎችን ሊያዘጋጅ እና የአፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት ሊዘረጋና ተግበራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
26. ኮሚሽኑ ከውጭ በርዳታ መልክና በግዥ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባቸውን ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውሉ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች በወቅቱ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

27. ኮሚሽኑ የክምችት መጋዘኖች የሚገቡ/በክምችት ያሉና የሚወጡ ምግብ ና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች የተቀመጠውን የጥራት ደረጃ ያሟሉ ስለመሆናቸው ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡
28. ኮሚሽኑ ቅርጫፍ ጽ/ቤቶችን (ማዕከላዊ መጋዘኖችን) ሊመራ፣ ሊያስተባብርና ሊቆጣጠር ይገባል፡ ፡
29. ኮሚሽኑ የክምችትና የስርጭት መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ሊያደርግ እና በየደረጃው ተፈፃሚ ስለመሆኑ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡
30. ኮሚሽኑ ለምላሽ ስራ የሚውል መጠባበቂያ በጀት፣ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ እንዲሁም በተጨማሪ በመንግስት የሚመደብና በርዳታ የሚሰበሰብ ሀብት በአግባቡ ለምላሽ ስራው ጥቅም ላይ መዋሉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
31. ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይልን መነሻ ያደረገ የመጠባበቂያ ዕቅድ በየጊዜው ሊያዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
32. ኮሚሽኑ ቅፅበታዊ ለሆኑ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ቀልጣፋ የሆነ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
33. ኮሚሽኑ የመገናኛ ብዙሃንን በጠቀም ለአደጋ የሚሰጥ ምላሽን አስመልኮቶ ለህዝቡ የግንዛቤ ማስጨበጫና ወቅታዊ መረጃ እንዲደርስ ሊያደርግ ይገባል፡፡
34. ኮሚሽኑ አስፈላጊ ቋሚ ንብረቶችንና መገልገያ መሳሪያዎችን ሊያሟላ፣ሊስተዳድርና በአግባቡ ለአደጋ ምላሽ ስራና መለሶ ማቋቋም ሊያውል ይገባል፡፡
35. ኮሚሽኑ ለአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራ በራሱ ወይም በመንግስት የግዥ ተቋማት በኩል ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ግዥ ሊያከናውን እና ሊያከማች ይገባል፡፡
36. ኮሚሽኑ በአደጋ የተጎዱ ወይም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ እንስሳቶችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
37. ኮሚሽኑ ያከናወናቸውን የአደጋ ምላሽ ስራዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትልና ግምገማ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
38. ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር በመንግስት የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የልማት ዕቅድና ፕሮግራሞች፣ በግል መ/ቤቶች ዕቅዶች እንዲሁም በስርዓተ-ትምህርት መካተቱን ሊያረጋግጥና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
39. ኮሚሽኑ መሪ ሴክተር መ/ቤቶች ተብሎ የተሰየሙ የፌደራል መንግስት የአስፈፃሚ አካላት በዕቅዳቸው ውስጥ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ማካተታቸውን ሊያረጋግጥና አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡
40. ኮሚሽኑ የአደጋ ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞችን ሊያስተባብር፣ ሊከታተልና ሊገመግም ይገባል፡፡

41. ኮሚሽኑ በአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር ዙሪያ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ውጤታማ የሆኑ ተሞክሮዎችን ቀጣይነት ባለው መልኩ የመለየትና የማስፋፋት አሰራር ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
42. ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው መሪ ሴክተር መ/ቤቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጇታዊ አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

## አባሪ ሦስት

## በአዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ መ/ቤቶች ዝርዝር

1. የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
2. የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች
3. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአደጋ ስጋትና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት
4. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት፣
5. የሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምግብ ዋስትናና አደጋ መከላከል ጽ/ቤት
6. የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ቢሮ
7. የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
8. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የጌዲኦ ዞን የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ናቸው፡፡